በአዲስ ዓመት ዋዜማ ...

ገጽ 11

ትርጉም ያለው ግንኙነት ለመገንባት

ገጽ 14

የህዋና የከዋክብት ባህሪ በዘርፉ ሊቅ እይታ

ገጽ 20


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

84ኛ ዓመት ቁጥር 081 ኅዳር 21 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# ለሁለንተናዊ ብልጽግና የአምስት ዓመታት ውጤቶች

ገጽ 8



## ‹‹ያስመዘገብናቸው ውጤቶች ለነገ ተጨማሪ ድሎችና ስኬቶች ወረቶቻችን ናቸው››

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በልዕልና መር የህልም ጉዟችን ያስመዘገብናቸው ውጤቶች ለተጨማሪ ድሎች እና ስኬቶች እንድንተጋ የሚያደርጉ ወረቶቻችን ናቸው ሲሉ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ

ያስመዘገብናቸው ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል











## የኢኮኖሚ ማሻሻያው የወጪ ንግድ ትርፋማና ሳቢ እንዲሆን አድርጎታል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የወጪ ንግድ ትርፋማና ሳቢ እንዲሆን አድርጎታል ሲሉ የግል ዘርፉ አስመጪና ላኪ ተቋማት ገለጹ።

የላንፍሮንስ ትሬዲንግ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍሬው ደሳለኝ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ላንፍሮንስ ትሬዲንግ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች ላይ የተሰማራ ድርጅት ነው። ከቅባት እህሎች ሰሊጥን፤ ከጥራጥሬ ደግሞ ነጭ፣ጥቁርና ቀይ ቦለቄ እና መሰል ምርቶችን ለውጭ ገበያ ያቀርባል።

የኢኮኖሚ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል



ዶ/ር ደረጀ ዱጉማ

## የኤች አይቪን ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔን ስድስት በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል

ገጽ 8



# በክልሉ በቆላማ አካባቢዎች 85 ከመቶ በላይ የደረሰ ሰብል ተሰበሰበ

**ዓስማየሁ ግዛው**



አዲስ አበባ፡- በመኸር እርሻ ከለማው ውስጥ በቆላማ አካባቢዎች 85 ከመቶ በላይ የደረሰ ሰብል መሰብሰቡን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ ገለጸ፡፡

በማዕከለዊ ኢትዮጵያ ክልል በርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የግብርናና ገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ስሩር ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በመኸር ወቅት በልዩ ትኩረትና በጥንቃቄ ውጤታማ የምርት አሰባሰብ ሥራ እየተከናወነ ነው። በዚህም መሠረት በቆላማ አካባቢዎች 85 ከመቶ በላይ ምርት መሰብሰቡንና የምርት ብክነትንና የጥራት ጉድለትን በመከላከል ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡

የተዘራው ሰብል በሚሰበሰብበት ወቅት ብክነት እንዳይኖርና በአግባቡ እንዲሰበሰብ ከመስከረም 24/2017 ዓ.ም ጀምሮ የተቀናጀ የግብርና ልማት ሥራ ከክልል እስከ ቀበሌ የንቅናቄ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ኡስማን ገለፃ፣ ክልሉ ሦስት የአየር ንብረት ክልሎች (ደጋ፣ ወይና ደጋ እና ቆላ) የሚገኙበት ነው። የቆላው አካባቢ ሰብሉ ቀድሞ ስለሚደርስ ቀጥሎ የወይና ደጋ አካባቢዎች እና መጨረሻ ደግሞ የደጋ አካባቢ ሰብሎች እንደሚደርሱ ተለይተው «አንድም ፍሬ አትባክንም» በሚል ህብረተሰቡን ያሳተፈ የምርት አሰባሰብ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡

የምርት አሰባሰቡ በዘመናዊ መሣሪያዎች ታግዞ ህብረተሰቡን እና በጎ ፈቃደኞችን በማስተባበር እየተከናወነ እንደሚገኝ የጠቆሙት አቶ ኡስማ፤ የሃይማኖት አባቶች፣ ተማሪዎች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የጤና ባለሙያዎች እና ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን በመጠቀም ምርቱ ወቅቱን ካልጠበቀ ዝናብ ለመከላከል ልዩ ሥራ መከናወኑን አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም ሁሉንም ህብረተሰብ በማስተባበር የአረጋውያንን እና የአካል ጉዳተኞችን ምርት አሰባሰብ ቅድሚያ ተሰጥቶት በቅንጅት በኮምባይነሮች ጭምር እየተሰበሰበ እንደሚገኝ አቶ ኡስማን ገልጸዋል፡፡

ስንዴ፣ ገብስ፣ ጤፍ፣ በቆሎ እና የቦሎቄ ምርቶችን የመሰብሰብ ሥራ በደጋማ አካባቢዎች እስከ ጥር ድረስ እንደሚቀጥልም ጠቁመዋል፡፡

በፀደይ የእርሻ ወቅት 25 ሺ ሄክታር መሬት ቶሎ በሚደርሱ የሽንብራ፣ ጓያ እና ሌሎች ምርቶች መሸፈኑን ገልፀውም፤ ከዚህም ከአንድ ሚሊዮን በላይ ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ ተናግረዋል፡፡

ክልሉ ባለፈው ዓመት ህብረተሰቡን፣ ባለሀብቱን፣ አመራሩን እና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበርና በንቅናቄ ከ550 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በማረስ ከ49 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ለማምረት አቅዶ ወደ ሥራ እንደገባም አውስተዋል፡፡

በክልሉ ምርታማነትን ለማሳደግ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያሳተፈ የንቅናቄ ሥራም እንደተሠራም አስታውቀዋል፡፡

# ማዕከሉ የነፃ ህክምና አገልግሎትን በክልል ከተሞች ተደራሽ ሊያደርግ ነው

**ነፃነት አለሙ**

አዲስ አበባ፡- የነፃ ህክምና አገልግሎቱን በየክልል ከተሞች ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን በኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ህፃናት መርጃ ማዕከል ገለጸ፡፡

የማዕከሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ዶክተር ኤሌዘር ሃይሌ እንዳሉት፤ የማዕከሉ ነጻ የሕክምና አገልግሎቱን ከአዲስ አበባ ባለፈ በክልል ከተሞች የማስፋፋት ሥራዎች እየሠራ ይገኛል፡፡ በየክልል ከተሞች ለባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት የልብ ህሙማኑ በአቅራቢያቸው ክትትላቸውን እንዲያደርጉ ለማስቻል እየተሠራ ነው፡፡

እስካሁን ድረስም 14 ለሚሆኑ በህፃናት ህክምና ዘርፍ ለሚሠሩ ስፔሻሊስት ሀኪሞች ሥልጠና መሰጠቱን ገልጸው፤ እነዚህ የህክምና ባለሙያዎችም በተለያዩ የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ውስጥ አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ማዕከሉ የተለያዩ ተራድኦ ድርጅቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡና አገልግሎት እንዲሰጡ የማመቻቸት ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመው፤ ደረጃቸውን የጠበቁ የማዕከሉ ላብራቶሪዎችና ግብዓቶች እነዚህን ድርጅቶች ለመሳብ የሚያስችሉ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡

ክትትሉን ሳይጨምር በዓመት ከ500 እስከ 600 የሚሆኑ የልብ ቀዶ ጥገናዎች በማዕከሉ እንደሚሠሩ የገለፁት ዳይሬክተሩ፤ የውጭ ምንዛሪን ከማዳን አንፃር ማዕከሉ ቀላል የማይባል አስተዋፅኦ እንዳለው መገመት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

እያንዳንዱ ቀዶ ጥገና ቢያንስ ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን እስከ ሁለት ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር የሚገመት ወጪ እንደሚያስፈልገውም ጠቁመዋል፡፡ እንዲሁም ውጭ ሀገር ለመሄድ የሚያጋጥሙ ሂደቶችንና ድካሞችን ያስቀረ አገልግሎት መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

በዓለማችን ውድ ከሚባሉ ህክምናዎች ውስጥ የካንሰርና የልብ ህክምና ትልቁን ቦታ ይይዛሉ ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ማዕከሉ ለልብ ህክምና የሚሆኑ ግብዓቶችን ሙሉ በሙሉ ከውጭ እንደሚያስመጣ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አኳያ አሁንም ቀጣይነት ያለው እገዛና ድጋፍ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ማዕከሉ ሶስት ዋና ዋና አገልግሎቶችን እንደሚሰጥ ገልፀው፤ የመጀመሪያው የክትትልና የመድሃኒት ህክምና ሲሆን ከዘጠኝ ሺህ እስከ 12ሺህ የሚደርሱ ታካሚዎችን አገልግሎቱን እንደሚያገኙ አመልክተዋል፡፡

ሁለተኛው አገልግሎት ደግሞ ቀዶ ጥገና ሳይፈልግ በደም ስር ብቻ ተገብቶ ቀዶ ጥገናን መሥራት የሚያስችል ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህን አገልግሎት ለህፃናት ብቻ ሳይሆን ለአዋቂዎችም እንደሚሰጡ ጠቁመዋል፡፡ ማእከሉ በዋናነት ተደራሽነቱ ለህፃናት ቢሆንም ለአዋቂዎችም 25 በመቶ የሚሆነው አገልግሎት እንደሚያገኙ ተናግረዋል፡፡

ሶስተኛው የማዕከሉ አገልግሎትም ሙሉ በሙሉ ደረት ተከፍቶ የሚሠራ የልብ ቀዶ ጥገና መሆኑን የገለፁት ዳይሬክተሩ፤ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው የልብ ቀዶ ጥገና ህክምና በግል ዘርፉም መንገድ የከፈተ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡ በተጨማሪም ማዕከሉ ባለሙያዎችን በማሠልጠን ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን የተቋቋመ የልብ ቀዶ ጥገና ሀኪሞች ቡድን ያዋቀረ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ማዕከሉ ባለፉት 35 ዓመታት ምን አስተዋፅኦ አበርክቷል የሚል ጥናት መካሄዱን የገለፁት ዳይሬክተሩ፤ በውጤቱም ድሮ በጤና ችግር ምክንያት ከትምህርት ቤት ይቀሩ የነበሩ ልጆች መቅረት አቁመው ትምህርት ቤት መግባት እንደቻሉ እንዲሁም በተለያየ ዘርፍ ተመርቀው በሥራ ላይ እንዳሉ ማወቅ ችለናል ብለዋል፡፡

ማዕከሉ የመላው ኢትዮጵያ ቤት ነው፡፡ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ያስፈልገዋል ሲሉም ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል፡፡

“የገና ስጦታ ለልብ ህሙማን ህፃናት” በሚል መሪ ቃል እስከ ገና በዓል የሚቆይ የገቢ ማሰባሰቢያ ንቅናቄም በማዕከሉ ተጀምሯል፡፡

# የኢኮኖሚ ማሻሻያው የወጪ ንግድ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በፊት የወጪ ንግድ ብዙም ትርፋማ ያልሆነ አንዳንዴም በኪሳራ የሚሠራ የሥራ ዘርፍ መሆኑን የገለጹት አቶ ፍሬው፤ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በኋላ የወጪ ንግድ ትርፋማ የሥራ ዘርፍ ሆኗል። በተለይ ከውጭ ምንዛሬ ጋር ተያይዘው የሚነሡ ችግሮች መፍትሔ አግኝተዋል ነው ያሉት።

ይህም የሀገር ውስጥ አምራቾች ከማበረታታቱም በላይ የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮች ጭምር በዘርፉ እንዲሳተፉ እድል እየሰጠ መሆኑን ገልጸው፤ አርሶ አደሩ ጥሩ ክፍያ እንዲያገኝ አድርጎታል። የንግድ ዘርፉ ተዋናዮችንም በሙሉ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ያሳያል ብለዋል።

የበላይነህ ክንዴ ግሩፕ የገቢና ወጪ ንግድ ሥራ አስፈፃሚ አቶ እንዳሻው በላቸው በበኩላቸው፤ በላይነህ ክንዴ ግሩፕ ለዓመታት የቅባት እህሎችን በጥሬው ይልክ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ እሴት ጨምሮ ወደ መላክ ተሸጋግሯል ብለዋል።

ግሩፑ በቀጣይም ያለውን አቅም በማጠናከር በወጭ ንግድ ዘርፍ የላቀ ሚናውን ይጫወታል ያሉት አቶ እንዳሻው፤ ግሩፑ ለተከታታይ ዓመታት የቅባት እህሎችን ወደ ወጭ በመላክ በቀዳሚነት የሚጠቀስ ሲሆን ከ 700 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለሀገር ማስገኘት መቻሉን ገልጸዋል።

ከወጪ ንግድ የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ ይገባል። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በገቢም ይሁን በሌሎች መለኪያዎች የወጪ ንግድ ትርፋማ አድርጎታል ብለዋል።

በወጪ ንግድ ከተለመዱት የግብርና ምርቶች በተጨማሪ አዳዲስ ምርቶች ወደ ዘርፉ እንዲቀላቀሉ እንደሚያደርግ አቶ እንዳሻው ተናግረዋል።

ከሐምሌ 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ደግሞ የንግድና ኢንቨስትመንት መስኮችን ተወዳዳሪና ውጤታማ ለማድረግ፤ የሀገር ውስጥ ምርትና ምርታማነት አቅምን ማጠናከር፣ ጥራት ያለው አገልግሎት ለማቅረብና አጠቃላይ የሀገርን የምጣኔ ሀብት እድገት ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑን የኢኮኖሚ ምሁራን ገልጸዋል።

በዚህም መሠረት የማሻሻያ ትግበራው በተለያዩ የኢኮኖሚ አመላካቾች አመርቂ ውጤቶች እየተመዘገበበት መሆኑ ታውቋል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)፤ እንደ ሀገር የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያ ተግባራዊ መደረጉ ለኢኮኖሚ እድገት ማነቆ የነበሩ በርካታ ችግሮችን መፍታት አስችሏል ብለዋል።

በመጀመሪያው በሩብ ዓመት በወጪ ንግድ፣ በገቢና በሃዋላ ፍሰት የታዩ ውጤቶች ጥሩ ማሳያ መሆናቸውንም ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸው፤ በግብርና፣ በቱሪዝም፣ በማዕድንና በዲጂታል ዘርፎች የታዩ ውጤቶችም ማሻሻያው ፍሬ ማፍራት መጀመሩን ማሳያ ናቸው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በተያዘው የ2017 በጀት ዓመት 8 ነጥብ 4 በመቶ ዕድገት ያስመዘግባል ተብሎ እንደሚጠበቅም ጠቅሰዋል፡፡

# በአራት ዓመታት ሶስት ሺህ 300 አዳዲስ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ተመዝግበዋል

**መስከረም ሰይፋ**

አዲስ አበባ፡- ከለውጡ ወዲህ ሶስት ሺ 300 አዳዲስ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መመዝገብ መቻሉ የኢፌዴሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

የኢፌዴሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ምክትል ዳይሬክተር ፋሲካው ሞላ እንደገለጹት፤ ከባለፉት አራት ዓመታት ጀምሮ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሪፎርም እየተደረገ ነው፡፡ በሪፎርሙም ሶስት ሺ 300 አዳዲስ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መመዝገባቸውን ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜም ክልልን ጨምሮ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቁጥር ከስድስት ሺህ በላይ መድረሱን አመልክተው፤ ባለሥልጣኑ የሲቪል ድርጅቶች ቁጥር ከመጨመሩ ባለፈም ሥራቸውን ባግባቡ እንዲወጡ እየሠራ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ለዚህም ማሳያው የሲቪል ድርጅቶች በሰላም ግንባታ ፣ በአፋጣኝ ሠብዓዊ ርዳታ ፣ በተለያዩ የልማት ሥራዎችና በሽግግር ፍትህ ላይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በትኩረት እየሠሩ መሆኑ ገልጸዋል፡፡

ባለሥልጣኑ ባደረገው ሪፎርም በሥራቸው ለማህበረሰቡ መትረፍ ያልቻሉ እንዲሁም በተደረገላቸው ተደጋጋሚ ጥሪ በሥራ ላይ ስለመኖራቸው ቀርበው ማስረዳት ያልቻሉ አንድ ሺ 500 የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መታገዳቸውን ገልጸዋል፡፡

4ኛው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሳምንት "ለዘላቂ ሰላም እና ፍትሃዊ ልማት ቃልኪዳናችንን እናድስ" በሚል መሪ ቃል ከህዳር 27 እስከ ህዳር 29 2017 ዓ.ም እንደሚከበር የኢፌዴሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን አስታውቋል፡፡

በሌላ በኩል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሳምንት በዋናነት የዘርፉን ገጽታ ለመገንባት፣ ትስስር ለመፍጠር፣ በሰላም ግንባታ፣ አፋጣኝ ሠብዓዊ ርዳታ እና የልማት ሥራዎች ላይ ውይይት ለማድረግ ታላሚ ተደርጎ የተዘጋጀ ነው ብለዋል።

በዚህ ሳምንትም ከስድስት በላይ የፓናል ውይይቶች እንደሚካሄድና 80 የሚሆኑ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሥራዎቻቸውን የሚያስተዋውቁበት ኤግዚቢሽን እንደሚዘጋጅ ጠቁመዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የግሉንና የመንግሥት ዘርፉን በማስተሳሰር ሚዛናዊ ለማድረግና ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ መሆን የሚቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ሳምንቱም ድርጅቶች ራሳቸውን በደንብ እንዲያስተዋውቁ የሚረዳቸው መሆኑ አብራርተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አህመድ ሁሴን በበኩላቸው ምክር ቤቱ በሀገሪቱ ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ የመወከልና የማስተባበር ሃላፊነት በአዋጅ ያገኘ መሆኑ ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅትም ከአራት ሺህ በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባል መሆናቸውንና እነሱም በሽግግር ፍትህና በሀገሪቱ የሰላም ሁኔታ ላይ አተኩረው እየሠሩ የሚገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

አቶ አህመድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሪፎርም ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ የበለጠ እንዲጠናከር ድጋፍና ክትትል ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል።



አቶ ስዩም መኮንን

# ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በሠራችው ሥራ እውቅና አግኝታለች

## -የዴንማርክ መንግሥት ለኢትዮጵያ 15 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል ገብቷል

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በሠራችው ሥራ በኮፕ29 እውቅና ማግኘቷን የፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ የዴንማርክ መንግሥት ለኢትዮጵያ 15 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል መግባቱም ተመላክቷል፡፡

በ29ኛው የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያ የነበራትን ተሳትፎ በማስመልከት የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ትናንት ለመገናኛ ብዙሃን መግለጫ ሠጥቷል፡፡

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ስዩም መኮንን እንደገለጹት፤ በ29ኛው የተባበሩት መንግሥታት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ (COP29) ላይ በፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀሥላሴ የተመራ ልዑካን ቡድን ተሳትፏል፡፡ በጉባዔው ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እየሠራች ያለችውን ሥራ ለጉባዔዉ ተሳታፊዎች በማሳየት እውቅና ማግኘቷን አስታውቀዋል፡፡

ሀገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በአረንጓዴ ዐሻራ፣ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት፣ በሌማት ትሩፋት፣ በተፈጥሮ ቱሪዝም፣ በአረንጓዴ ከተማ ልማት፣ በታዳሽ ኃይልና በሌሎች ዘርፎች በርካታ ሥራዎችን እየሠራች መሆኑን አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እየሠራች ያለውን ሥራ ለማሳየት በኮፕ29 መካነ ርዕይ አዘጋጅታ ለዕይታ ማቅረቧን አንስተው፤ መካነ ርዕዩን በ12 ቀናት ውስጥ ከሁለት ሺህ 800 በላይ የተለያዩ ሀገራት ተሳታፊዎች እንደጎበኙት ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከአገኘችው እውቅና በተጨማሪም አጋርነቷን የሚያጠናክር ከ19 ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ውይይት ማድረጓን እና ከሩሲያ እና ዴንማርክ ጋር የመግባቢያ ስምምነት መፈራረሟን አመላክተዋል።

በዚህም መሠረት የዴንማርክ መንግሥት ለኢትዮጵያ 15 ሚሊዮን ዶላር ለመስጠት ቃል መግባቱን ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የፒፎርጂ (Partnering for Green Growth and the Global Goals 2030) ዓለም አቀፍ ጉባዔን በ2027 እንድታዘጋጅ መወሰኑን ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያን የኮፕ 29 ተሳትፎ የሚመለከቱ ዘገባዎች በሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ተላልፈዋ፤ በዚህም የኢትዮጵያን ገጽታ መገንባት ተችሏል

በሌላ በኩል በኮፕ 29 በተደረገው ድርድር ለታዳጊ ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እቅዶቻቸው መተግበሪያ የሚሆን 300 ቢሊዮን ዶላር እ.ኤ.አ 2035 ለመስጠት ቃል መገባቱን አስታውቀዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፣ የአየር ንብረት ኢንቨስትመንት ፈንድ 41 ሚሊዮን ዶላር ለተፈጥሮ ተኮር መፍትሔ የሚውል ድጋፍ ለማድረግ ተስማምቷል፡፡

የጣሊያን መንግስትም accelerator adaptation hub ለሚል ኢኒሼቲቭ 860 ሚሊዮን ዩሮ ለአፍሪካ ሀገራት ደግሞ ሁለት ነጥብ 94 ቢሊዮን ዩሮ ለመስጠት ቃል መግባቱን አስረድተዋል፡፡

# ሀገራዊ ኃይል የማመንጨት አቅም ከስድስት ሺህ ጊጋ ዋት በላይ ደርሷል

ፋንታነሽ ክንዴ



አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ኃይል የማመንጨት አቅም ከስድስት ሺህ ጊጋ ዋት በላይ መድረሱን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሚኒስቴሩ የኤሌክትሪፊኬሽንና የኢነርጂ መረጃ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ዳቢ እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር በሁሉም ዘርፍ በቂ የታዳሽ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር እየተሠራ ነው፡፡ በዚህም የኢትዮጵያ ከተለያዩ ምንጮች ኃይል የማመንጨት አቅም ከስድስት ሺህ ጊጋ ዋት በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ በሁለትና ሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥም ይህን ቁጥር በእጥፍ ለማሳግ እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በሁሉም ዘርፍ ነዳጅ ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ ታዳሽ ኃይል ላይ መሠረት ያደረገ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ በቂ የማመንጨት አቅም፣ ኃይል የማስተላለፍና መሠረተ ልማት መገንባት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የጠቆሙት አቶ መስፍን፤ ከ20ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ግንባታ ተከናውኗል፡፡ የማሰራጫ መሠረተ ልማቶችም ከ150 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ ደርሰዋል፡፡

ከዚህ በፊት የትራንስፖርት ዘርፉ ሙሉ በሙሉ የነዳጅ ምርቶች ላይ ጥገኛ ነበር ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ታዳሽ ኃይል ላይ መሠረት ያደረገ የትራንስፖርት አቅርቦት እንዲኖር በቂ የኃይል አቅርቦት ሊኖር ይገባል፡፡ ለዚህም ታዳሽ ኃይልን በሚመለከት ያሉ የተቋማት የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚጣጣሙ እንዲሆኑ ተደርጓል ነው ያሉት፡፡

ኢትዮ- ግሪን ሞቢሊቲ 2024 አውደ ርዕይና ኤግዚቢሽን ከነዳጅ ውጪ የታዳሽ ኃይል ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም የሚያስችል ሰፊ እድል መኖሩን የሚያሳይ መሆኑን ገልጸው፤ በሂደትም ነዳጅ ላይ መሠረት ያደረገውን የትራንስፖርት ዘርፍ ሙሉ በሙሉ ታዳሽ የሆነ የኃይል አቅርቦት ልንተካው እንደምንችል ያየንበት ነው ብለዋል፡፡

ታዳሽ ኃይልን መሠረት ያደረገ የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ ሥራ መግባት ከነዳጅ የሚወጣውን የካርቦን ልቀት በማስቀረት የአየርን ንብረት ለውጥን በመከላከል በኩል ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ገልጸው፤ በተጨማሪም ሀገሪቱ ለነዳጅ ግዢ በየዓመቱ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማስቀረትም ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዳለው ጠቁመዋል፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በሁሉም ዘርፍ ላይ የታዳሽ ኃይል አጠቃቀም እንዲያድግ እንደሚሠራ ጠቁመው፤ አምራች ኢንዱስትሪው፣ የትራንስፖርት ዘርፉ ብሎም በቤተሰብ ደረጃ ያለው የኃይል ፍጆታ ሙሉ በሙሉ በታዳሽ ኃይል ቴክኖሎጂዎች ላይ የተመሠረተ እንዲሆን እየተሠራ ነው፡፡

ለዚህም የኢነርጂ ልማቱ ታዳሽ ኃይልን መሠረት ያደረገና አካታች እንዲሆን የሚያስችል ፖሊሲ ተቀርጾ እየተተገበረ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የታዳሽ ኃይል ቴክኖሎጂዎች ከታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር እንዲገቡ ማድረግን ጨምሮ ዘርፉ ላይ የተለያዩ ማበረታቻዎች እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም የተፋጠነ የታዳሽ ኃይል ልማት እንዲኖር ያግዛል ብለዋል፡፡

# የተገነቡት መሠረተ ልማቶች ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉ ምቹ ሥነ ምህዳር ፈጥረዋል

## - የሀገር በቀል የቴክኖሎጂ አውደ ርዕይ በሳይንስ ሙዚየም ሲካሄድ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ባለፉት አምስት ዓመታት የገነባቸው መሠረተ ልማቶች ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉ ምቹ ሥነ ምህዳር ፈጥረዋል ሲል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ገለጸ።

ግሬስፌት የተሰኘ ዓለም አቀፍ የሀገር በቀል የቴክኖሎጂ አውደ ርዕይ ህዳር 23 እና 24 ቀን 2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሳይንስ ሙዚየም እንደሚካሄድ ተጠቁሟል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ባይሳ በዳዳ (ዶ/ር) አውደ ርዕዩን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ ግሬስፌት በየሁለት ዓመቱ በደቡባዊ ትብብር ድርጅት አማካኝነት የሚሰናዳ በሀገር ውስጥ የሚበለፅጉ ፈጠራዎችን እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከዓለም አቀፍ መድረኮች ጋር ለማጣጣም እንዲሁም ስልታዊ አጋርነቶችን ለማጎልበት የሚዘጋጅ ዓውደ ርዕይ ነው።

ድንበር ተሻጋሪ የንግድ ግንኙነት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማጠናከር ለዘርፉ እድገት ጉልህ ሚና አለው ያሉት ባይሳ በዳዳ (ዶ/ር)፤ ለዚህም መንግሥት ባለፉት ዓመታት የገነባቸው መሠረተ ልማቶች ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉ ምቹ ሥነ ምህዳር ፈጥረዋል ብለዋል።

ይህም ሀገራዊ መፍትሄዎችን እና ፈጠራዎችን በማሳየት የሀገር ውስጥ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ፣ በአዳዲስ ቴክኖሎጂ ፈጣሪዎች፣ አልሚዎች እና ኢንዱስትሪዎች መካከል ትብብርን ለማጎልበት ያስችላል ነው ያሉት።



ባይሳ በዳዳ (ዶ/ር)

ይህ ዓለም አቀፍ ዓውደ ርዕይ የቴክኖሎጂ አልሚዎችን፣ ሳይንቲስቶችን፣ የንግድ ማህበረሰቡን፣ የትምህርት ተቋማትን፣ የሲቪል ማህበረሰቡን፣ የሕዝብ እና የግል ዘርፍ ተዋናዮችን ከደቡባዊ ትብብር ድርጅት (OSC) አባል ሀገራት ህብረተሰብን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ገልፀዋል።

በደቡባዊ ትብብር ድርጅት (OSC) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ኃላፊ ሹመቴ ግዛው (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ አውደ ርዕዩ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና በደቡባዊ ትብብር ድርጅት (OSC) ትብብር የተዘጋጀ ነው። ይህም ህዳር 23 እና 24 ቀን 2017 ዓ.ም አዲስ አበባ ሳይንስ ሙዚየም ይካሄዳል ብለዋል።

የድርጅቱ አባል ሀገራት ቁጥር ኢትዮጵያን ጨምሮ 28 መሆናቸውን ገልፀው፤ አውደ ርዕዩ በሀገራቱ መካከል ቴክኖሎጂን ለማሳደግ፣ የገበያ እድል ለመፍጠር እና ሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሳደግ እንደሚያስችል ገልፀዋል።

በአውደ ርዕዩ በስድስት ዘርፎች 41 የቴክኖሎጂ ዳሶች ተዘጋጅተዋል። ተሳታፊዎች የዓውደ ርዕዩን ጎብኚዎች ሳይጨምር እስከ 500 ይደርሳሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል።

ከሀገር ውጭ ያሉና የዲፕሎማሲ ማህበረሰቡን ጨምሮ ወደ 200 የሚጠጉ ተሳታፊዎች ሲኖሩ፤ 300 የሀገር ውስጥ ተሳታፊዎች እንደሚገኙ ተናግረዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# “የኮሪደር ልማቱ አንድ የቱሪስት ከተማ ማሟላት ያለባትን መስፈርት አዲስ አበባ እንድታሟላ አስችሏታል ”

- ሂሩት ካሳው (ዶ/ር) የአ.አ ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ

እስማኤል አረቦ



ከተመሰረተች ከ130 ዓመታት በላይ የሆናት አዲስ አበባ የብሔር ብሔረሰቦች መናኸሪያ፣የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የአፍሪካ መዲና እና የተለያዩ አህጉር እና ዓለም አቀፍ ተቋማት መገኛ ነች። ከ90 በላይ ኤምባሲዎችን በማቀፍም በዓለም ላይ ካሉት ጥቂት የዲፕሎማቲክ ማዕከል ከሆኑት ከተሞች ውስጥ ግንባር ቀደሚ ነች።

አዲስ አበባ፣ ከአሜሪካዋ ኒውዮርክና ከሲውዘር ላንድ ጄኔቫ በመቀጠል ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ ውሳኔዎች የሚተላለፉባት፤ የዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ከተማ ሆና በባለብዙ የትብብር መስኮች አገልግሎት እየሰጠች ነው። ሆኖም ከተማዋ የእድሜዋን ያህል ባለማደጓ እና ጭራሹንም ልማቷ የኋሊት ሲጓዝ የቆየ በመሆኑ ከአፍሪካ ህብረት መቀመጫነቷ ጭምር ለማንሳት በርካታ ሙከራዎች ነበሩ።

ሆኖም የመንግሥትን ለውጥ ተከትሎ ከተማዋ ባገኘችው ትኩረት አዲስ አበባ እንደ ስሟ ውብ አበባ የመሆን እድል አግኝታለች። የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብሎም አፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ እንደ ስሟ አዲስ የሆኑ የልማት ስራዎች እየተከናወኑባት ነው። ከተማዋ በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ከቱሪስት መተላለፊያነት ወደ ቱሪስት መዳረሻነት የሚያበቋት የተለያዩ መሰረተ ልማቶችና የመዝናኛ ስፍራዎች በስፋት እየተከናወኑባት ይገኛሉ። የአንድነት ፓርክ፤የወዳጅነት አደባባይ፤ እንጦጦ ፓርክ የመሳሰሉት የቱሪስት መዳረሻዎች ከተማዋ እንደገና እንድታንሰራራ አድርገዋታል።

በመጀመሪያው ዙር የአዲስ አበባን ገጽታ ከመሰረቱ የሚለውጥ የኮሪደር ልማት በአምስት አቅጣጫዎች ተተግብሮ አዲስ አበባን ውበት አላብሷታል። በአሁኑ ወቅትም ሁለተኛው ዙር ኮሪደር ልማት በመፋጠን ላይ ይገኛል። የኮሪደር ልማቱ የተጎሳቆለውን አዲስ አበባ ገጽታ ለመቀየር ከማስቻሉም በላይ አዲስ አበባ ከአቻ ከተሞች ጋር መሳ ለመሳ እንድትቆምና የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት ማዕከል የመሆን እድል አግኝታለች። አስገራሚ በሆነ መልኩም የኮንፈረንስ ቱሪዝም መናኸሪያ ለመሆን በቅታለች።

የኮሪደር ልማቱ ትሩፋቶች የሆኑት የዓድዋ ሙዚየም፤ልዩ ልዩ የመስህብ ቦታዎች እና ማራኪ እይታዎች እና የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች ለስብሰባ የምትመረጥ ከተማ እንድትሆን አድርጓታል።

**የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብ እና አዲስ ለማድረግ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ለቱሪዝም ዘርፉ ምን አዲስ እድል ይዘው መጥዋል በሚል ከአ.አ ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሳው(ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርጓል። መልካም ንባብ።**

**አዲስ ዘመን፦ በአዲስ አበባ ባህልን፣ ጥበብንና ቱሪዝምን ለማሳደግ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ምንድናቸው?**

**ዶክተር ሂሩት፦** አዲስ አበባ ከዚሁ ጎን ለጎንም የመንገድ ዳርቻዎች ኮሪደር ልማት፤ የወንዝ ዳርቻዎች አዋሳኝ የተፋሰስ ልማት፣ የብስክሌትና ሞተር አልባ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ልማት፣ ዘመናዊ የትራንስፖርት ተርሚናሎች ግንባታ፣ አገናኝ የኮሪደር ልማት ድልድዮች፣ ማሳለጫዎችና የመጋቢ መንገዶች ልማት፣የመንገድ ዳር የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች፤ ፋውንቴኖች እና የሕዝብ መናፈሻ ስፍራዎች፣ ወጥ የህንጻ ቀለምና የከተማ ማብራት፣ ደረጃቸውን የጠበቁ ፓርኪንጎች፣የመኪና መጫኛና ማውረጃ አገልግሎቶችን ጨምሮ የአረንጓዴ ልማት ስራዎች የአዲስ አበባ መለያዎች ሆነዋል።ይህ የአዲስ አበባ ውበት እና ምቹነት ብዙዎችን ወደ ከተማዋ እንዲሳቡ እያደረጋቸው ነው።

ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ ከ30 በላይ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን በማስተናገድ ከወዲሁ የኮንፈረንስ ቱሪዝም መዳረሻነቷን አስመስክራለች። ባለፉት ሶስት ወራትም ከርሃብ ነፃ ዓለም ጉባኤ፣ የካፍ ጉባኤ፣ ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣ የአፍሪካ ንግድ ሚኒስትሮች ጉባኤና ሌሎች ጉባኤዎችን በስኬት ማስተናገድ ችላለች። በዚህም ከአፍሪካ አልፎ የዓለም የኮንፈረንስ ቱሪዝም መዳረሻ የመሆን አቅም ያላት ከተማ መሆኗን አስመስክራለች።

በአጠቃላይ አዲስ አበባን እንደ ስሟ ውብና አዲስ ለማድረግና አልፎ ተርፎም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ያሟላች ከተማ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ተስፋ ሰጪ ነው። የአዲስ አበባ ከተማ ገጽታ መለወጥም የአፍሪካ መዲናነቷን ለማጽናት ከማስቻሉም ባሻገር ከተማዋን የቱሪዝምና ኢንቨስትመንት መዳረሻ በማድረግ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ መነቃቃት የማይተካ ሚና እንድትጫወት አድርጓታል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ባህል እና ጥበብ ለማልማትና ለማሳደግ መሰረታዊ የሚባሉ መሠረተ ልማቶች በስፋት የተሰሩበትና የተመቻቹበት ጊዜ ነው። በተለይም ደግሞ ከአምስት ዓመት ወዲህ በቱሪዝም ዘርፍ የተሰራው የመስህብ ልማት ለኪነጥበቡና ለባህሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው። ቀደም ሲል በነበረው አስተሳሰብ ለባህል ብቻ ትኩረት ይሰጥ ነበር። አሁን ደግሞ ለቱሪዝም ተብለው የተሰሩ መስህቦችና መሠረተ ልማቶች ባህላዊ መቀራረብን እየፈጠሩ ይገኛሉ። በከተማዋ የሚሰሩ የመስህብ ስፍራዎችም የተለያዩ ባህሎችን እንዲያንጸባርቁ ተደርገው በመሰራታቸውም ለባህል እድገትም ሆነ ለቱሪዝም መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ።

ነባር የምንላቸውን የጥበብ ቦታዎችን እንደ የሀገር ፍቅር አይነቱን በማደስ፤ የአዲስ አበባ ባህልና ትያትር አዳራሽን ዘመናዊ የሆነ የትያትር ቤት እንዲሆን በማድረግ፣ ራስ ትያትርን በሰፊ ቦታ ላይ በአዲስ እንዲገነባ ቦታዎችንና የመሬት ይዞታን በማስተካከል በዘመናዊ መልኩ ለመስራት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ከተማዋ የባህል፣ የኪነጥበብ እና የቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን አድርጓታል።ለረጅም ዘመን ትኩረት አጥቶ የቆው የራስ ቲያትር ቤት ግንባታ ዲዛይን እያለቀ ነው። አሜሪካ ግቢ አካባቢ ግንባታውን ለማከናወን የመሠረተ ድንጋይ ተቀምጧል፤ በግዝፈቱ እና ዘመናዊነቱም ምናልባት እስከአሁን ካሉን ትያትር ቤቶች የተሻለ ነው።

ከዛ ውጪ የሕፃናትና ወጣቶች ትያትር ቤት ዕድሳት ከተጀመረ ቆይቷል። ማዕከል አካባቢ እየተገነባ ያለው ይኸው ማዕከል ግንባታው ለረጅም ዓመታት ተጓትቶ ቆይቶ በቅርቡ ነው የተጠናቀቀው። ይሄ እራሱ የጥበብ ሥራን የሚያሳድግ ነው። በተለይ ከታች ትውልዱን ኮትኩቶ የሚያመጣ ተተኪ ሕፃናትንና ወጣቶችን ኮትኩቶ የሚያወጣ (የጥበብ ፔዳጎጅካል ማዕከል) እንዲሆን ተደርጎ እየተሰራ ያለ ነው። በጣም ብዙ ማሰልጠኛዎች አሉት፤ መለማመጃዎች አሉት። የሕፃናት ፖምፔት ማሰልጠኛ፣ የስዕል፤ የዘመናዊና ባህላዊ ውዝዋዜ፣ የድምፅ፣ የትያትር፣ የድርሰት፣ ማሰልጠኛዎችንና መለማመጃዎችን የያዘ ነው። ሁለት ሲኒማ ቤቶችን እና ቤተመጻሕፍትን የያዘ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ዘርፉ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ለከተማዋ ምን ትሩፋት ይዘው መጡ?**

**ዶክተር ሂሩት፡-** በአጠቃላይ በአዲስ አበባ እየተገነቡ ያሉ የባህል፤ኪነጥበባት እና የቱሪዝም ማዕከላት ከተማዋ በሀገር ውስጥ ሆነ በውጪ ጎብኚዎች ተፈላጊ እንድትሆን አድርገዋታል።ወደፊት ደግሞ በእርግጠኝነት የአፍሪካ የአርትና የባህል ማዕከል ትሆናለች። እንደሚታወቀው አዲስ አበባ ሞዛይክ ናት፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩባት፤ የሁሉም ብሔር ብሔረሰብ ባህል ማንነት የሚገለፅባት ከተማ ናት። የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር እና የጋራ የወል ትርክት የምንፈጥርባት ከተማ ነች።በዚህ ረገድ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ለሀገራችን መሰረት መጣል ብቻ ሳይሆን ከእኛም አልፈን ለአፍሪካ ምሳሌ የምንሆንበት ስራ እየተሰራ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው።

**አዲስ ዘመን፡-ካለፉት አምስት ዓመታት አዲስ አበባን የቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ከተማዋ ለቱሪዝም ተመራጭ እንድትሆን ምን ያህል አስተዋጽኦ አበርክተዋል?**

**ዶክተር ሂሩት፡-** ከአምስት ዓመታት በፊት ለቱሪስት አዲስ አበባ መስህብ አላት ልሂድ ልጎብኝ ብሎ የሚመጣበት ምክንያት አልነበረውም። አዲስ አበባ ወደ ሌሎች ክልሎች ለሚደረጉ የቱሪስት ጉዞዎች መሸጋገር እንጂ መቆያ አልነበችም። ሆኖም ከመንግሥት ለውጥ ወዲህ ለዘርፉ በተሰጠው ትኩረት የአዲስ አበባ የቱሪዝም ትንሳኤ ሆኗል።

በአምስት ዓመታት ውስጥ ለአዲስ አበባ ቱሪዝም እምርታ የመጀመሪያ ተደርጎ የሚወሰደው ገበታ ለሸገር ነው። ከአንድነት ፓርክ ፣ ወዳጅነት ፣ እንጦጦ፣ ሳይንስ ሙዚየም፣ ዓድዋ መታሰቢያ ከተገነቡ በኋላ ግን የሀገር ውስጥም ሆነ የውጪ ቱሪስቶች አዲስ አበባ ውስጥ የሚገበኙ ነገሮች መኖራቸውን በመረዳት ከተማዋ ላይ ትኩረት አድርገዋል። በፊት መሸጋገሪያ ብቻ የነበረችው ከተማ ዛሬ እስከ 15 ቀናት ድረስ ሊገበኙ የሚችሉ ሀብቶችን በውስጧ አቅፋለች። ይህ ደግሞ አዲስ አበባን የመውጪያ መግቢያ የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን አስችሏታል።

እነዚህ ቦታዎች መስህብ ብቻ አይደሉም። ለምሳሌ አንድነት ፓርክ በርካታ ጎብኚዎች የሚያዩት ነገሮችን የያዘ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው። አንደኛ ታሪክ አለው ፤ የኢትዮጵያ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ከየት ተጀምሮ የት ይደርሳል የሚለው ታሪክ ይዟል። አደረጃጀቱ ታሪክን በመዝገብ ብቻ ሳይሆን በመስህብ ደረጃም አርትስቲክ በሆነ መንገድ የተቀመጠ ነው። ሁለተኛው ራሱ ቤተ መንግስቱን መጎብኘት ይቻላል። በዚህም የኢትዮጵያ ቤተመንግሥት ምን ይመስል ነበር ? አሁንስ ምን ይመስላል? የሚለውን ለማየት ያስችላል።

ሶስተኛው ተፈጥሮም ተጨምሮበታል። ቦታው የተለያየ ሀገር በቀል እጽዋት በርካታ የዱር እንስሳት አሉበት። በጥቅሉ ተፈጥሮን ይዟል። በተጨማሪም በተወሰነ ደረጃ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን የአኗኗር እና የአመጋገብ ሁኔታን ያሳያል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ቤት አሰራርና የተለየ መገለጫቸው የሆኑ ነገሮች አሉ። እነዚህን ነገሮች ሁሉ በአንድ ቦታ ማግኘት መቻል ትልቅ ነገር ነው። ይህ በቱሪዝም መስፈርትም ትልቅ የቱሪስት ማዕከል ያሰኘዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ተፈጥሮን ለፈለገ ደግሞ ወደ እንጦጦ ማምራት ይቻላል። በዚህ ቦታ በአዲስ አበባ ያሉ ተፈጥሯዊ እጽዋትን እንዲሁም ከፍታ ቦታ ላይ በመሆን አጠቃላይ የከተማዋን ገጽታ ለማየት የሚያስችልም ነው። በዚህ ውስጥ ደግሞ ከፈረስ ግልቢያ ጀምሮ ሕፃናትንም የሚያካትቱ በርካታ መዝናኛዎች አሉ። ደረጃቸውን የጠበቀ የሆቴልና ካፍቴሪያ አገልግሎትም ጎብኚዎች በዚህ ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# "የኮሪደር ልማቱ አንድ የቱሪስት ከተማ ማሟላት...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ወደ ወዳጅነት ፓርክ ሲመጣ ደግሞ የተለየ መልክአ ምድር ነው። የተለየ መዝናኛ በተለየ ሁኔታ ሰው ራሱን ሊያዳምጥበት የሚችል ቦታ ሆኖ ይገኛል። ከዚህም ባለፈ ከትልልቅ ኮንሰርቶች ጀምሮ ሠርግ፣ ስብሰባ፣ ስፖርት፣አትር እና ሌሎች ኩነቶችም ሊዘጋጁበት የሚቻል ነው።

ወደ ሳይንስ ሙዚየም ስንመጣ ደግሞ ዘመኑን የሚመጥን፤ የእውቀት መስመራችን ወዴት እየሄደ እንደሆነ የሚያሳይና የወደፊት የቱሪዝምን አቅጣጫም የሚያመላክት ነው። በዚህ ውስጥም ትልቅ የአውደ ርእይ የኮንፈረንስ ማእከል ይገኛል።

ወደ መስቀል አደባባይ ስንመጣ ደግሞ ለኮንሰርት፤ ለሕዝብ መሰብሰቢያ ፣ለስፖርት ማዘውተሪያ የተለያዩ በዓላት ማክበሪያ ለኢግዚቢሽን የሚሆኑ ዝግጅቶች የሚከናወኑበትን ዕድል ይዞ መጥቷል። ቦታው ሰዎች በጥንድም በተናጠልም ሊዝናኑበት የሚችል ቦታ ነው።

እነዚህ ቦታዎች በአጠቃላይ አዲስ አበባ ትክክለኛ የቱሪዝም መዳረሻ እንድትሆን ለማስቻል የተሰሩ ቦታዎች ናቸው። እነዚህም ስራዎች ዘመን ተሻጋሪ ከመሆናቸውም ባሻገር በየትኛው ዓለም ከሚገኙ የቱሪስት መስህቦች የሚስተካከል ውበት እና ዘመናዊነትን አጣምረው የያዙ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ከጠቃቀሷቸው በተጨማሪ አዳዲስ የቱሪስት መስህቦችም እየተገነቡ ነው። ለአብነትም የኢዮቤልዩ ቤተመንግሥትን ማንሳት ይቻላል።**

**ዶክተር ሂሩት፡-** አዲስ አበባ ላይ የቱሪስት መስህብ የሚሆኑ መዳረሻ ቦታዎች ዝግጅት የሚቀጥል ይሆናል። ቅድም ያላነሳሁልህና ትልቁ የኮንፈረንስ ቱሪዝም መናኸሪያ የሆነው አድዋ ድል መታሰቢያ ማእከል ነው። ይህ ማእከል ኢትዮጵያውያን በጋራ ሀገርን ለመገንባት ያደረጉትን ታሪክ ፤ያገኙትን ድል ለትውልድ የሚያስተዋውቅ ነው። የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም እርስ በእርስ የሚያስተሳስር ገመድ ሆኖ ትውልድ የሚማርበት ራሱን የሚገነዘብበት ነው። ከዚህም በላይ ደግሞ ማእከሉ በአሁኑ ወቅት ራሱን ችሎ የመስህብ ቦታ ለመሆን በቅቷል። በአሁኑ ወቅት በርካታ ቱሪስቶች እየጎበኙት ይገኛል። በከተማዋ እየተካሄዱ ካሉት ኮንፈረንሶች ዘጠና በመቶ የሚሆኑት በዚሁ ማእከል የተካሄዱ ናቸው።

ዓድዋ መታሰቢያ ማእከል በከተማ አስተዳደሩ የተገነባ ሲሆን፤ ከህዳሴው ግድብ ቀጥሎ ትልቁ ፕሮጀክት ነው። ይህም እስካሁን ከተገለጹት በላይ ለአዲስ አበባ ከተማ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ትልቅ እምርታ ያመጣ ነው። በአሁኑ ወቅት ደግሞ የአንድነት ፓርክ ሁለተኛ ክፍል የሆነው የኢዮ ቤልዩ ቤተ መንግሥት እየተጠናቀቀ ይገኛል። እሱ ሲመረቅ ደግሞ ትልቅ የቱሪስት መስህብ ለመሆን ይችላል።

የአዲስ ቱሞሮ ማዕከል ግንባታ ደግሞ ለአፍሪካውያን ጎብኚዎች ትልቁ የቱሪስት መዳረሻና መስህብ ሊሆን የሚችል ነው። ከአውሮፕላን ላይ ተሁኖ የሚታይና የአፍሪካ ቅርጽ የያዘም ነው። ይህም ሌላኛው ትልቁ መስህብ ይሆናል።በዚህ ማዕከል ውስጥ በርካታ ሆስፒታሎች ስለሚገነቡ ከተማዋ የጤና ቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን የሚያደርጋት ነው። ዘመናዊ የሆነው የአፍሪካ የስብሰባ ማዕከል (አፍሪካ ኮንቬንሽን ሴንተር ) ሌላኛው የከተማዋን የኮንፈረንስ ቱሪዝም እድገት የሚያፋጥን ነው።

በአጠቃላይ የአዲስ አበባ አቧራ እየተገለጠ ነው።አቧራ ለብሰው የነበሩ ታሪኮች ጿጋዎች እየተገለጡ ሲወጡ በየደረስንበት ሁሉ ደረጃቸውን የጠበቁ የቱሪስት መስህቦችን እናገኛለን ማለት ነው። አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ እንደ መሆኗ እና የኢትዮጵያን ታሪክ በውስጧ ከመያዟ አኳያ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ጎብኚዎች ዘንድ ተፈላጊ ከተማ እንድትሆን ያደርጋታል። አሁን እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ጎብኚዎች ከአስራ አምስት ቀን እስከ አንድ ወር ሊቆዩበት የሚችሉባት ከተማ እየሆነች ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ አበባ ከሌሎች አቻ ከተሞች አንጻር ያለችበት የመስህብ ደረጃ ምን ላይ ደርሷል ?**

**ዶክተር ሂሩት፡-** አዲስ አበባ በአሁኑ ወቅት ከየትኛውም ከተማ በተሻለ ቱሪስቶችን የሚያማልል መስህብ አላት። በዓለም ላይ ያሉ የቱሪዝም አይነቶችን በአንድ ከተማ ውስጥ ማግኘት አይታሰብም፤ በአንድ ከተማ ውስጥ ሁለት ቢበዛ ሶስት አይነት የቱሪስት መስህብ ቢኖር ነው። አዲስ አበባ ግን ከአስር የበለጠ መስህብ ያላት ከተማ ነች።የስፖርት ቱሪዝም ፣ የንግድ ቱሪዝም፣ የትምህርት ቱሪዝም ፤ የባህል የተፈጥሮ ቱሪዝም ፤ የታሪክ፣ የቅርስ የቱሪዝም አይነቶች በአዲስ አበባ ይገኛሉ።ይሄን የትኛውም ከተማ ውስጥ ልናገኘው አንችልም። ከዚህ በላይ በአሁኑ ወቅት የኮንፈረንስ ቱሪዝም ለአዲስ አበባ ትልቁ ቱሪዝም ሆኗል፤ በአንድ ወር ውስጥ ብቻ ከ20 በላይ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ኮንፍረንሶችን አካሄደናል። በሩብ ዓመት ከ40 በላይ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ አካሂደናል።

የምግብ ቱሪዝምን ብንወስድ ወደ ባህላዊ ሬስቶራንቶቻችን የሄደ ቱሪስት ተደስቶ ነው የሚመለሰው። ምን አልባት እጥረት ያለብን የውሃ ቱሪዝም ብቻ ነው።ይሄ ደግሞ ወደ ፊት በትኩረት ከሚሰሩት ውስጥ ነው። ሆኖም ፍል ውሃ ከፍተኛ የጤና ቱሪዝም የሚሆን ነው።

የጤናን ጉዳይ ካነሳን ባሉን ሆስፒታሎች በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎች እየመጡ እየታከሙ ነው። ለምሳሌ ኤርትሪያ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን፣ የመሳሰሉ ሀገራት ዜጎች እዚህ መጥተው ይታከማሉ፣ በተለያዩ ሆስፒታሎቻችን ዳታው ስላለን ነው። ይህም በቀጣይ ተጠናክሮ የሚቀጥል ነው።

በአጠቃላይ በአንድ ሀገር ወይንም በአንድ ከተማ ውስጥ የቱሪስት መዳረሻዎች በአይነትም በመጠንም መብዛት ሁለት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። አንደኛው በዓለም ላይ ያሉ ቱሪስቶችን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል ይሆናል። አንዳንዱ ቱሪስት ማየት የሚፈልገው ተፈጥሮን ይሆናል። ሌላኛው ደግሞ መዝናኛ ይፈልጋል፤ ሌላው ደግሞ ታሪካዊ መዳረሻዎችን ወይንም ቅርሶችን ማየት ይፈልጋል። አንዳንዶች ደግሞ ለምግብና ለስፖርት ብቻ ብለው የሚንቀሳቀሱም አሉ። በመሆኑም ሁሉንም ነገር ማካተት ከቻልን የቱሪስቶች አይን ወደእኛ መዞሩ አይቀርም።

ሁለተኛው ደግሞ የቱሪስት ቆይታ ጊዜ ረዘም ያለ መሆኑ ነው። ከቱሪስት መዳረሻነት የሚገኙ ተጠቃሚነቶች ሲታሰቡ አንድ ቱሪስት ወደ ሀገር ቤት ለጉብኝት መምጣቱ ብቻ ሳይሆን የሚቆይበትም ጊዜ ወሳኝ ነው። በዚህ ሁኔታ በርካታ ደረጃቸውን የጠበቁ መዳረሻዎች ሲኖሩ ቱሪስቶች መቆያ ጊዜያቸውን ለማራዘም ይገደዳሉ። ይህ ደግሞ ብዙ ገንዘብ ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚያስችል ይሆናል። አሁን ላይ አዲስ አበባ እንደ ከዚህ ቀደሙ በሶስት ቀን ቆይታ የሚሰናበቷት መሆኗ ቀርቶ ከአስራ አምስት ቀን በላይ የሚሰነብቱባት ከተማ ለመሆን በቅታለች ።

**አዲስ ዘመን፡- የኮሪደር ልማቱ ለቱሪዝም ዕድገቱ ምን እያበረከተ ነው**

**ዶክተር ሂሩት፡-** ኮሪደር ልማት ከቱሪዝም ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው የመሰረተ ልማት ስራ ነው። የኮሪደር ልማቱ ቅርሶቻችንን አጉልቶ በማውጣት፣ የበለጠ በመጠበቅ፣ በማደስ፣ በመጠገን ፊት ለፊት መጥተው እንዲታዩ የሚያደርግ ዘመናዊ አሰራር ነው። በተለይ በአዲስ አበባ የተሰራ የኮሪደር ልማት የቱሪዝምን ደረጃ በሚያሳድግ መልኩ ነው የተከናወነው። የኮሪደር ልማቱ አንድ የቱሪስት ከተማ ማሟላት ያለባትን መስፈርት እንድታሟላ አስችሏታል።

የኮሪደር ልማቱ የቱሪስቶችን ደህንነት እንዲጠበቅ የሚያደርግ ነው። መሰረተ ልማቱ ከመንገድ ባሻገር መብራቶች እና የደህንነት ካሜራዎች የተሟሉለት ነው። ቱሪስቶች በማታ መንቀሳቀስ ሊፈልጉ ይችላሉ። ቱሪስት በተሽከርካሪ ብቻ ሳይሆን በእግሩም በተለያዩ ቦታዎች እየተንቀሳቀሰ የመስህብ ቦታዎችን ለመጎብኘት ይፈልጋል። ለዚህ ደግሞ አካባቢው ውብ መሆን ብቻ ሳይሆን ንጹህ መሆን ያስፈልገዋል። ደህንነቱ የተጠበቀም ሊሆን ይገባል። በዚህ ረገድ አዲስ አበባ በቀን ብቻ ሳይሆን በማታም በብርሃን የተንቆጠቆጠች



**በአጠቃላይ በአዲስ አበባ እየተገነቡ ያሉ የባህል፤ ኪነጥበባት እና የቱሪዝም ማዕከላት ከተማዋ በሀገር ውስጥ ሆነ በውጪ ጎብኚዎች ተፈላጊ እንድትሆን አድርገዋታል፡ ፡ ወደፊት ደግሞ በእርግጠኝነት የአፍሪካ የአርትና የባህል ማዕከል ትሆናለች**

ሆናለች። ይህም ከውጪ ሀገራት ለሚመጡ እንግዶች ብቻ ሳይሆን ዜጎችም በእነዚህ አካባቢዎች ያለ ስጋት ንጹህ በሆነ ቦታ በነጻነት ለመንቀሳቀስ ያስችላቸዋል።

የኮሪደር ልማቱ መከናወንም ለቱሪስት የሚያስፈልገውን መሰረተ ልማት ለማሟላት ያስቻለ ነው። ከደህንነት ጀምሮ የተመቻቸ መንገድ እንዲኖር አስችሏል። መስህቡ እያለ እነዚህ ነገሮች ባይሟሉ ኖሮ ቱሪስት የሚመጣበት እድል አይኖርም ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- በቱሪዝም ረገድ አንዲት ከተማ ማሟላት ያለባት ምንድን ነው ?**

**ዶክተር ሂሩት፡-** የመጀመሪያው መስህብ ነው። ሳቢ ነገር ያስፈልጋል። ማለትም ቱሪስቱ ወደዚህ ሀገር ለመምጣት የሚስበው ነገር ያስፈልጋል። ለምሳሌ የሚጎበኝ ባህላዊ ነገር አለ ወይ? ተፈጥሮ አለ ወይ? ከሌላው ሀገር የተለየ እኛ ጋር ምን ተፈጥሮ አለን? የሚሉት መመለስ አለባቸው።ከዚህ አንጻር ከላይ እንዳነሳሁት አዲስ አበባ ሀብታም ነች።

ለምሳሌ መርካቶ ለእኛ አንዱ መስህባችን ነው። መርካቶ እቃ ለመግዛትና እቃ ለመሸጥ ተብሎ በሀገራችን የትኛውም አቅጣጫ ያለው ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ከአፍሪካም ከቻይናም ከቱርክም የሚመጡ ሸቀጦች መርካቶ ይገኛል። ስለዚህም መርካቶ የቱርክም የቻይናም ከተማ ነች።

ሌላው መስህባችን ስፖርት ነው። አሁን አሁን ታላቁ ሩጫ የሀገራችን ገጽታ ለሌላው ዓለም እያስታወቀ ነው። ኢትዮጵያ የስፖርተኞች ሀገር ከመሆኗ አንጻር በርካታ የስፖርት ቱሪዝም የሚኖራት ሀገር ነች። ባህላዊ አልባሳት፣ባህላዊ ምግብ ፣ነባር ቅርሶች ወዘተ አዲስ አበባን ተመራጭ ያደርጓታል።

ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ መሰረተ ልማት ወሳኝ ነው። ከመስህቦቹ ጋር አንደኛ መንገድ መኖር አለበት፤ ሁለተኛ ትራንስፖርት ከአውሮፕላን እስከ ታክሲ አጠቃላይ የትራንስፖርት አይነቶች መሟላት አለባቸው፤ ሌለው ትልቁ ነገር ሆቴል ነው። የሆቴል አገልግሎት መኖር ለቱሪዝም እንቅስቃሴ ወሳኝ ነው።

በአሁኑ ወቅት ደግሞ ቴክኖሎጂ መሰረታዊ ነገር ነው። ኢንተርኔት አለ ወይ? የተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ አመራጮች ማግኘት እችላለሁ ወይ? የሚሉ ጉዳዮች በቱሪስቶች የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው። መብራት፣ ውሃ የመሳሰሉትም አንድ የቱሪስት ከተማ ልታሟላቸው የሚገቡ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው። በዚህ ረገድ አዲስ አበባ ከሞላ ጎደል ብዙዎቹን ታሟላለች።

**አዲስ ዘመን ፡- ስለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ሂሩት ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ለሁለንተናዊ ብልጽግና የአምስት ዓመታት ውጤቶች

**ሞገስ ተስፋ**

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ በሕዝብ ጥያቄ ለውጥ ከመጣ ስድስት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ብልጽግና እንደፓርቲ ተቋቁሞ ሀገር መምራት ከጀመረ አምስት ዓመታት ሁኖታል። በእነዚህ ዓመታት በርካታ ለውጦችና ፈተናዎች ተስተውለዋል፡፡

ፈተናዎችን ወደ ዕድል በመቀየር ሕዝብ የሚፈልገውን የኢኮኖሚ፤ የማህበራዊና የፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ብልጽግና ፓርቲ ከግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ እስከ ኢንዱስትሪው፤ ከሌማት ትሩፋት እስከ ኮሪደር ልማት የመጡ ውጤቶች እንደ ማሳያ የሚገለጹ አብነቶች ናቸው፡፡

የብልጽግና ፓርቲ አምስተኛ ዓመት በማስመልከት የፓርቲው ፕሬዚዳንት እና የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ‹‹ለውጡና የለውጡ ፍሬዎች›› በሚል ባስተላለፉት መልዕክት፤ በሕዝብ ግፊትና በፓርቲ ሳቢነት የመጣው ሀገራዊ ለውጥ፣ የመጀመሪያውን ምእራፍ እየተሻገረ ነው፡፡ በዚህም የለውጡ ሃሳቦች በቃልና በተግባር ተገልጠዋል፡፡ የለውጡ ፈተናዎችም አካል ገዝተው በሚገባ በመገለጣቸው ሕዝብ አውቆ እንዲታገላቸው ተደርጓል፡፡ ይሄም የለውጡን ፍሬዎች ለማጎምራት፣ የለውጡን ፈተናዎችንም ለመርታት ዕድል መስጠቱን ተናግረዋል፡፡

ብልጽግና ፓርቲ ነባሮቹን ፖለቲካዊ ዕሴቶች በሚያጎለብትና የፖለቲካ ስብራቶቻችንን በሚጠግን፤ መልኩ ተመሥርቷል ያሉት ፕሬዚዳቱ፤ ይህም የለውጡ አንዱ ፍሬ ነው፤ ፓርቲው የዳርና የመሃል፤ ዋና እና አጋር፣ አርብቶ አደርና አርሶ አደር፤ ተራማጅና አድሃሪ፤ ጠላትና ወዳጅ፣ የሚባሉትን ግንቦች በማፍረስ በሃሳብ ላይ ብቻ የተመሠረተ የፖለቲካ አደረጃጀት መፍጠር እንደተቻለ በመልዕክታቸው አስፍረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት በኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካ ታሪክ ሲጠየቁ የነበሩ ጥያቄዎች ከቃል አልፈው ተግባራዊ ምላሽ አግኝተዋል፡፡ ለአብነት የፖሊሲ፣ የሕግ እና የአሠራር ብቻ ሳይሆን የባህል ለውጥ መጥቷል፡፡ ለውጡ ያለፉት የሀገሪቱን ስብራቶች የሚጠግን፣ ዛሬን የሚዋጅና የነገውን የኢትዮጵያ ጉዞ ያቀና ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የእምነት ተቋማት ከለውጡ በፊት በመንግሥት ጣልቃ ገብነትነት፣ ጥገኛነትና የህልውና ፈተና እንደነበረባቸው በማስታወስ፤ ከለውጡ በኋላ የእምነት ተቋማት ልዕልና ተከብሯል፡፡ ይሄንን ልዕልና ለማስከበርም መንግሥት በተቋማቱ ላይ ሲያደርግ የኖረው ፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነት እንዲቆም ተደርጓል ነው ያሉት፡፡

በተጨማሪም የሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት ቀደም ሲል የነበረውን የተንሸዋረረ አመለካከት በማስተካከል፣ ለሀገር በሚበጅ መልኩ በአዲስ ሕግና አደረጃጀት እንዲዋቀሩ አድርጓል፡፡ ከለውጡ በፊት አንድ ሺህ 900 የነበሩት የሲቪክ ማህበራት ባለፉት አምስት ዓመታት ብቻ ሶስት ሺህ 300 አዳዲስ ሲቪክ ማህበራት መመዝገባቸውን አመላክተዋል፡፡

የዴሞክራሲ ተቋማት ከነበረባቸው ችግር በመላቀቅ ነጻ፣ ገለልተኛና ተአማኒ እንዲሆኑ የሚያስችል የሕግና የአደረጃጀት ለውጦች ተደርጎባቸዋል፡፡ በተመሳሳይም የሚዲያ የብዝኃነት እንዲሻሻል አሣሪ ሕጎች ማሻሻል፤ የሚዲያ ተደራሽነትን ማበረታታት፣ ሚዲያዎች እርስ በርስ ራሳቸውን የሚቆጣጠሩበትን ሥርዓት የመዘርጋት ሥራዎች ስለመከናወናቸው አብራርተዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በለውጡ ዘመን የግብርና ኋላ ቀርነትን ቀርፎ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማስከበር በተሠራው ሥራ የባህል ለውጥ መጥቷል፡፡ ዝናብ ላይ መሠረት ያደረገውን የግብርና ባህል መስኖን በመጠቀም፣ በኩታ ገጠም እርሻና መሬት ጦም እንዳያድር በተሠራው ሥራ፣ ዓመቱን ሙሉ የሚመረትበት ባህል እያመጣ ነው፡፡

ስንዴን፣ ሩዝን፣ ገብስን፣ በቆሎንና የፍራፍሬ ምርቶችን ትኩረት አድርጎ በተሠራው ሥራ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀዳሚዋ የስንዴ አምራች ሀገር መሆኗን ጠቁመው፤ ስንዴን ከውጭ ማስገባት ወደ ውጭ መላክ ተሸጋግራለች። በሌማት ትሩፋት በተሠራው ሥራም የወተት፣ የዶሮና የማር ምርቶች በየቤተሰቡ ሌማት ላይ እንዲገኙ ሰፊ ሥራ መከናወኑን አመላክተዋል፡፡

ኢትዮጵያን ለማዘመን በተሠራው ሰፊ ሥራ የኢንዱስትሪ ምርታማነት ሥራ ላይ ከፍተኛ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረት እየተቻለ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ማዘመን ያለ ድጂታላይዜሽን የሚረጋገጥ ባለመሆኑ በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ፣ በዲጂታል ኢትዮጵያ እና በሌሎች ቴክኖሎጂዎች ላይ የሚያደርገው ምርምር እና የሚያፈሰው ሙዓለ ንዋይ እየጨመረ መጥቷል ነው ያሉት፡፡

በገበታ ለሸገር በአዲስ አበባ ከተማ ከተገነቡት የቱሪስት መዳረሻዎች በተጨማሪ፣ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት በጎርጎራ፣ በወንጪ፣ በሐላላ ኬላና በኮይሻ የቱሪስት መዳረሻዎች ተገንብተው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በገበታ ለትውልድ ደግሞ በሌሎች ሰባት የሀገሪቱ ክፍሎች እየተገነቡ ያሉት ፕሮጀክቶች ኢትዮጵያን ለማዘመን ከተደረጉ ጥረቶች መካከል ስለመሆናቸው ጠቅሰዋል፡፡

የኢትዮጵያን ከተሞች ለዜጎች ምቹ፣ ጤናማና አካታች ለማድረግ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ከአዲስ አበባ ተጀምሮ በአሁኑ ጊዜ ወደ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ ደርሷል ነው ያሉት፡፡

የጸጥታና የደህንነት ተቋማትን ለማዘመን በተሠራው ሥራ ሠብዓዊ፣ መዋቅራዊና ቴክኖሎጂያዊ ብቃት ያላቸው የጸጥታና የደህንነት ተቋማት ተፈጥረዋል ያሉት ዐቢይ( ዶ/ር)፤ ተቋማቱ ሕገ መንግሥቱን ብቻ መሠረት አድርገው ተልዕኳቸውን እንዲያከናውኑ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ ሆነዋል፡፡ የሕግ፣ የአሠራርና የአደረጃጀት ሪፎርም በማድረግ ኢትዮጵያን የሚመጥኑ ተቋማት እንዲሆኑ እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

ለውጡ እንዲመጣ ገፊ ከሆኑ ሀገራዊ ስብራቶች አንዱ የማክሮ ኢኮኖሚ ስብራት መሆኑን በመልዕክታቸው ያሰፈሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ስብራቱ ለመጠገን ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በመተግበር ሁሉን አቀፍ ሥራ ተሠርቷል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ተገቢና ትክክለኛ መሆኑን ዓለም በብዛት እንዲቀበለው ለማድረግ ተችሏል፡፡ በዓለም አቀፍ መድረኮችም ብሔራዊ ጥቅሞቿን ሊያስከብሩ በሚችሉ የሁለትዮሽና ባለ ብዙ ወገን ትብብሮች ላይ በጉልሕ እንደምትሳተፍ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው አስፍረዋል፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፤ እንደሀገር ከዚህ ቀደም የነበሩ መዛነፎችን ብልጽግና በመደመር እሳቤ ፍትሃዊነት እንዲሰፍን ማድረጉን በመጥቀስ፤ ድህነት ለማሸነፍ ፈርጀ ብዙ ፋይዳዎች ያሏቸው ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ያሉ አንጡራ ሀብቶች፤ እሴቶች፤ ባሕሎች፣ እሴቶችና አቅሞችን በመደመር ታላቅ ሀገራዊ አቅም ፈጥረናል ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ የሰላምና የልማት ሥራዎችን በማጠናከር በዓለም የፖለቲካና የኢኮኖሚ መድረክ ኢትዮጵያ የሚገባትን የመሪነት ሚና መጫወት እንደሚኖርባት ያስታወሱት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ብልፅግና ፓርቲ ያለ ዕረፍት በመሥራት የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ብልፅግና እውን ያደርጋል ነው ነው ያሉት፡፡

የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ፤ ብልጽግና ፓርቲ በለውጥ ትግል ውስጥ ተወልዶ በአዲስ እይታ፣ አዲስ ምዕራፍ ከፍቶ እያደገ ያለ ነው፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ መስኮች ሁለንተናዊ ብልፅግናን የሚያረጋግጡ አስደናቂ ውጤቶችን ማስመዝገብ ችሏል፡፡

የብልጽግና ፓርቲ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ ኃላፊ ቢቂላ ሁሪሳ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የተጓዘችው የአምስት ዓመት ጉዞ ስኬት ያስመዘገበችበትና ፈተናም የተጋፈጠችበት ነው፡፡ ሆኖም ግን በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ማኅበራዊና ዲፕሎማሲ መስክ ያስመዘገበቻቸው ድሎች ታላላቅ ናቸው።

ብልጽግና ፓርቲ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያቀፈ፣ ኅብረ ብሔራዊ፣ ሀገራዊና ወጥ ፓርቲ ሆኖ በመፈጠሩ ምክንያት ኢትዮጵያውያን በአንድ ጥላ ስር መሰባሰብ የቻሉበት ነው። ፓርቲው ከተመሠረተ ወዲህ የትርክት ለውጥ መጥቷል፤ ከሚለያዩን ነገሮች ይልቅ አንድ የሚያደርጉን እና አብሮነትን የሚፈጥሩ ትርክቶች እንዲጠናከሩ ማድረግ መቻሉን ይገልጻሉ፡፡

ቢቂላ(ዶ/ር)፤ ባለፉት አምስት ዓመታት በኢኮኖሚው በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሞች በማካሔዱ ኢኮኖሚውን ከመንኮታኮትና ከውድቀት የታደገ ፓርቲ ነው፡፡ የእዳ ማስተካከያ እና የእዳ ሽግሽግ በማስደረግ የሀገሪቱን የእዳ ጫና በማቃለልም ትልቅ ሥራ ተሠርቷል፡፡ ግብርና መር ብቻ ይባል የነበረው የኢኮኖሚ እሳቤ የብዝሃ ዘርፍ ኢኮኖሚ እንዲሆን ግብርናን፣ ማኑፋክቸሪንግን፣ ማዕድንን፣ ቱሪዝምን እና የዲጂታል ኢኮኖሚን አንድ ላይ በማጣመር የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዘርፎች ሚዛናቸውን ጠብቀው እና ተደጋግፈው እንዲያድጉ ማድረግ ያስቻለ ሥራ መሥራቱን አስረድተዋል፡፡

## ‹‹ያስመዘገብናቸው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማዕከል ኃላፊና የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ገለጹ፡፡

አቶ አደም ፋራህ የብልፅግና ፓርቲ 5ኛ ዓመት የምሥረታ በዓልን በማስመልከት ባስተላለፉት መልዕክት፤ ብልፅግና ህዳር 21 ቀን 2012 ዓ.ም በለውጥ ትግል ውስጥ ተወልዶ በአዲስ ዕይታ፣ አዲስ ምዕራፍ ከፍቶ እያደገ ያለ ፓርቲ ነው፡፡ ባለፉት 5 ዓመታት በልዕልና መር የህልም ጉዟችን ያስመዘገብናቸው ውጤቶችም ለነገ የቤት ሥራችን አቅም ሆነው ለተጨማሪ ድሎች እና ስኬቶች እንድንተጋ የሚያደርጉ ወረቶቻችን ናቸው ብለዋል፡፡

ፓርቲው ባለፉት 5 ዓመታት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊ እና ዲፕሎማሲያዊ መስኮች ሁለንተናዊ ብልፅግናን የሚያረጋግጡ አስደናቂ ውጤቶችን ማስመዝገብ እንደቻለ ጠቅሰው፤ ዛሬ ላይ በሪፎርም የተመዘገቡ ድሎችን ለማስቀጠልና ወደ እመርታ ለመሸጋገር በብቃት እየተዘጋጀ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ትናንት በሕዝባችን የለውጥ ፍላጎት እና ተራማጅ የለውጥ እሳቤን ባነገቡ ብርቱ መሪዎቻችን ጥረት ታግዘን የጀመርነው የለውጥ ጉዞ ብልፅግና ፓርቲን ወልዷል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በተመሠረተ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያን የዓለም ፈርጥ ምድራዊት ኮከብ ሊያደርጉ የሚችሉ መሠረቶችን ጥሏል ነው ያሉት።

በልዕልና መር የህልም ጉዟችን ያስመዘገብናቸው ውጤቶች ለነገ የቤት ሥራችን አቅም ሆነው ለተጨማሪ ድሎች እና ስኬቶች እንድንተጋ የሚያደርጉ ወረቶች መሆናቸውን አመላክተዋል፡፡

ያልታዩ እምቅ ሀብቶችን እንዲታዩ፣ በአቧራ የተሸፈኑ እልፍ ውበቶች እንዲገለጡና አይደፈሬ የሚመስሉ ተግዳሮቶችን በመጋፈጥ ሀገርን ከብተና ማዳን መቻሉን ጠቅሰው፤ በሁላችን ከሁላችን ለሁላችን የሆነች ህብረ-ብሔራዊ አንድነቷ የተጠናከረ ኢትዮጵያን ለመገንባት ሌት ተቀን ለፍተናል ብለዋል።

እያንዳንዱ ሰኮንድ እና ደቂቃ ያለ ትጋት እንዳያልፍ በፍጥነትና በፈጠራ የገሰገስንበት መንገድ የፓርቲያችንን 5ኛ ዓመት የምሥረታ በዓልን በሁለንተናዊ ድሎች ታጅበን የምናከብርበት ጊዜ ላይ ሊያደርሰን ችሏል ብለዋል። ስንዴን የሀገር ውስጥ ፍላጎታችንን ከማሟላት አልፈን ኤክስፖርት ያደረግነው፣ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ፕሮጀክትን ነፍስ የዘራንበት፣ የዲፕሎማሲ መልህቃችን ከብሪክስ ጥምረት ጋር የቀላቀለን፣ ተቆጥረው የማያልቁ ዘርፈ ብዙ ስኬቶችን ያስመዘገብነው በሕዝባችን ሁለንተናዊ ድጋፍ ታጅበን ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ የተወረወሩብን የጥፋት ቀስቶች የመከኑት ችግሮችን በብልሀት የመፍታት ጥበብን በማዳበራችን ነው ያሉት አቶ አደም፤ በፈተናዎች የማይዝል የደነደነ ትከሻን በመጎናፀፋችን፣ ለልማት እና ለብልፅግና የቀደመ ብሩህ እሳቤ በመከተላችን ውጤታማ መሆን ችለናል ነው ያሉት፡፡

"የሃሳብ ልዕልና ለሁለንተናዊ ብልፅግና" በሚል መሪ ቃል ሲከበር የቆየው የፓርቲው 5ኛ ዓመት የምስረታ በዓል አከባበር ሲጠናቀቅ ለተጨማሪ ድሎች ኃይላችንን የምናድስበት፣ ለሃሳብ ልዕልና እና በሀገራችን ኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ ያለንን ቁርጠኝነት የምናረጋግጥበት እንደሚሆን እምነቴ ነው ብለዋል።

# የኤች አይቪን ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔን ስድስት በመቶ ዝቅ ማድረግ ተችሏል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡ -ባለፉት አራት ዓመታት የኤች አይቪን ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔን ስድስት በመቶ ያህል ዝቅ ማድረግ መቻሉን ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ደረጀ ዱጉማ 36ኛውን የዓለም የኤች አይቪ ኤድስ ቀን በማስመልከት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት ፤ የኤች አይቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔን እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ኤች አይቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፍ ምጣኔ ከአራት ዓመታት በፊት ከነበረበት 14 ነጥብ 96 በመቶ በአሁኑ ጊዜ ወደ 8 ነጥብ 64 በመቶ ማድረስ ተችሏል።

ይህ ውጤት የተገኘው እናቶች በእርግዝና ወቅት ተገቢውን የህክምና ክትትል እንዲያገኙ፣ እንዲሁም በጤና ተቋማት እንዲወልዱ መሥራት መቻሉ መሆኑን ገልጸው፤ ለውጤቱ መገኘት የጤና ተቋማት ውጤታማ ሥራ አስተዋጽኦ ማድረጉ ተናግረዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ኤች አይቪ በደማቸው ከሚገኙ እናቶች የሚወለዱ ህጻናትም በወቅቱ የምርመራና ህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ቫይረሱን የመከላከል ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል።

ዶ/ር ደረጀ በዓለም ደረጃ በ2030 ኤች አይቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የመግታትና የመተላለፍ ምጣኔው ከአምስት በመቶ በታች ለማድረስ የተቀመጠ ግብ መኖሩንና ኢትዮጵያም ይህንን እየተገበረች ስለመሆኑ የተገኘው ውጤት ማሳያ መሆኑን አመልክተዋል።

በሀገር ደረጃ የኤች አይቪ ኤድስ ስርጭት መጠንን ዜሮ ነጥብ 87 በመቶ ማድረስ መቻሉን ጠቁመው፤ በሀገሪቱ የኤችይቪ ስርጭት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ቢመጣም በአሁኑ ትኩረት የሚሻ ነው ብለዋል፡፡

ዶ/ር ደረጀ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ባካሄደው ጥናታዊ ትንበያ መሠረትም በሀገሪቱ 606 ሺህ 238 ሰዎች ኤች አይቪ በደማቸው ውስጥ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በየዓመቱም ከሰባት ሺህ በላይ ሰዎች በኤች አይቪ ኤድስ እንደሚያዙ ገልጸው፤ ከእነዚህ ውስጥም 70 በመቶ የሚሆኑት ከ15 እስከ 29 እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡

የበሽታው የስርጭት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ቢመጣም በአዲስ አበባ፣ በሀረርና በድሬዳዋ ከተሞች እንዲሁም ጋምቤላ ፣ ትግራይና አማራ ክልሎች ያለው የስርጭት መጠን ከፍተኛ መሆኑ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ በ2030 ኤች አይቪ /ኤድስ የማህበረሰቡ የጤና ችግር ወደ የማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ እቅድ መያዟን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህንን ራዕይ ለማሳካት የተለያዩ ግቦችን አስቀምጣ በመተግበር ላይ ትገኛለች ብለዋል፡፡

በዚህም መሠረት እንደ ሀገር የኤች አይቪ ስርጭት ምጣኔ በ2010 ዓ.ም ከነበረበት አንድ ነጥብ 26 በመቶ አሁን ወዳለበት ዜሮ ነጥብ 87 በመቶ ዝቅ ማድረግ መቻሉን አመልክተዋል፡፡

90 በመቶ የሚሆኑ ህሙማን ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ መኖሩን እንዲያውቁ ፣ 94 በመቶ ያህሉን ደግሞ የጸረ- ኤች አይቪ መድሃኒት እንዲጠቀሙና መድኃኒት ከሚወስዱት ውስጥ 96 በመቶ ያህሉ የቫይረሱ ልኬት መጠን በሚፈለገው መጠን እንዲወርድ ማድረግ መቻሉን አብራርተዋል፡፡

ዶ/ር ደረጀ በ2030 ኤች አይቪ /ኤድስ የማህበረሰቡ የጤና ችግር ወደማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ በተያዘው እቅድ አተገባበር ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን ገልጸው፤ በተለይ በየደረጃው የሚገኙ የኤድስ ምክር ቤት በሚፈለገው መልኩ አለመቋቋምና ሥራ ላይ አለመሆን፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የኤች አይቪ/ ኤድስ ፕሮግራሞችን በባለቤትነት አለመተግበር በአስቸኳይ መፍትሄ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

የበሽታው ስርጭት አሁንም በማህበረሰቡ ላይ የጤና፣ የልማት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚ ችግሮችን እያስከተለ መሆኑን ጠቁመው፤ ከበሽታው አሳሳቢነት አንፃር አሁንም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

36ኛው የአለም የኤች አይቪ ኤድስ ቀን ህዳር 22 በሀገር አቀፍ ደረጃ ‹‹ሠብዓዊ መብትን ያከበረ የኤችአይቪ አገልግሎት ለሁሉም" በሚል መሪ ቃል እንደሚከበር ጤና ሚኒስቴር ትናንትና በሰጠው መግለጫ አስታውቋል፡፡

# ባሕላዊ ሕክምናን ለማዘመን

አስናቀ ፀጋዬ

ባሕላዊ ሕክምና ሀገር በቀል የሆነና በልምድ የዳበረ እንዲሁም በህብረተሰቡ ተቀባይነት ያገኘ እውቀት ሆኖ የእጽዋትንና የእንስሳትን ተዋጽኦ ወይም ማዕድናትንና የእጅ ጥበብን በመጠቀም የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት እንደሆነ ይነገራል። በኢትዮጵያ የባሕል ሕክምና ከጥንት ጀምሮ የነበረና ዘመናዊ ሕክምና ወደ ሀገሪቱ ከመግባቱ በፊት ሕዝቡ በስፋት ሲገለገልበት የቆየ ነው። ዘመናዊ ሕክምና በኢትዮጵያ ከተስፋፋም በኋላ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው የማህበረሰብ ክፍል የዚሁ የባሕል ሕክምና ተጠቃሚ መሆኑን ጥናቶች ያረጋግጣሉ።

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የባሕል ሕክምና ሙያ ያላቸው አዋቂዎች በተናጠልና በተበታተነ ሁኔታ አገልግሎቱን ለህብረተሰቡ ሲሰጡ ቆይተዋል። ህብረተሰቡም ከዘመናዊው ሕክምና ባልተናነሰ መልኩ የዚሁ ባሕላዊ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ ነበር። ሕክምናው በሳይንሳዊ መንገድ ተፈትሾና ተረጋግጦ ለማህበረሰቡ እንዲቀርብ ሲደረግ የነበረው ጥረትም ያን ያህል አልነበረም።


በአሁኑ ወቅት ግን በተለይ የአዲስ አበባ የባሕል ሕክምና አዋቂዎች ማህበር ተበታትነው እየሠሩ ያሉ በርካታ የባሕል ሕክምና ባለሙያዎችን በማሰባሰብና የማህበሩ አባል እንዲሆኑ በማድረግ ከሚመለከተው አካል ፍቃድ አግኝተው ለህብረተሰቡ የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ እየሠራ ይገኛል። ከዘመናዊው ሕክምና ጋር እንዲቀራረብም ከአዲስ አበባ ከተማ ጤና ቢሮ፣ ከአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣንና ከአርማወር ሃንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በጋራ እየሠራ ነው።

ሐኪም መኳንንት ብርሃኑ የባሕል ሐኪም ናቸው። ባሕላዊ ሕክምናን ለማዘመን በሚደረገው ጥረት ሙሉ ፍቃደኛ ሆነው ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ሲሰሩ ቆይተዋል። የባሕል ሕክምና በአግባቡና በሳይንሳዊ መንገድ ከተሠራበት ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን በመረዳትና ለዚህም ተባባሪ በመሆን በተለይ እንደ አዲስ አበባ ከተማ የባሕል ሕክምና አዋቂዎች ማህበር አባል በመሆን ሕክምናው እንዲሻሻል ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ የባሕላዊው ሕክምና ከዘመናዊው ጋር እንዲቀራረብና በጋራ ለመሥራት እንደ ማህበር እቅድ ተይዟል። የባሕል ሐኪሞች እውቀታቸውንና ሙያቸውን ለአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን እንዲያስመዘግቡም እየተደረገ ነው። እርሳቸውም የባሕል ሕክምና እውቀታቸውን ለአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን አስመዝግበው እየሠሩ ይገኛሉ። ለእውቀታቸው ጥበቃ አግኝተውም ሥራቸውን እንዲሰሩ ሆነዋል።

ባሕላዊ ሕክምናን ለማሳደግ፣ ለማዘመንና ራሱን የቻለ ለማድረግ እንደ ማህበር ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። በትምህርት ደረጃም የባሕል ሕክምና ሙያን ለማሳደግ ሥራዎች እየተከናወኑ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ትምህርት ቤት ለመክፈት እየተደረገ ያለው ዝግጅት ነው። ከዚህ በተጓኝ በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ፣ በአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣንና በአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት በኩል ሕክምናው የአዕምሯዊ ባለቤትነት እንዲኖረው በሳይንሳዊ መንገድ ተደግፎ አገልግሎት እንዲሰጥበት የተጀመሩ ሥራዎች አሉ። እነዚህ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ልጃቸው በላብራቶሪ ሳይንስ መመረቁን የሚናገሩት ሐኪም መኳንንት፤ ባሕላዊ ሕክምና ዘመናዊ መልክ ተላብሶ እንዲሰራበት ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ልጃቸው አብሯቸው እንዲሠራ ማድረጋቸውን ይገልፃሉ። ለሕክምናው ግብዓት የሚውሉ አንዳንድ መሳሪያዎችን ከውጭ ለማስመጣት ጥረት እያደረጉ እንደሆነም ይናገራሉ። በእነዚህ መሳሪያዎች አማካኝነት ለምርምር የሚያቀርቧው መድኃኒቶች



ሐኪም መኳንንት ብርሃኑ፤



አቶ ለሜሳ ነገራ፤

እንደሚኖሩም ነው ሐኪም መኳንንት የገለጹት። በሌላ በኩል ደግሞ የእፅዋት ግብዓት ችግር እንዳለም ጠቅሰው፤ በተለይ ሀገር በቀል እፅዋት እየጠፉ መሆናቸውንና ያሉትንም ለማግኘት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አስቸጋሪ መሆኑን ያስረዳሉ። እንዲያም ሆኖ ግን ከጉለሌ እፅዋት ማዕከል ጋር በመነጋገር ለባሕል ሕክምና መድኃኒት ግብዓትነት የሚውሉ እፅዋት በአንድ ቦታ የሚተከሉበት ሁኔታ እንዲመቻች ቃል እንደተገባም ይናገራሉ።

አቶ ለሜሳ ነገራ በአዲስ አበባ ጤና ቢሮ የመድኃኒትና የሕክምና አቅርቦትና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ስር የባሕል ሐኪሞች አስተባባሪ ሆነው ይሰራሉ። እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ የባሕላዊ ሕክምናን ከዘመናዊው ጋር ማቀራረብ ሲባል ሥራውን ዘመናዊነት በተላበሰ መልኩ እንዲያከናውኑ ነው። በባሕላዊ ሕክምና ሕዝቡ የሚያውቃቸው መድኃኒቶች አሉ። ለምሳሌ፡- ጤና አዳም፣ ነጭ ሽንኩርትና ፌጦ የመሳሰሉት በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚታወቁና ለመድኃኒትነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ የማያውቃቸው ነገር ግን የባሕል ሐኪሞች ብቻ የሚያውቋው መድኃኒቶች አሉ። እነዚህ መድኃኒቶች እንዳይዘረፉና እንዳይጠፉ በአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን እንዲመዘገቡ የማድረግ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። ይህም አራት መሠረታዊ ሃሳቦች አሉት። አንደኛው የቅጂ መብት ነው። ሁለተኛው የራስ መብት መሆኑን የሚያሳይ ነው። ሶስተኛው የራስ መብትንና የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነትን አጣምሮ የሚይዝ ነው። አራተኛው ደግሞ የጂኦግራፊያዊ መብት መሆኑን ይጠቁማል። እነዚህ የባሕላዊ ሕክምናን ምስጢራዊነት ለመጠበቅ ድጋፍም ያደርጋሉ።

ከዚህ አንፃር ባሕላዊ ሕክምናን ወደ ዘመናዊ ለማምጣት የተሠሩ ሥራዎች አሉ። አንዱና ዋነኛው ከአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን

**ባሕላዊ ሕክምና ወደ ዘመናዊነት እንዲመጣ ሕክምናውን በፖሊሲ መደገፍ ያስፈልጋል**

ያላቸው የመድኃኒት ቅመማ እውቀት ወደ ክሊኒካል ሙከራ አልፎ ወደ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን ሄዶ ወደ ሥራ የሚገባበት እድል አለው። ለምሳሌ፡- ኢትዮጵያ አብዛኛውን ዘመናዊ ስታርች ከውጭ ሀገር ታስገባለች። ይሁንና ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ቀላል በሆነ ዘዴ በስኳር ድንች ስታርች ማምረት ይቻላል። በዚህም የስኳር ድንችን በስፋት በማምረት የካሳቫ ዘይት ማምረት ተችሏል። በተመሳሳይ ነጭ ባሕር ዛፍ ላይ ዘይት በማውጣት ለጉንፋንና ሌሎች በሽታዎችን ለመከላከያ እንዲውል የማድረግ ጅምር ሥራዎች አሉ። ከዚህ አንፃር ወደ ዘመናዊነት እየተመጣ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ ባለፈ ባሕላዊ ሕክምና ወደ ዘመናዊነት እንዲመጣ ሕክምናውን በፖሊሲ መደገፍ ያስፈልጋል። ሀገር አቀፍ ፖሊስ በመንግሥት ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ ባሕላዊ ሕክምናን ስለማሻሻል ይጠቅሳል። ይህም አጀንዳው ትልቅ መሆኑን ያሳያል። ሀገር በቀል እውቀቶችን ማለትም ሕክምናውን፣ እደ ጥበቡን፣ ሸማውን ጨምሮ ለማሻሻል ትልቅ የሆነ አጀንዳ የብሔራዊ ፖሊሲ ላይ መኖሩ ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል።

አስተባባሪው እንደሚሉት፤ የባሕል ሕክምናው ሥርዓተ ትምህርትም ያስፈልገዋል። የባሕል ሐኪሞች እውቀታቸው እስከምን ድረስ ነው የሚለው መታወቅ አለበት። ለምሳሌ፡- የባሕል ሐኪም ሆኖ ለመሥራት ቢያንስ መጽሐፍ ማንበብ እንዳለባቸው ሕጉ ይገልፃል። ነገር ግን መጽሐፍ ማንበብ ብቻ በቂ አይደለም። ወደ ምርምር ሲኬድ የባሕል ሐኪሙ አብሮ ምርምር ማድረግ ይጠበቅበታል። ለባሕላዊ ሕክምና የትምህርት ሥርዓት መቅረፅም ሌላኛው ዘርፉን የማዘመኛ መንገድ ነው። ለዚህም የአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ጉለሌ እፅዋት ማዕከል ከአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ጋር በጋራ እየሠሩ ይገኛሉ።

የባሕል ሐኪሞች ያላቸውን እውቀትና ምስጢር መጠበቅ ግን መብታቸው ነው። በግዴታ አሳዩ ሊባሉ አይችሉም። ሕክምናውን ለማሳደግና ለማዘመን ግን በትብብር መሥራት ይቻላል። ለምሳሌ የባሕል ሐኪሞች ያሏቸውን እውቀት በጋራ ወደ ምርመር ማምጣት ይችላሉ። የባሕል ሕክምና ማህበራት አለን የሚሉትን እውቀት በራሱ በአንድ ቦታ ተሰባስቦ ጥናትና ምርምር ሊካሄድበት ይችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ የባሕል ሐኪሞች የሚሰሩባቸው የሕክምና ዘርፎች እንዳሏቸው ይታወቃል። ከዚህ አኳያ ሥርዓተ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። ለአብነት በጋና በባሕላዊ ሕክምና ላይ ትምህርት የሚሰጡ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች አሉ። በተመሳሳይ በናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካና በሌሎችም የአፍሪካ ሀገራት የባሕል ሕክምና የሚያስተምሩ ዩኒቨርሲቲዎች ይገኛሉ። ስለሆነም በእነዚህ ሀገራት የባሕል ሕክምና በጤና መድህን ሥርዓት ውስጥም ጭምር ገብተዋል። የባሕል ሕክምና ከዘመናዊ ሕክምና ጋር እንዲቀራረብ እያደረጉ ያሉት ጥረትም የሚደነቅ ነው።

በተቃራኒው ግን በኢትዮጵያ ያለው የባሕል ሕክምና ከዘመናዊው ጋር እንዲቀራረብ እየተደረገ ያለው ጥረት አናሳ ነው። አሁን ላይ ሕክምናውን ለማዘመን ግን በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በተለይ የባሕል ሐኪሞችን ማስተማርና የማብቃት ሥራ እየተሠራ ነው። የባሕል ሐኪሞቹ ከማንበብ በዘለለ ጠለቅ ያለ እውቀት ኖሯቸው የባሕል ሕክምናውን በዘመናዊ መንገድ እንዲከውኑ ለማድረግ መጠነኛ የትምህርት ሥርዓት ማዘጋጀት የግድ ይላል። ለዚህም ለምሳሌ፡- የሰውነት መዋቅር /anatomy/ ላይ ስልጠና እንዲወስዱ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመሆን የተጀመሩ ሥራዎች አሉ።

ብዙ ጊዜ የባሕል ሐኪሞች ብዙ ዓይነት ህመሞችን ቢጠየቁ ሁሉንም እንደሚያውቁና ማከም እንደሚችሉ ይናገራሉ። ይሁንና ይህ አሁን ላይ አይፈለግም። ለምሳሌ፡- የባሕል ሐኪሙ ወጌሻ ከሆነ ወጌሻ ላይ ብቻ ነው መሥራት ያለበት እንጂ በሌሎች ሕክምናዎች ላይ ገብቶ መሥራት አይጠበቅበትም። ለዚህም ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት መስጠት አይቻልም። ስለዚህ የባሕል ሐኪሞቹ የባለቤትነት መብት ካገኙ በኋላ ወደ ምርምር ይመጣሉ። በአዲስ አበባ ከተማም አብዛኛው የባሕል ሐኪም እውቀቱ በአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን ተመዝግቧል።

ወርልድ ኢንተሌክችዋል ፕሮፐርቲ ኦርጋናይዜሽን ከኢትዮጵያ የአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የባሕል ሐኪሞች በሙሉ እውቀታቸውን በአንድ የሕክምና ዘርፍ ብቻ እንዲያስመዘግቡ እየተደረገ ነው። በዚሁ መሠረትም የባሕል ሐኪሞቹ ሥራቸውን እያከናወኑ ይገኛሉ። ይህም የባሕል ሕክምናን አንድ ርምጃ ከማራመድ አኳያ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

አስተባባሪው እንደሚያብራሩት፤ የባሕል ሐኪሞች በፖሊሲ ደረጃ የመጀመሪያ ሕክምና አገልግሎት ይሰጣሉ እንጂ ከፍተኛ ደረጃ ያለውን ሕክምና እንዲሞክሩ አይፈቀድም። ፖሊሲውም ሆነ የቢሮ አሠራርም ይህንኑ ነው የሚደግፈው። ከዚህ ባለፈ ግን እንሠራለን የሚሉ የባሕል ሐኪሞች አሉ። ይህ ሲሆን የባሕል ሐኪሙ ስፔሻል ዘርፍ አለኝ ብሎ እንዲመጣና በአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን እንዲመደብ ይደረጋል። የጉበት ሕክምና ከሆነ ጉበት ላይ ብቻ እንዲያተኩር ይሆናልም።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ለባሕላዊ ሐኪሞች የአቅም ግንባታ ሥልጠና ከጤና ሚኒስቴርና ከምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመሆን ይሰጣል። የባሕል ሐኪሞቹ በሚሰሩባቸው ቦታዎች ላይ ከምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመሆን አሟልተው እንዲሠሩ ዝቅተኛውን ደረጃ ድጋፋዊ ክትትል ያደረጋል። ባሉበት ቦታ ከክፍለ ከተሞች ጋር ተገናኝተው ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያገኙም እድሉን ይፈጥራል።

ኢኮኖሚ

## ስኬት

# ፈር ቀዳጁ እሴት የተጨመረበት የሰሊጥ ምርት ላኪ

ማህሌት አብዱል

እሳቸውም ሆኑ መላው የቤተሰባቸው አባላት በጠንካራ የስራ ባህል ተኮትኩተው ማደጋቸውን ይናገራሉ። በሥራው ዓለም አርአያዬ የሚሏቸው የወላጅ አባታቸውን ትጋት እና የስራ ፍቅር እያዩ ማደጋቸው አሁን ላሉበት ደረጃ ወሳኝ መሰረት ጥሎላቸዋል።

አባታቸውን ብርቱ እና ሃገር ወዳድ ሲሉ ይገልጧቸዋል። አባታቸው በትምህርቱም ሆነ በንግድ ስራ የጠለቀ እውቀት እንዲኖራቸው በማድረግ የላቀውን ድርሻ እንደሚይዙ የዛሬው የስኬት አምድ እንግዳችን የኬ መቅድም አጠቃላይ አስመጪና ላኪ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ዶክተር ሙሉጌታ ኪዳነ ማርያም ይመሰክራሉ። ከልጅነታቸው ጀምሮ የተለያዩ የእህል አይነቶችን ከአርሶ አደሮች እየገዙ የመሸጥ የንግድ ስራዎች እየሰሩ ይገኛሉ።

የተወለዱትም ሆነ ያደጉት አዲስ አበባ ከተማ ነው። ከነጋዴ ቤተሰብ የተወለዱት እኚህ ሰው በጠንካራ ስራ ባህል ተኮትኩተው ቢያድጉም በትምህርትም ገፍተው እንዲሄዱ ወላጅ አባታቸው ከፍተኛ ድጋፍ የደርጉላቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። በዚህም በእንስሳት ሕክምና ትምህርት ዘርፍ ዶክትሬት ዲግሪያቸውን ይዘዋል።

ይሁንና አባታቸውን ለማገዝ በነበራቸው ጽኑ ፍላጎት መሰረት እንደተመረቁ ኬ መቅድም አጠቃላይ አስመጪና ላኪ በተሰኘው የአባታቸው ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ሁመራ በሚገኘው የሰሊጥ ማዘጋጃ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ሆነው ማገልገላቸውን ያስታውሳሉ።

‹‹እኛ ቤት ሁላችንም ሚዛን መዛኞች ነበርን፤ እንደአሁኑ ምርቱን በምርት ገበያ በኩል መላክ ሳይጀመር ግዢ ላይ ልናደርግ የሚገባንን ጥንቃቄ በቅጡ ተገንዝበን አድገናል፤ እኔም ጎበዝ መዛኝ ነበርኩ። ከፍተኛ ትምህርቴን እንደጨረስኩ ሁመራ የቅርንጫፍ ማናጀር ሆኜ ስመደብ የሰሊጥ ጆንያውን እየወጋሁ ጥራቱን እያየሁ፤ እየመዘንኩ በመግዛት ስራ ጀመርኩ›› ይላሉ።

ከተመሰረተ ከ29 ዓመታት በላይ በሆነው በዚሁ የአባታቸው ላኪና አስመጪ ድርጅት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ መስራት ከጀመሩ ወዲህ በተለይም ድርጅቱ የሚታወቅበትን የሰሊጥ ንግድ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ችለዋል። ስራውን በኃላፊነት መምራት ሲጀምሩ ድርጅቱ ሰሊጥ ምንም አይነት እሴት ሳይጨምር ከመላክ በዘለለ እሴት የተጨመረበትን ምርትም በመላክ ለሃገር የውጭ ምንዛሬ ግኝት እድገት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት ቆርጠው ተነሱ።

ይህንን ሕልማቸውን ለማሳካት ያስችላቸው ዘንድም በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የተባለውን የሰሊጥ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ከአሜሪካ ድርጅት ጋር በመተባበር ከፈቱ። እናም የኢትዮጵያን የሰሊጥ ቂቤ (ታሂኒ) በአውሮፓ መስፈርት (ስታንዳርድ) መሰረት በጥራት በማምረት ወደ ተለያዩ የዓለም ሃገራት መላክ ጀመሩ።

ጃፓን ቀዳሚዋ የድርጅታቸው ምርት መዳረሻ ሃገር መሆንዋን ጠቅሰው፣ በሌሎችም የዓለም ሃገራት ምርቱ ከፍተኛ ተቀባይነት ማግኘቱን ያስረዳሉ። ይሁንና በተለይ ባለፉት ዓመታት በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ በተከሰተው አለመረጋጋት ምክንያት የሰሊጥ ምርትና ምርታማነት መቀዛቀዝ ውስጥ ገባ፤ ሁመራ የሚገኘው ፋብሪካቸውም ተዘጋ። በዚህ የተነሳም የሰሊጥ ቂቤ (እሴት የተጨመረበት) ምርቱን በገበያው ፍላጎት መጠን ለማምረት አለመቻሉን ያስረዳሉ።

ይህን ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ተከትሎ በድርጅታቸው ላይ የተፈጠረው ጉዳት ብዙም አላስደነገጣቸውም። ከዚህ ይልቅ የድርጅታቸው ገቢ በእጅጉ እንዳይቀንስ ለማድረግ ይበልጥ ማውጣት ማውረድ ጀመሩ፤ የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ነድፈው በመስራትም ድርጅታቸውን ከኪሳራ መታደጋቸውን ያመለክታሉ። በተለይ እንደ ሚዲያ ማቀዝቀዣ ያሉ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ከሚመረቱባቸው ሀገሮች በቀጥታ በማስመጣትና ለሃገር ውስጥ ገበያ የሚያከፋፍል እህት ድርጅት በመክፈት የድርጅታቸውን አቅም ማጎልበት መቻላቸውን ይጠቁማሉ።

‹‹የድርጅታችን ዋና ስራ የኢትዮጵያ የግብርና ምርቶች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማድረግ ለሀገር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ነው›› የሚሉት ዶክተር



ሙሉጌታ ኪዳነ ማሪያም ዶ/ር

ሙሉጌታ፤ በአሁኑ ወቅት ድርጅታቸው ሁመራ እና ወለጋ የተባሉ ምርጥ የሰሊጥ ዝርያዎችን እንዲሁም የተፈተገውን ሰሊጥ እየላከ መሆኑን አስታውቀዋል።

እነዚህ ምርቶች ጃፓን ላይ ትልቅ ገበያ እንዳላቸው ጠቅሰው፣ እንደሃገር ለጃፓን ከሚሸጠው ሰባት ሺ ሜትሪክ ቶን ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው የእሳቸው ድርጅት የሚልከው ሰሊጥ መሆኑን ይጠቅሳሉ። ‹‹የእኛ ድርጅት እስከ 15 ሺ ቶን ሰሊጥ የመላክ አቅም ነበረው፤ በዓለም ገበያ ያለው ተቀባይነትም ከፍተኛ ነበር። ሆኖም በተለያዩ ሃገራዊ ችግሮች ምክንያት የምንልከው መጠን ቀንሷል። ባለፉት ዓመታትም የላክነው ሶስት ሺ ሜትሪክ ቶን ሰሊጥ ብቻ ነው›› ሲሉ ያብራራሉ።

በመሆኑም ድርጅታቸው በተያዘው ዓመት ወደ ውጭ የሚልከውን የሰሊጥ ምርት መጠን በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ እርሳቸውም ሆኑ መላው የድርጅቱ ባልደረቦች ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ‹‹ለዚህም ይረዳን ዘንድ አሁን ላይ በአዲስ አበባ የራሳችንን ዘመናዊ ማበጠሪያ ቤት ገንብተን ጨርሰናል። ስለዚህ የነበረብን የማበጠሪያ ቤት ችግር ስለተፈታ እንዲሁም ገበያው እጃችን ላይ ስላለ በያዝነው ዓመት ወደ ቀድሞ አቅማችን እንመለሳለን ብለን እናስባለን›› ሲሉም ያስረዳሉ።

ዶክተር ሙሉጌታ ድርጅቱን ከአባታቸው ሲረከቡ ስምንት ያህል ሰራተኞች ብቻ ነበሩት፤ እሳቸው ግን ከመላው ቤተሰባቸው ጋር በመሆን ተጨማሪ ድርጅቶችን ከፍተዋል። እነዚህ ድርጅቶችም የሰሊጥ ቂቤ ማምረቻ ኢንዱስትሪ (ታሂኒ)፣ የቡና ማበጠሪያ፣ ሪል ስቴት እና የኤሌክትሮኒስክ አስመጪ ድርጅቶች ናቸው። በእነዚህ ድርጅቶችም የቋሚና የጊዜያዊ ሰራተኞችን ብዛት ወደ 500 ማሳደግ መቻሉን ያመላክታሉ። የድርጅቱን የተመዘገበ ካፒታል ከ10 ሚሊዮን ወደ 400 ሚሊዮን ብር ማድረስ መቻሉን ጠቅሰው፣ በዚህ ስራም የእሳቸው ሚና የጎላ ነው ብለው እንደሚያስቡ ተናግረዋል።

ድርጅታቸው ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት በኩልም እየሰራ መሆኑን ይጠቅሳሉ። ማንኛውም የግል ድርጅትም ሆነ ዜጋ ያስተማረውን ማህበረሰብ እና ሃገር መደገፍ አለበት ብለው በጽኑ እንደሚያምኑ አስታውቀው፣ ድርጅታቸው ለበርካታ ሥራ አጥ ወጣቶች የስራ እድል ከመፍጠር በዘለለ በአካባቢው ያሉ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የተለያዩ ነዋሪዎችን በመርዳት ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

**ድርጅቱን ከአባታቸው ሲረከቡ ስምንት ያህል ሰራተኞች ብቻ ነበሩት፤ እሳቸው ግን ከመላው ቤተሰባቸው ጋር በመሆን ተጨማሪ ድርጅቶችን ከፍተዋል። በእነዚህ ድርጅቶችም የቋሚና የጊዜያዊ ሰራተኞችን ብዛት ወደ 500 ማሳደግ፣ የድርጅቱን የተመዘገበ ካፒታል ደግሞ ከ10 ሚሊዮን ወደ 400 ሚሊዮን ብር ማድረስ ችለዋል**

በተለይም በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስተባባሪነት ለአቅመ ደካሞችና አነስተኛ ገቢ ላላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በተከናወነው የቤት ግንባታ መርሃ-ግብር ድርጅታቸው ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ አስተዋፅኦ ማድረጉን ጠቅሰዋል። ከዚያም ባሻገር ስራውን የሚመራው ኮሚቴ አካል ሆነው ግንባታው እውን እንዲሆንም ያደረጉትም አስተዋጽኦ ከፍተኛ ስለመሆኑንም አስታውቀዋል።

በሌላ በኩልም የሰሊጥ ምርትና ምርታማነት እንዲጎለብት፤ ሀገሪቱ ወደ ተለያዩ ሀገራት የምትልከውም ምርት በጥራትም ሆነ በመጠን እንዲያድግ ድርጅታቸው ቋሚ የሆነ የድጋፍ መርሃግብር እንዳለው ዶክተር ሙሉጌታ ይናገራሉ። በዋናነትም በኮንትራት እርሻ ለተሰማሩ የተወሰኑ ገበሬዎች ድጋፍ እየሰጠ መሆኑን ጠቅሰው፣ ‹‹የፋይናንስም ሆነ የምርት ግብዓት በማቅረብ አምራቾቹ ምርታማነታቸውን እንዲያሳድጉ፤ ወደ ውጭ የሚላከውም ምርጥ ጥራቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የበኩላችንን ጥረት እያደረግን ነው›› ሲሉ ተናግረዋል።

ከዚህም ባሻገር ዘርፉን በመሰረታዊነት ማሳደግ ይገባል የሚል እምነት ያላቸው ዶክተር ሙሉጌታ፤ የኢትዮጵያ ሰሊጥ በዓለም ገበያ ተፈላጊ፣ የጥራትና የዋጋ መለኪያ ሆኖ እንዲቀጥል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅተው በመስራት ላይ እንደሚገኙም ይገልጻሉ። በዋናነትም እርሳቸው የቦርድ አባል በሆኑበት የኢትዮጵያ ጥራጥሬና ቅባት እህሎች ማህበር አማካኝነት ከምርምር ተቋማት እንዲሁም ከግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ጋር በመሆን ተደራሽነቱን ለማስፋት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል። ለዚህም ይረዳ ዘንዳ ከንግድ ሚኒስቴር እና ከሌሎችም መንግስታዊ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር ለዘርፉ መጎልበት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ ጥሬ ሰሊጥ ወይም እሴት ያልተጨመረበት ሰሊጥ ወደ ውጭ መላክ በማቆም እና እሴት ጨምራ በመላክ አሁን ከምታገኘው በላቀ የውጭ ምንዛሬ እንድታገኝ ማድረግ ይገባል የሚል ፅኑ እምነት አላቸው። በዚህ ረገድም በእሳቸው ፈርቀዳጅነት የተከፈተውን የሰሊጥ ቂቤ ማምረቻ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት እቅድ አላቸው። በተለይም አቅሙን በማጎልበት የሚያመርተውን ምርት በማስፋት የመዳረሻ ሀገራትን ቁጥር ለመጨመር እቅደው እየሰሩ መሆናቸው ይጠቁማሉ።

መንግስት የኢትዮጵያን ምርት ወደ ተለያዩ ሃገራት ለሚልኩም ሆነ በኢንዱስትሪ ልማት ለተሰማሩ ባለሃብቶች ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገ መሆኑንም መስክረው፣ ‹‹በተለይም ላኪዎች የሚያጋጥሟቸው ችግሮች እንዲፈቱ ከመንግስት ጋር በቅርበት ሆነን እየሰራን ነው›› ሲሉም አስታውቀዋል።

ዶክተር ሙሉጌታ ድርጅታቸው አሁን ከጀመረው የሰሊጥ ቂቤ (ታሂኒ) ምርት በተጨማሪ ወደፊት በሌሎችንም ምርቶች እሴት ጨምሮ በማምረት ወደተለያዩ ሃገራት የመላክ እቅድ አለው። ለዚህም ይረዳው ዘንድ በተለያዩ ዓለም አቀፍ አወደ ርዕዮች ላይ በመሳተፍ ተሞክሮ በመውሰድ፤ የኢትዮጵያን ምርቶች በማስተዋወቅ የደንበኞችን መጠን ለማሳደግ ከወዲሁ አልመው እየሰሩ ስለመሆናቸውም ተናግረዋል።

‹‹በአሁኑ ወቅት የታሂኒ ምርታችን አነስተኛ ነው፤ በገበያ ላይ ያለውን ፍላጎት የማሟላት ስራ ከሰራን በኋላ ሌላ ማስፋፊያ ስራ መስራት እንፈልጋለን፤ በዚህም 140 ለሚደርሱ ዜጎች ተጨማሪ የስራ እድል እንፈጥራለን ብለን እናስባለን›› የሚሉት ዶክተር ሙሉጌታ፤ ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ ወደ ሃገር ውስጥ የምታስገባቸውን ምርቶች በሃገር ውስጥ እንዲመረቱ ለማድረግ ፕሮጀክት ቀርፀው እየሰሩ መሆናቸውንም ያመለክታሉ።

‹‹እዚሁ ሃገር ቢያንስ በከፊል ያለቁ እቃዎችን በራሳችን የሰው ኃይል ገጣጥመን በማምረት ሀገሪቱ እነዚህን ምርቶች ለማስገባት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ለማስቀረት እቅድ ይዘን እየሰራን ነው›› በማለትም ያብራራሉ። በዚህም ትልቅ ኢንቨስትመንት ከ400 እስከ 500 የሚደርሱ ሰዎችን የስራ እድል ተጠቃሚ የማድረግ ፍላጎቱ አላቸው። በአሁኑ ወቅት እነዚህን ትላልቅ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች እውን ለማድረግ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለመግባት ከመንግስት ጋር ድርድር በማድረግ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል።

## ተናጋሪው ዶሴ

# በአዲስ ዓመት ዋዜማ ...

**ሰሚራ በርሀ**



አሰፋ አህመድ ሀሰን የ25 ዓመት ወጣት ነው። ትውልድ እና እድገቱ በአማራ ክልል ነው። ሕይወት በብዙ አጋጣሚ እና መንገድ ከትውልድ ቦታው ወጥቶ ወደ ሌላ አካባቢ መኖር እንዲጀምር አድርጎታል። በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ሕይወቱን ለመምራት እና ኑሮውን ለማቃናት ደፋ ቀና ማለቱን ቀጠለ።

አሰፋ ባለትዳር እና የአንድ ልጅ አባትም ጭምር ነው። በአዲስ አበባ ከተማ መኖር ከጀመረ ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ሰፈሮች ላይ አቅሙን የሚመጥን ቤት በመፈለግ ኖሯል። የቀን ሥራ ተቀጥሮ በመሥራት ጥበቃ ሆኖ ይሠራል። ሕይወትን በተለያየ መንገድ ለማሸነፍ የአባትነቱን እና የአባወራነቱን ያህል ይሯሯጣል።

አሰፋ በዚህ የከብት እርባታ ሥራ በሚከናወንበት አድራሻውን በየካ ክፍለ ከታ ወረዳ 12 በአንድ ጊቢ ውስጥ መሥራት ከጀመረ ሁለት ዓመት ያህል ጊዜ ሆኖታል። ከብቶች በጎች የሚገኙበት የቢኒያም ቡዙዬ የከብት እርባታ ድርጅት ውስጥ የሰው እንቅስቃሴም ሥራም የማይጠፋበት ነው።

ወይዘሮ አይናለም ማለዳ ከወፎች እኩል ተነስተው በድርጅቱ ውስጥ ላሞችን ማለብ የእለት ተእለት ሥራቸው ነው። ታዲያ የታለበውን ወተት ለተለያዩ በአካባቢው ለሚገኙ እና ራቅ ብለው በዚህ ሥራ ለሚሰማሩ አከፋፋዮች፣ ካፌዎች እንዲሁም በጠዋት የማከፋፈል ሥራ ይሠራል። ለከብቶቹ ምግብ በየሰዓቱ መስጠት እና በረታቸውን ማጽዳት ደግሞ የወጣት ከተማ ሥራ ነው። በመሆኑም ወጣቱ ጠዋት የታለቡትን ወተቶች ካደረሰ በኋላ ረፋድ ድረስ እና በቀኑ ማብቂያ ደግሞ እስከ አመሻሽ ያለውን ጊዜ በድርጅቱ ጊቢ ውስጥ ያሳልፋል።

ከተማ አበባው ገና የ22 ዓመት ወጣት ነው። ከትውልድ ከተማው ጎንደር የተሻለ ሥራ ፍለጋ ብሎ ከወጣ አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል። ታዲያ በእነዚህ አምስት ዓመታት ውስጥ ያልሠራው እና ያልሞከረው የሥራ ዓይነት የለም። በዚህ የቢኒያም የከብት እርባታ ድርጅት ውስጥ ሥራ ከጀመረ ገና ስድስት ወር ቢሆነው ነው። በድርጅቱ ውስጥ ለከብቶቹ ምግብ መስጠት እና ማጽዳት የእርሱ የሥራ ድርሻ ነው።

በድርጅቱ ውስጥ የማህበሩ አባላትን ጨምሮ ወደ 10 የሚጠጉ ሠራተኞች አሉ። አሰፋ በዚህ ድርጅት ውስጥ በጥበቃ ሥራ ነው የተቀጠረው። የሥራ ቦታ ሰዎች ወዳጅነትን ጉርብትናን የሚፈጥሩበት አንዱ ስፍራ ነው። በእለት ተእለት እንቅስቃሴ ውስጥም በሥራ ላይ የሚገኝ ሰው ቀርቶ እግርና እግርም ይጋጫል። አንድ ቀንም የሆነው ይህ ነው።

ወቅቱ የዓመቱ ማብቂያ የክረምቱ መደምደሚያ የነሐሴ ወር ነው። የአዲስ ዓመትን አስታኮ የሚፈካው አደይ አበባም ሆነ የመስከረም ወር ፀሐይ ከክረምት ጭጋግ በኋላ የሚናፈቁ ናቸው።

የነሐሴ ወር ከተጀመረ ሁለተኛውን ሳምንት ይዟል። ለወትሮው በቢንያም የከብት እርባታ ድርጅት ውስጥ ያሉ ሠራተኞች እስከ አንድ ሰዓት ድረስ ሥራቸውን ጨርሰው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ። ከተማ በጊቢው ውስጥ ከሁሉም ሠራተኞች መጨረሻ ላይ ነው የሚወጣው። አሰፋ በዚህ ቀን አዳሪ የጥበቃ ሠራተኛ በመሆኑ ከምሽቱ 12 ሰዓት ላይ እራቱን እና ለምሽቱ ብርድ የሚደርበውን ልብስ ይዞ ወደ ቢንያም ከብት እርባታ ድርጅት ሥራ ቦታው አመራ። የተወሰኑ ሠራተኞች ወተት ያደረሱበትን እቃ አስገብተው የሥራ ልብሳቸውን በመቀየር ላይ ናቸው።

### ያቺ ቀን

አየሩ ብርዳማ ነው። አልፎ አልፎ የሚጥለው ዝናብ የእለቱን አየር ቀዝቃዛማ አድርጎታል። አሰፋ ሁልጊዜ እንደሚያደርገው የጥበቃ ተራውን እንደተረከበ በጊቢ ካሉ ሠራተኞች ጋር ሰላምታ መለዋወጥ፣ ጊቢውን ተዘዋውሮ የመመልከት ልምድ አለው። ለዛሬ ግን ስሜቱ ጥሩ አይመስልም ቦታውን ተዘዋውሮ ከተመለከተ በኋላ በቦታው ላይ ቁጭ አለ። ወደ ድርጅቱ ከማምራቱ በፊት በአካባቢው በሚገኘው ግሮሰሪ ጎራ ብሎ ጥቂት ቀማምሷል።

ከተማ ሥራውን ጨርሶ የሥራ ልብሱን ቀይሮ ወደቤቱ ለማቅናት እየተጣደፈ ሲወጣ አሰፋ በበሩ ላይ ሲያስቆመው አስተዋለ። ለሰላምታ የመሰለው ወጣቱ ከተማ ንግግሩን ከአሰፋ ጋር ቀጠለ። ወደቤቱ ሊሄድ የነበረው ከተማ ግን ባሰበበት ሰዓት ወጥቶ መሄድ አልቻለም። በጊቢው ውስጥ ቁጣ የተቀላቀለበት ምልልስ፤ መደማመጥ የጎደለው ጭቅጭቅ በሁለቱ ሠራተኞች መሀከል ተፈጠረ። ብቅ ብሎ ምንድነው ያለ ግን አልነበረም፤ ድንገት ምልልሱ እየከረረ እና ከግቢው አልፎ መሰማት ሲጀምር ግን ወደቤታቸው ለመሄድ በመሰናዳት ላይ የነበሩት ሠራተኞች ትኩረታቸውን ወደ ሳበው የሥራ ባልደረቦቻቸው ጭቅጭቅ አመሩ።

ነገሩ ለገላጋይ የተመቸ አልነበረም። በአሰፋ እና በከተማ መሀል የነበረው ጭቅጭቅ ከሮ ከተማ ከጥበቃ ሠራተኛው አሰፋ በተሰነዘረበት ዱላ መሬት ወድቋል። በዚህ ጊዜ አካባቢው በጩኸት ታወከ፤ ከድርጅቱ ሠራተኞች ባለፈም የአካባቢው ሰዎች ወደ ድምጹን የሰሙበትን ጊቢ ሞሉት።

### የፖሊስ ምርመራ

ነሐሴ 9 ቀን 2015 ዓ.ም ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከ30 ላይ አሰፋ አህመድ ከተማ አበባውን የጸቡ መነሻ ባልታወቀ ምክንያት በተፈጠረ ግጭት በእንጨት ዱላ ጭንቅላቱን ብሎ በመምታት የራስ ቅሉ ላይ በደረሰበት ጉዳይ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል ለህክምና ተልኳል። ጭንቅላቱን ከተመታ በኋላ ለቀናት በህክምና ላይ የቆየው ከተማ ነሐሴ 15/2015 ዓ.ም በሆስፒታሉ ውስጥ በህክምና ላይ እያለ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል።

በቦታው የተፈጠረው ክስተት መረጃው የደረሰው የየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ፖሊስ ጥቃቱን ያደረሰውን አሰፋን በቁጥጥር ስር አዋለው።

ጥቃቱ የደረሰበት ወጣት ከተማ ሕይወቱ ማለፉን የሰማው የወረዳው ፖሊስ በእለቱ በቦታው የነበሩ ምስክር ቃል እና የጥቃት አድራሹን ቃል ከተቀበለ በኋላ፣ የአስክሬን ምርመራ በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ የፎረንሲክ ሜዲሲንና ቶክሲኮሎጂ ምርመራ ከላከ እና የሟች አስክሬን ገላጭ የፎቶግራፍ ማስረጃ ከምርመራ መዝገቡ ጋር እንዲያያዝ በማድረግ የድርጊቱ ፈጻሚ አሰፋ አህመድን በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የወንጀል መዝገብ ቁጥር 194/16 የፌዴራል አቃቢ ሕግ ክስ መሰረተ።

### የወንጀሉ ዝርዝር

ተከሳሽ አሰፋ አህመድ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ስር የተመለከተውን የሕግ ድንጋጌ በመተላለፍ ተከሳሽ ሰውን ለመግደል በማሰብ በቀን ዘጠኝ ነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም ምሽት በግምት አንድ ሰዓት ከ30 ላይ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ልዩ ቦታው ካራ ጋቢሳ በሚገኘው በአቶ ቢኒያም የከብት እርባታ ድርጅት ውስጥ የጸቡ መነሻ ባልታወቀ ምክንያት ሟች ከተማ አበባውን በእንጨት ዱላ ጭንቅላቱን ብሎ በመምታት በራስ ቅሉ ላይ በደረሰበት ጉዳት በህክምና ሲረዳ ቆይቶ በነሐሴ ወር ቀን 15 /2015 ዓ.ም ሕይወቱ ያለፈ በመሆኑ በፈጸመው የተራ ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል።

### ማስረጃዎች

በከሳሽ የፌዴራል ዓቃቢ ሕግ እና በተከሳሽ አሰፋ አህመድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ክርክር በተካሄደባቸው ጊዜያት የራሱን ማስረጃዎች ማሰባሰብ ቀጠለ። በቀን ዘጠኝ በጳጉሜን ወር 2015 ዓ.ም ተከሳሽ አሰፋ ፍርድ ቤት የቀረበ ሲሆን ዓቃቢ ሕግ የምስክሮችን ተጨማሪ ቃል ለማሰባሰብ ፣ የሟች አስክሬን ምርመራ ውጤት ባለመድረሱ፣ ከብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት የተጠየቀ የስልክ መረጃ ለማሰባሰብ ተጨማሪ የ14 ቀን የጊዜ ቀጠሮ እንዲሰጠው ጠየቀ። ፍርድ ቤቱ ዓቃቢ ሕግ መረጃውን አጠናክሮ ለማቅረብ የ10 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ፈቅዶ ለቀን ዘጠኝ መስከረም ወር 2016 ዓ.ም ፈቀደ ።

ዓቃቢ ሕግ በተሰጠው የጊዜ ቀጠሮ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒዬም ሜዲካል ኮሌጅ የፎረንሲክ ሜዲሲንና ቶክሲኮሎጂ ምርመራ በባለሙያ ተተንትኖ እንዲቀርብለት እና ገላጭ የፎቶግራፍ ማስረጃ ከምርመራ መዝገቡ ጋር አያይዞ ለማቅረብ ምርመራውን በሰውና በሰነድ ማስረጃ አጠናክሮ ውሳኔ እስኪሰጥ ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮን አቅርቦ መረጃዎቹን የማሰባሰብ ሥራውን ሰርቷል።

ወንጀሉ በተፈጸመበት እለት በቦታው የነበሩት የቢኒያም ከብት እርባታ ድርጅት ውስጥ የነበሩ የምስክሮችን ቃል ካጠናከረ በኋላ በአስክሬን ምርመራው ላይ የተላከው ውጤት እንደሚሳየው ተከሳሽ በጭንቅላቱ ከተመታ በኋላ በውጫዊ አካሉ ላይ እና በውስጣዊ አካሉ ላይ ባደረገው ምርመራ ስለታማ ባልሆነ ቁስ አካል በራስ ቅሉ ላይ በመመታቱ በአንጎሉ ላይ ጉዳት መድረሱን ለፍርድ ቤቱ ላከ። በተጨማሪም ዓቃቢ ሕግ በምርመራው ጥቃቱን የሚያስረዳ ሰባት ገላጭ የፎቶግራገፍ ማስረጃ አያይዞ አቅርቧል።

### ውሳኔ

ተከሳሽ አሰፋ አህመድ በተከሰሰበት ወንጀል በክርክር ላይ የነበረና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስና ማስረጃ ከሕግ ጋር አገናዝቦ በሰጠው ውሳኔ ተከሳሽ በሰባት ዓመት ከስምንት ወር ጽኑ እስራት ይቀጣ በሚል ውሳኔ አሳልፏል።

# የቀለም እንቦጭ

ሀብታሙ ባንታየሁ

የእንቦጭ አረም የጣናን ወዝ መጥምጦ በውስጡ የያዛቸውን ፍጥረታት ሕይወት ስጋት ላይ እንደጣለው ሁሉ፣ የቀለም እንቦጭም በትምህርት ሥርዓታችን የዘራው እንክርዳድ ለማህበራዊ መስተጋብራችን ተረፈና "በእውር በቅሎ ቃጭል ተጨምሮን" አስተረተብን። ሙሸት ያነሰው አዲስ ምጣድ እንጀራ እንደሚያኖኩረው ያለ "ቢጎርሱት ከአንጀት ጠብ የማይል፤ ቢጠጡት ጥም የማይቆርጥ፤ ቢለብሱት ከርዛት የማያስጥል ትውልድ በቀለ" እያሉ ከአጥቢያ እስከ ጀንበር መግቢያ የሚኮኑኑ ሰዎችን ስሰማ

**ውል አልባ ክስሽን ምነው ማቅለምሽ፤**

እንደው በደፈናው ስትቀቢ ከረምሽ።

ብሎ መዝፈን ይከጅለኛል። ስንኙ የተሳፈረበትን የሃሳብ ጀልባ ስንበረብር ከማን ምን አይተን ለማን ምን እናስተምር? የሚል ጥያቄን ቢጭርም የነገሩ ስር ወዲህ ነው። ሀገር በቀል እውቀቶቻችንን ኋላቀር ናቸው ብለን ልጅ ከማይደርስበት አርቀን ቀብረን ከርዳታ ጋር በተቀበልነውና በልካችን ባልተሰፋ ሥርዓተ ትምህርት ስንወላከፍ ጠልፎ ጣለንና የቀለም እንቦጩ በግላጭ ታየ።

"የጎባጣ አሽከር አጎንብሶ ይሄዳል" ነውና የትምህርት ሥርዓታችን ጉድፍ ለባህላችንና ለፖለቲካ ልምምዳችን የማይሽር ቁስል አውርሶት መላ እስኪጠፋን ድረስ ከንፈር ለሚያስነክስ ፀፀት ዳረገን። እናም ባልንጀሬ ... "ሁሉን ቢያወሩት ሆድ ባዶ ይቀራል" እንጂ ሀገራችን የተቃኘችበትን ሥርዓተ ትምህርትንስ "ላም እሳትን ወለደች" የሚለው አባባል የሚገልፀው ይመስለኛል።

እንዳንተወው ሀገር የምትቆምበት ምሰሶ ሆነ፣ እንዳንይዘው ማር በእሬት ተለውሶ ጎመዘዘን፤ የቸገረ ነገር... በዚህ ጉዳይ ዙሪያ በአንድ ወቅት ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ስለ ትምህርት ፖሊሲያችን የሰጠውን ምክረ ሃሳብ እማኝ መጥቀሱ ሚዛን ይደፋልና በሰላ ልቦና እንስፈረው። ከመንገድ ዳር ድንች የሚሸጡት ሴትዮ ርሃባቸውን ለማስታገስ የተሰለፉትን ተማሪዎች ሲያዩ እናታዊ ኀዘኔታቸው ከገፃቸው እየተነበበ "እንዳይፈጃችሁ ልጆች" አሉና ትኩሱን ድንች ለመጀመሪያው ልጅ ሲያቀብሉት እጁን አራግፎ ለሁለተኛው አሳለፈለት፤ እሱም ቢሆን ከእጁ ሳያቆይ ለሶስተኛው አሻገረለት። ትኩሱ ድንች እንዲህ እንዲህ እያለ ከመጨረሻው ተማሪ ቢደርስም ከሆድ አትግባ ብሎታልና ከመጀመሪያው ልጅ ዘንድ ዞሮ ተመለሰ።

ተማሪዎች ትኩሱን ድንች አብርደው ለመብላት አለመሞከራቸው ምሳሌነቱ ለእኛው ማህበረሰብ ነው። መንግሥት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በሚያደርገው ርብርብ ድጋፋችንን ከመስጠት ይልቅ እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ ማፈግፈጋችን ሳያንስ የትምህርት ሥርዓታችን ያለበትን ችግር እየነቀስን መተቸት እንጂ የበኩላችንን ሃላፊነት ስንወጣ አይስተዋልም። ከያዝነው ሥራ እንዳያናጥቡንና ሲያለቅሱ ለማባበል በሚል ሰበብ ስልካችንን በመስጠትና እድሜያቸውን የማይመጥን የቴሌቭዥን ዝግጅቶችን በማሳየት የልጆቻችንን ናላ የምናዞር ስንት ቤተሰቦች አለን? በመማር ማስተማሩ ሂደትስ ያሉበትን ደረጃ እንከታተል ይሆን?

ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ የኖርዌይ ተወላጅ ወዳጄ ያጫወተችኝን ሀገርና ትውልድ በቀና የትምህርት ሥርዓት የሚሰናሰሉበትን ብልሀት ማንሳቱ አግባብ አለው። ወዳጄ በአቅራቢያዋ ካለው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመቀጠር ባመለከተችጊዜመምህርነትንለምንእንደመረጠች ሲጠይቋት "ሁሉም ወላጆቼ መምህራን ስለሆኑ ፈለጋቸውን መልቀቅ አልሻም" ስትል የሰጠቻቸው መልስ አላጠገባቸውምና ህፃናትን ለማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ እንደሚያስፈልግ ነግረው አሰናበቷት። ተስፋ ሳትቆርጥ ጽናት ባጎለመሰው ሞራል ማስተርሷን ተማረችና ዳግመኛ ደጃቸውን ጠናች። አሁንም መልሷ ያው ነበር መምህር የመሆን ህልም! የትምህርት ቤቱ ባለቤቶች ግን እንደበፊቱ "ሾላ በድፍኑ" ብለው ሊያልፏት አልፈቀዱም። ይልቁንም ዝንተዓለም ከልቦናዋ የሚከተብ መልዕክት ነገሯት እንጂ።

"ህፃናትን ማስተማር ማለት በሚያልፍ ቀን የማያልፍ የትውልድ ስብራት እንዳይገጥማትና መሠረቱ በፀና አለት ገንብቶ ኖርዌይን ማስቀጠል ነው። እናም አንቺ መምህር የመሆን ፍላጎትሽ ላይ የሀገር ፍቅር አብሲት ጣይበትና ተመልሰሽ ነይ" ሲሉ ደራሽ ውሃ ያመጣውን ጊዜያዊ ስሜቷን አርቀው ሸኟት።

ሕዝቤ ሆይ አየህልኝ?... "ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ" እንደሚባለው የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፈለግን የትኩረት ክትትላችንን ከህፃናት መጀመር ይኖርብናል፤ አሊያ ግን "ሆድ ከጠገበ እግር ሞኝ ነውና" መድረሻውን አስቦ መነሻውን ያላበጀ የትምህርት ሥርዓት ሄዶ ሄዶ እንደ ህዳር አህያ ማንም ያሻውን የሚጭነው ትውልድ እንዲበቅል ምክንያት ይሆናል።

እርግጥ ነው የመጣንበት ሁነት እንደሚያስረዳው ነጋ ጠባ ጭንቀታችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን ናቸው። እውነት እናውራ ከተባለ የሚፈለገውን ያህል የትምህርት ጥራት ዩኒቨርሲቲዎቻችን ውስጥ አለ? ዩኒቨርሲቲዎቻችን ሀገር ተረካቢ ትውልድ እያፈሩ ናቸው?። የፎቶ ኮፒ ቤቶች ከመምህራን የፈተናውን ጥያቄ ገዝተው አዙረው ለተማሪ በውድ ዋጋ ሲሸጡ ያየሁበት አጋጣሚ አለ። የፈተና ጥያቄዎች ከአመት አመት ያው ናቸው። መምህራኑ አማካሪም ፈታኝም ሆነው ሳለ የተማሪውን የመመረቂያ ጹሁፍ ገንዘብ እየተቀበሉ የሚሠሩ መኖራቸው ያደባባይ ሀቅ ነው። ይህ ድርጊታቸው መንፈሱ የዛለና መምህርነት ባጣ ቆይ ሙያ እንደሆነ የሚያምን ትውልድ እንድናፈራ ያደረገው። የዚህን ዳፋ ገና በልጅነት ማለዳ ፊደል ስንቆጥር የማስታውሰውን ለፍርድ እንዲመች ላካፍላችሁ።

የድጎማ መምህራችን "ሀበል ፒዙ ለበል ፒዙ " እያለ ግራ ግራውን ሲያስተምረን የተመለከተው ርዕሰ መምህራችን እንደወረቀት በነጣ ብሩህ አዕምሮአችን ለምን እንክርዳድ እንደሚዘራ ቢጠይቀው "በ180 ብር ደመዎዝ እየኖርኩ በቀና ልብ ላስተምር አልችልም" አለ የቀነጨረ ትውልድ ለሀገር ውድቀት መንስኤ መሆኑ ግድ ሳይሰጠው። ታዲያ ከዚህ በላይ የቀለም እንቦጭ ምን አለ"?

## ዓለም አቀፍ

### ፑቲን በአዲሱ ባለስቲክ ሚሳኤል የዩክሬን ውሳኔ ሰጪ ማዕከላትን እንደሚመቱ አስጠነቀቁ

የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በዩክሬን መዲና ኪዬቭ የሚገኙ ውሳኔ ሰጪ ማዕከላት ላይ ኦሬሽኒክ በተሰኘው አዲሱ የሀገሪቱ የባለስቲክ ሚሳኤል እንደሚመቱ አስጠነቀቁ። ዩክሬን ከአሜሪካ የተለገሰችውን አታካምስ ሚሳኤል በመጠቀም ሩሲያ ላይ እየፈጸመችው ያለውን ተከታታይ ጥቃት ተከትሎ ፑቲን የተቀናጀ ነው ያሉትን አጸፋዊ ምላሽ መስጠት መጀመራቸውን ተናግረዋል።



ሩሲያ ከትናንት በስቲያ ሌሊት የዩክሬን የኃይል አቅርቦትን ከመታች በኋላ ነው ፕሬዚዳንት ፑቲን የሀገራቸውን አቋም የተናገሩት። የዩክሬን ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ ለማንኛውም የሩሲያ ጥቃት ከባድ ምላሽ እንደሚሰጥ አስጠንቅቀዋል። ባለፈው ሳምንት ዩክሬን ከአሜሪካው አታካምስ በተጨማሪ ከዩናይትድ ኪንግደም የተለገሳትን ሻዶው ሚሳኤልን የሩሲያ ግዛትን ዘልቃ እያስወነጨፈች ትገኛለች።

ምዕራባውያን አጋሮች የሩሲያን ምድር በእነዚህ ሚሳኤሎች እንድትመታ ፈቃድ መስጠታቸውን ተከትሎ ነው ዩክሬን እነዚህን ጥቃቶች እየፈጸመች ያለችው። ሩሲያ በአጸፋው በርካታ ሰዓታትን የፈጀ የድሮን እና የሚሳኤል ጥቃቶችን ፈጽማለች። በእነዚህ ጥቃቶች ሞት ባይከሰትም ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዩክሬን ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ውጪ ሆነዋል። ዘለንስኪ የሰላማዊ ሰዎች እና የሃይል መሠረተ ልማቱን ለመምታት የክላስተር አረሮች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ተናግረዋል።

"ክላስተር አረር ተሸካሚ መሣሪያዎች በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጥቃት የሚፈጸምባቸው በጣም አደገኛ የሩስያ የጦር መሣሪያ አይነት ነው" ብለዋል ዘለንስኪ።

ሩሲያ በፈጸመችው በዚህ ጥቃት ኦሬሽኒክን ጨምሮ 90 ሚሳኤሎች እና 100 ሰው አልባ አውሮፕላኖች መሳተፋቸውን ፕሬዚዳንት ፑቲን ተናግረዋል። እንደ ፑቲን ከሆነ ኦሬሽኒክ የተሰኘው የሩሲያ አዲሱ ባለስቲክ ሚሳኤልን ማክሸፍ አይቻልም። የአሜሪካ ባለሥልጣት ሩሲያ ጥቂት ቁጥር ያላቸው የሙከራ ኦሬሽኒክ ባለስቲክ ሚሳኤሎች ሊኖራት እንደሚችል የሚያምኑ ሲሆን በበርካታ ቁጥር ለማምረት ጊዜ ያስፈልጋታል ይላሉ።

ዘለንስኪ ፕሬዚዳንት ፑቲን "ጦርነቱን የማቆም ፍላጎት የላቸውም እንዲሁም ሌሎች ይህንን ጦርነት እንዳያቆሙ መከላከል ይፈልጋል" ሲሉ ተናግረዋል።"ጦርነቱን ማባባሱ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት የሩሲያን አቋም እንድትቀበል ጫና ለማድረግ የታለመ ነው" ብለዋል።

ፕሬዚዳንት ፑቲን በበኩላቸው ዩክሬን የኒውክሌር መሣሪያዎችን እንድታገኝ ሀገራቸው እንደማትፈቅድ ገልጸዋል። መሣሪያዎቹን ካገኘች ሩሲያ ማንኛውንም መሣሪያዎች ትጠቀማለች ማለታቸውን የሩሲያው መንግሥታዊ ሚዲያ አርአይኤ ዘግቧል። ባለፈው ሳምንት ስማቸው ያልተጠቀሰ ምዕራባውያን ባለሥልጣናት ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከሥልጣን ከመልቀቃቸው ከጥር ወር በፊት ለዩክሬን የኒውክሌር መሣሪያ እንዲሰጡ ምክረ ሃሳብ አቅርበዋል መባሉን ቢቢሲ የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ዘገባን ጠቅሶ ዘግቧል።

### ቻድ ከፈረንሳይ ጋር ያላትን ወታደራዊ ስምምነት አቋረጠች

ቻድ ከፈረንሳይ ጋር ያላትን ወታደራዊ ስምምነት አቋረጠች። ፈረንሳይን ጨምሮ ከምዕራባዊያን ሀገራት ጋር ጥሩ ወዳጅነት የነበራት ቻድ ከፓሪስ ጋር የነበራትን ወታደራዊ ስምምነት አቋርጫለሁ ብላለች። የሀገሪቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በጉዳዩ ዙሪያ ባወጣው ማስታወቂያ ሉዓላዊነቴን በነጻነት ለማጣጣም ከፈረንሳይ ጋር የነበረውን ወታደራዊ ትብብሮች መቋረጣቸውን ገልጿል።

የቻድ አዲስ ውሳኔን ተከትሎ ፈረንሳይ በሀገሪቱ ያሰፈረቻቸውን ወታደሮች እንድታስወጣ ልትገደድ ትችላለች ተብሏል። ሌላኛዋ የፓሪስ ቁልፍ የአፍሪካ አጋር የሆነችው ሴኔጋል ፕሬዚዳንት ባሲሩ ፋዬ የፈረንሳይ ወታደሮች በሀገራቸው መስፈራቸው ተገቢ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

ሀገሪቱ በሴኔጋል 350 ወታደሮችን ያሰፈረች ሲሆን ፕሬዚዳንት ባሲሩ ፋዬ ፈረንሳይ ወታደሮቿ በሀገራቸው መስፈራቸውን ከመተቸታቸው ባለፈ እንዲወጡ ፍላጎት ይኑራቸው አይኑራቸው አልተጠቀሰም። ፈረንሳይ ከቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿ ጋር ያላት ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸረሸረ ሲሆን ከኒጀር፣ ቡርኪናፋሶ እና ማሊ ተገዳ እንድትወጣ መደረጉ አይዘነጋም።

የፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን መንግሥት በቻድ ውሳኔ ዙሪያ እስካሁን ያሉት ነገር የለም። ፈረንሳይ በአፍሪካ ባሰፈረቻቸው ወታደሮች እና በቀጣይ ሊኖራት ስለሚችለው ግንኙነት ዙሪያ አዲስ እቅድ በማውጣት ላይ እንደሆነች ተዘግቧል። የፈረንሳይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኖኤል ባሮት ከሰሞኑ የቻድ ጎረቤት በሆነችው ሱዳን ጉብኝት አድርገዋል።

ፈረንሳይ በቻድ፣ ጋቦን እና ኮትዲቯር በሚኖሯት ወታደሮች ዙሪያ አዲስ እቅድ ያወጣች ቢሆንም እስካሁን ዝርዝሩ ይፋ አልተደረገም ሲል አል ዐይን ዘግቧል።



ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ትርጉም ያለው ግንኙነት ለመገንባት

ዳግም ከበደ

ፈጣን በሆነው በ21ኛው ክፍለ ዘመን ትርጉም ያለው ግንኙነት መገንባት ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊ ነው። መልካም ግንኙነት ለሕይወታችን፣ ዓላማችን ግብ መምታት፣ ለደስታ እና አስፈላጊውን ድጋፍ ለማግኘት እድል ይሰጣል። በቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ትስስር፣ ከጓደኞች ጋር ያለው እምነት፣ ወይም ከሥራ ባልደረቦች ጋር የገነባነው ግንኙነት ማንነታችንን ይቀርጹታል። በተጨማሪ የሕይወት ውጣ ውረዶችን የምንፈታበት ብስል አዕምሮ እንድናዳብር ይረዳናል።

በእያንዳንዱ ትርጉም ያለው ግንኙነት ውስጥ ሶስት አስፈላጊ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ‹‹መተማመን›› ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ‹‹መግባባት›› ነው። የመጨረሻውና ሶስተኛው ቁልፍ የግንኙነት መሠረት ‹‹መከባበር›› ነው። እነዚህን ባሕርያት ማዳበር እና ግንኙነቶችን ማሳደግ ጊዜ፣ ትዕግስት እና ጥረት ይጠይቃል።

### መተማመን

መተማመን የማንኛውም ጠንካራ ግንኙነት መሠረት ነው። ሰዎች አንዳቸው በሌላኛቸው ላይ እምነትን ማግኘታቸው ደህንነት እንዲሰማቸው የሚፈቅድላቸው ቁልፍ የግንኙነት መሠረት ነው። እምነት ከሌለ ግንኙነቶቹ ደካማ ይሆናል። በርግጠኝነት በሁለቱ አካላት (በቤተሰቦች መካከል፣ በባለ ትዳሮችና በጓደኞች መካከል) በማይታወቅ ጥርጣሬ የተሞላ ግንኙነት ይፈጠራል። መተማመንን መገንባት የሚጀምረው ግንኙነት ለፈጠርንለት ወገን ታማኝነትን በማሳየት ነው። ሁልጊዜ እውነት መናገር አስቸጋሪ ቢሆንም ግንኙነቱን ግልጽነት የሰፈነበት ለመሆን በቂ ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ስህተት ከሰራህ ከመደበቅ ይልቅ አምኖ መቀበል ታማኝነትህን ያሳያል።

ቃል ኪዳኖችን መጠበቅ ሌላው የመተማመን አስፈላጊ አካል ነው። የኛ የምንላቸው ሰዎች የሆነ ነገር ሲፈጽሙ (በቤተሰብ ዝግጅት ላይ መገኘትም ሆነ ጓደኛን በጀመረው ፕሮጀክት ዙሪያ) አጋርነታችንን ማሳየት ከሆነ፤ ልንረዳቸው ቃል ከገባን ያንን መፈፀም በመካከላችን ያለውን መተማመን በእጅጉ ይገነባዋል። መተማመን የበለጠ የሚጠነክረው ወጥነት ያለው ባህሪና ድርጊትን በማሳየት ነው። በደስታም፣ በሀዘንም እንዲሁም በሁሉም አጋጣሚዎች ተመሳሳይ ባህሪን ማሳየት ዘላቂ ግንኙነት ለመፍጠር መሠረት ይጥላል። አንድ የሥራ ባልደረባህን ደጋግሞ ርዳታ ጠይቆህ ዛሬ ነገ እያልክ ቃልህን የማታከብር ከሆነ በርግጠኝነት በመካከላችሁ መተማመን ይሸረሸራል። በጊዜ ሂደት ተግባሮችህ የእሱን እምነት ስለሚሸረሽሩ በአንተ ላይ አመኔታን ለመጣል አስቸጋሪ ያደርግበታል። በአንጻሩ ደግሞ በአስቸጋሪ ጊዜያት ያለማቋረጥ የሚደግፍ ጓደኛ በታማኝነት ረገድ መልካም ስም ይገነባል።

### መግባባት

መግባባት ጠንካራ ግንኙነቶችን ለመፍጠር ከመተማመን እኩል አስፈላጊ ነው። ማውራት ብቻ ሳይሆን መደማመጥና መረዳትም ጭምር የመግባባት ቁልፍ መሠረቶች ናቸው። ብዙዎቹ አለመግባባቶች የሚፈጠሩት በመጥፎ ግንኙነት ወቅት ነው። ንቁ ሆኖ ማዳመጥ፣ ሌላው ሰው በሚናገረው ላይ ሙሉ በሙሉ ማተኮርና ሁኔታዎችን ለመገንዘብ መሞከር፣ በመረዳት ውስጥ የተፈጠሩትን ክፍተቶችን ለማስተካከል ይረዳል። ባላጋራችሁን ሳታቋርጡ ወይም በሚናገረው ጉዳይ ላይ ሳትፈርዱ ስታዳምጡ ያን ጊዜ የእነርሱም ሃሳብና ስሜታቸው አስፈላጊ መሆኑን ልትረዱ ትችላላችሁ።

አለመግባባትን ለመቅረፍና ወደ መግባባት ለማምጣት ሃሳብን የመግለጽ ችሎታም እንዲሁ አስፈላጊ ነው። ግልጽ የሆኑ ቃላትን መጠቀም ለትርጉም እንዳንጋለጥ ያደርገናል። ሃሳባችንን እና ስሜቶቻችንን ሌሎች ሊረዱት በሚችሉበት መንገድ መግለጽ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ‹‹ተናድጃለሁ›› ከማለት ይልቅ፣ ‹‹በሁኔታው መበሳጨት ቅር ተሰኝቻለሁ›› ብሎ ማስረዳት በግንኙነቱ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለማርገብ ይጠቅማል። ይህ ግልጽነት ግራ መጋባትን ይከላከላል እና ሌሎች በትክክል ምላሽ እንዲሰጡም ያስችላቸዋል። ትዕግስት የግንኙነት ቁልፍ ገጽታም ነው። ሁሉም ሰው በተመሳሳይ መንገድ ወይም ፍጥነት አይግባባም። ስለዚህ ለሰዎች ጊዜ መስጠት የጋራ መግባባትን ያመጣል።

> **ትጋትን፣ መረዳትን እና አብሮ ለማደግ ፈቃደኛነትን ይጠይቃል፡፡ መተማመንን፣ መግባባትን እና መከባበርን በማስቀደም ሕይወታችንን የሚያበለጽጉ ግንኙነቶችን መፍጠር እና የጊዜ ፈተናዎችን መቋቋም ቀዳሚው የሕይወት ልምዳችን ማድረግ ይገባናል**

### እርስ በእርስ መከባበር

እርስ በእርስ መከባበር ትርጉም ላለው ግንኙነት ሦስተኛውና ዋነኛው ምሰሶ ነው። ሌሎችን ማክበር ማለት አስተያየታቸውን፣ ድንበራቸውን እና ግላዊነታቸውን መገምገምና ያንን ፍላጎታቸውን ማክበር ማለት ነው። ሁለቱም ወገኖች በማንነታቸው ሲታዩ እና ሲመሰገኑ ግንኙነቶቹ ይበለጽጋሉ። ልዩነትን መቀበል ወሳኝ ነው፤ ምክንያቱም ሁሉም ሰዎች አንድ ዓይነት አይደሉም። ለምሳሌ፣ ጓደኛህ የማትጋራው የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያ ወይም እምነት ሊኖር ይችላል። ይህንን ምርጫዋን (ምርጫውን) ማክበር በግለሰብ ደረጃ በመካከላችሁ መከባበር መኖሩንና እንድምትቻቻሉ የሚያሳይ ቁልፍ አጋጣሚ ነው።

የአንድን ሰው ፍላጎቶች የሚጥሱ ድንበሮችን ማወቅ አሊያ ለራስ ማዘጋጀት እና ያንንም ማክበር ሊመጣ የሚችልን ቅራኔ ከወዲሁ ለመቅጨት ይረዳል። ለምሳሌ አንድ የቤተሰብ አባል በአስቸጋሪ ጊዜ ሆኖ ችግሩን በራሱ ለማጤን አሊያም ለመፍታት ግላዊነትን ከጠየቀ እርሱን ማክበር ያስፈልጋል። ከዚህ በተቃራኒው ሆኖ ወደ ዝርዝር ውስጥ መግባትና ማስጨነቅ ግንኙነትን ያበላሻል። የሚበጀው አማራጭ ወደማይፈልገው አቅጣጫ ከመግፋት ይልቅ ጥያቄውንና ያበጀውን ድንበር ማክበር ለዚያ ሰው እንደምናስብ እንዲሁም እንክብካቤ እንዳደረግንለት እንዲያስብ ያደርገዋል።

ሌላው የመከባበር ማሳያ፤ ቤተሰቦቻችን፣ የፍቅር አጋራችን፣ ጓደኞቻችን ላደረጉልን መልካም ነገር እውቅናን መስጠት አንዱ ነው። ‹‹አመሰግናለሁ›› ማለት ወይም የአንድን ሰው ጥረት እውቅና መስጠት ያሉ ትናንሽ የምስጋና ተግባራት ሰዎች የተከበሩ እንደሆኑ እንዲሰማቸው በማድረግ በጋራ ግንኙነቱ ረጅም ርቀት እንዲጓዝ ያደርገዋል።

ልክ እንደ ቤተሰባዊ ግንኙነት የምቆጥረው (የሚጠራ) ጓደኝነት በሕይወታችን ላይ ልዩ ቦታ የምንሰጠውና በጣም ጠቃሚ ከሆኑ ግንኙነቶች መካከል አንዱ ነው። ሆኖም ልክ እንደሌላው ማንኛውም ትስስር ጤናማ አድርገን ለማቆየት ጥረት ይፈልጋል። በተለይ በጋራ ጥራት ያለው ጊዜ ማሳለፍ፣ ለቡናና ሻይ መገናኘት፣ ማዕድ መጋራት፣ ወይም በቀላሉ በስልክ ማውራት ግንኙነቶችን ያጠናክራል። የልደት ቀኖች በጋራ በማክበር፣ በግል ስኬት የሚመጡ አጋጣሚዎችን ወይም ደግሞ የግል ስኬቶችን ለማሰብ፤ ለጓደኞችን ወይም ለቤተሰባዊ ግንኙነቱ በቂ ጊዜን መመደብ እርስ በእርስ መከባበራችንንና አንዳችን ለሌላኛችን ያለንን መልካምነት ያንፀባርቃል።

በአስቸጋሪ ጊዜያት ጓደኞቻችንን መደገፍ አስፈላጊ ነው። አንድ ጓደኛህ (ፍቅረኛህ አሊያም የቤተሰብህ አባል) አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲገባ ጆሮ መስጠቱ ወይም በፈተናው ወቅት ጊዜህን መስጠት ሁሉንም ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። በሌላ በኩል ቅናት እና ፉክክር ጓደኝነትን ሊጎዳ ይችላል። ለጓደኞቹህ፣ ለቤተሰብህ አባል ስኬት እውነተኛ ደስታ ሲሰማህ አዎንታዊ ግንኙነትን ይገነባል፤ ወዳጅህን ያበረታታል እና ግንኙነቱን ዘላቂ እንዲሆን ያጠናክራል።

ከሰው ልጆች ግንኙነት መካከል ምናልባት የቤተሰብ ግንኙነቶች መልካም እንዲሆን ለማድረግ እንደ ቀላል ይቆጠራል። ብዙ ኃይል እንደማይጠይቅም ይታሰባል። ልክ እንደ ሌሎቹ ግንኙነቶች ሁሉ በተመሳሳይ መልኩ የቤተሰብ ግንኙነት መንከባከብ ጠቃሚ ነው። ከቤተሰብ አባላት ጋር ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ ግንኙነቱን ለማጠናከር ይረዳል። እንደ ምግብ መጋራት፣ ጨዋታዎችን መጫወት ወይም በወጎች ውስጥ መሳተፍ ያሉ እንቅስቃሴዎች ሁሉንም ሰው የሚያቀራርቡ ትዝታዎችን ይፈጥራሉ። በቤተሰብ ውስጥም ግልጽ ግንኙነት አስፈላጊ ነው። አለመግባባቶችን በርጋታ መነጋገር እና የሌላውን አመለካከት መረዳት ግጭቶችን መፍታት እና ቂምን ለመከላከል ይረዳል።

ፍቅርን እና ምስጋናን መግለጽ የቤተሰብ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ሌላኛው መንገድ ነው። ለምሳሌ ባለቤትህን/ሽን ‹‹እወድሻለሁ/ሀለሁ›› ማለት አንዱ የግንኙነት ማጠናከሪያ መንገድ ነው። የቤት ውስጥ ሥራዎች ላይ መሳተፍ እንዲሁ መልካም ነው። ሌላው ከቤተሰብ አባላት ጋር ግንኙነትን የሚያጠናክረው ወንድም ወይም እህት እንደ መጠየቅ ያሉ ቀላል መንገዶችን መከተል ነው፤ ይህንን ማድረግ በመካከላችሁ መተሳሰብ መኖሩን ለማሳየት ይጠቅማል። ከቤተሰብ አባላት ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነት መፍጠር ትዕግስት ይጠይቃል፣ በተለይም የባህሪ ወይም የአመለካከት ልዩነቶች በሚፈጠሩበት ወቅት ነገሩ ይበልጥ ሊከብድ ይችላል። የጋራ ፍላጎቶች ወይም ግቦች መፈለግና ለዚያም በመተባበር መሥራት ችግሩን ያቃልለዋል ተብሎ ይታሰባል፤ በተለይ ክፍተቶች ለማጥበብ ይረዳል።

ግንኙነቶችን መገንባት እና ማቆየት በመጨረሻው ውጤቱ የሚክስ ቢሆንም፣ እዚያ ላይ ለመድረስ ግን መንገዱ ሊረዝም ተግዳሮቶችም ሊያጋጥመን ይችላል። ነገር ግን በምድር ላይ ማንኛውም ነገር ያለ ፈተናና ጥረት ሊመጣ እንደማይችል ልናውቅ ይገባል። አለመግባባት የሚጠበቅ ነው፤ በነገሮች ላይ ያለን የሃሳብና የፍላጎት መለያየት ውጥረት ሊፈጥር ይችላል። የቅርብ የምንለውን ግንኙነቶችን እንኳን ሊያበላሽ ይችላል። እነዚህን ተግዳሮቶች ለማሸነፍ ዋናው ነገር ፊት ለፊት በመነጋገር ለመፍታት መሞከር ነው። ስለ ችግሮች ቁጭ ብሎ መነጋገር፣ ውይይቶችን ማድረግ ሁለቱም ወገኖች ስሜታቸውን እንዲገልጹ እና የጋራ መፍትሔ እንዲፈልጉ ያስችላቸዋል። በአጋርህ ላይ ስህተት ስትሠራ ይቅርታ መጠየቅ፤ አንተንም የሚያስከፋ አጋጣሚ ሲፈጠር ይቅር ማለት መተማመንን ለመጠገን እና ወደፊት ለመራመድ ወሳኝ ርምጃ ነው።

በእያንዳንዱ ግንኙነት ውስጥ ጊዜን እና ጥረትን ማድረግ (ኢንቬስት) አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ የአትክልት ቦታ ስትንከባከበው እንዴት እንደሚያምር አስብ። ትኩረት ስትነፍገውና ስትተወው ደግሞ ምን ያህል እንደሚበላሽም አስተውል። ስለዚህ ግንኙነቶችህ እንዲያብቡ እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው ልትገነዘብ ይገባል። ሁሌም ከሰዎች ጋር የሚኖርህን ግንኙነት በመደበኛነት መፈተሸ ይኖርብሃል። አስደሳች ጊዜዎችን በጋራ ማክበር እና በአስቸጋሪ ጊዜያት እርስ በእርስ መረዳዳት ግንኙነቶችን ህያው እና ትርጉም ያለው እንደሚያደርጉት እወቅ። ፍፁም መሆን ባይቻልም ትክክለኛ እና እውነተኛ ለመሆን ጥረት ልታደርግ ይገባል። በሕይወትህ ውስጥ ላሉ ሰዎችና ባንተ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ምስጋናን ልታሳያቸው ይገባል። እነዚህ ከሰዎች ጋር ያለህን መልካም ግንኙነት አሊያም ትስስሮች የበለጠ ያጠናክሩታል።

ሳጠቃልልህ ትርጉም ያለው ግንኙነት በአንድ ጀምበር አይገነባም። ትጋትን፣ መረዳትን እና አብሮ ለማደግ ፈቃደኛነትን ይጠይቃል። መተማመንን፣ መግባባትን እና መከባበርን በማስቀደም ሕይወታችንን የሚያበለጽጉ ግንኙነቶችን መፍጠር እና የጊዜ ፈተናዎችን መቋቋም ቀዳሚው የሕይወት ልምዳችን ማድረግ ይገባናል። ጓደኛ፣ የቤተሰብ አባል ወይም የሥራ ባልደረባ፣ እነዚህን ግንኙነቶች ለመንከባከብ ጊዜ መውሰዱ ዘላቂ ደስታን እና ርካታን እንደሚያመጣለት አውቆ ከዛሬ ጀምሮ ይህንን የብልህ መንገድ ምርጫው ያድርግ። ሰላም!!

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመከላከያ ሠራዊታችን የሰላም ተልዕኮ ስኬታማነት ከሕዝባዊነቱ ይመነጫል!

ሀገራችን ስለ ሰላም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጨባጭ ዋጋ ከሚከፍሉ ጥቂት ሀገራት መካከል በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ነች። እ.አ.አ ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስከ ዛሬ በተለያዩ የሰላም ማስከበር ተልእኮዎች በመሳተፍ እና ውጤታማ ሥራዎችን በመሥራት ዓለም አቀፍ እውቅና አግኝታለች ።

በዓለማችን ሰላም እንዲሰፍን ከሊግ ኦፍ ኔሽን ጀምሮ በሰላም ማስከበር ተልዕኮ ውስጥ በመሳተፍ ብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር ነች። በዚህም በብዙ የሰላም እጦት ውስጥ ለነበሩ የዓለም ሕዝቦች የሰላም ግንባታ አቅም ሆናለች። ዘላቂነት ላለው መረጋጋት ብዙ ዋጋ ከፍላለች።

ከኮሪያ ልሣነ ምድር የሚጀምረው የሀገሪቱ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ፣ በአፍሪካ በኮንጎ፣ በላይቤሪያ፣ በሱዳን፣ በደቡብ ሱዳን፣ በኮትዲቯር፣ በብሩንዲ፣ በሩዋንዳና ከሶማሊያ ቀጥሎ አሁን ላይ ደርሷል። በዚህም በግጭት ውስጥ ለነበሩ እና ላሉ የአፍሪካ ሀገራት የእፎይታ ምንጭ ሆናለች።

የሀገሪቱ ሠራዊት በተሰማራበት የሰላም ማስከበር ተልዕኮ ከፍ ባለ ወታደራዊ ዲሲፕሊን የተሰጠውን ግዳጅ በስኬት በማጠናቀቅ የሚታወቅ ፣በሰላም እጦት የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የተዘበራረቀባቸውን በግዳጅ አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦችን ህይወት በማረጋጋትም ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ነው ። ይህ ሕዝባዊ ባህሪው በሄደበት ሁሉ ስኬታማ እና ተመራጭ አድርጎታል።

በተለይም በአፍሪካ የሰላም ማስከበር ተልእኮዎች፣ የአፍሪካውያን ወንድሞቹን የሰላም ዕጦት ፣የሰላም እጦቱ የፈጠረውን ችግር በአግባቡ በመረዳት የተሰጠውን ተልዕኮ በአፍሪካዊ ወንድማዊነት መንፈስ በመከወን በብዙዎች ሕሊና ውስጥ ሊፋቅ የማይችል ወገናዊነት መፍጠር ችሏል፤ የግጭት ቀጣናዎችን በአጭር ጊዜ በማረጋጋትም ተጠቃሽ ሆኗል።

ሠራዊቱ ከፍ ያለ ጀግንነት እና የሕይወት መስዋእትነት በሚጠይቁ የሰላም ማስከበር ተልእኮዎች ፣ ግዳጆችን በልበ ሙሉነት በመፈጸም ዓለም አቀፍ እውቅና የተቸረው ነው። ለገዛ ህይወቱ ሳይሰስት ለተልእኮው ያለውን ታማኝነት በተጨባጭ የሕይወት መስዋእትነት በመሆን ችሏል።

በተለይም በጎረቤት ሶማሊያ አልሸባብ እና ሌሎች ጽንፈኛ ኃይሎች ከቁጥጥር ውጪ ሆነው ለአካባቢው ፤ከዚያም አልፎ ለዓለም ስጋት በሆኑበት ወቅት ፤ወንድም የሆነውን የሶማሊያ ሕዝብ ከእነዚህ ኃይሎች ለመታደግ ከፍ ባለ ወታደራዊ ብቃት እና ጀግንነት በመንቀሳቀስ አኩሪ ታሪክ ፈጽመዋል። በዚህም ከሶማሊያ ሕዝብ ለዘላለም የሚታወስ ከፍተኛ ከበሬታ አትርፎለታል።

አስቸጋሪ የሰላም ማስከበር ተልእኮዎችን በስኬት የመፈጸም ብቃቱ ሕዝባዊ ከሆነው ባህሪው ጋር ተዳምሮ የሶማሊያ ሕዝብ የሰላም አየር እንዲተነፍስ ፣ የእለት ተእለት ህይወቱን አንጻራዊ በሆነ ሰላም ውስጥ እንዲመራ ትልቅ አቅም ሆኖት ቆይቷል። የክፉ ቀን ወዳጅ በመባልም በሕዝቡ ዘንድ እውቅና አግኝቷል። ዛሬ አንዳንድ የሶማሊያ ባለስልጣኖች የኢትዮጵያን ውለታ ለማንኳሰስ ቢሞከርም የሶማሊያ ሕዝብ አስተዋይ ነውና ያተረፈላቸው ትዝብት ብቻ ሆኗል።

በቀጣይ በሶማሊያ ሊከናወን በታቀደው የሰላም ማስከበር ተልእኮዎች ውስጥ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት መሳተፍ ወሳኝ ስለመሆኑ፤ያለ ኢትዮጵያ ተሳትፎ ተልዕኮው ውጤታማ መሆን እንደማይችል የአብዛኞቹ እምነት የሆነውም ከዚህ ከሠራዊቱ ተልዕኮ የመፈጸም ብቃት እና ሕዝባዊነት የመነጨ ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ።

ሰሞኑን የመከላከያ ሠራዊቱ በደቡብ ሱዳን የሰላም ማስከበር ተልእኮ ግዳጁን በላቀ ብቃት እየተወጣ ስለመሆኑ በተባበሩት መንግሥታት በኩል እውቅና ማግኘቱም፤ ከዚሁ ወታደራዊ ብቃቱ እና ሕዝባዊነቱ የመነጨ ነው። እውቅናው ከዚህም ባለፈ ለአፍሪካውያን ወንድሞቹ ዘላቂ ሰላም መስፈን ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

ይህ የሠራዊቱ የጀግንነት እና ሕዝባዊ ባህሪ በአጋጣሚ የተፈጠረ ሳይሆን፤በኮሪያ ልሳነ ምድር የሰላም ማስከበር ተልእኮ ተጀምሮ እስከዛሬ የዘለቀ፣በተለያዩ ሀገራት በተሳተፉባቸው የሰላም ማስከበር ተልእኮዎች በተጨባጭ የታየ ፣ በሀገራቱ ሕዝቦች ምስክርነት የተረጋገጠ የአደባባይ ምስጢር ነው!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## አዲስ አበባን እንደ ስሟ ይሏል እንዲህ ነው!

ትንሳኤ አበራ

«መልካም ስም ከመልካም ሽቶ ይበልጣል» እንዲሉ አበው ስም ከተግባር እንዲጣመርባት የተደረገችውን የአሁኗን አዲስ አበባ መጥቀስ ይገባል። አዲስ አበባን ልክ እንደ ስሟ ውብና አበባ ለማድረግ ታስቦ እየተከናወነ ባለው የኮሪደር ልማት በእርግጥም ስምን ከተግባር ማገጣጠም ተችሏል።

አዲስ አበባ ከተማ እንደ ስሟ ሳትሆን ዘመናትን ስለማስቆጠሯ ነዋሪዎቿ ብቻ ሳይሆኑ እንግዶቿም የሚናገሩት ሀቅ ነው። የከተማዋ ውበት ስሟ ላይ ብቻ የቀረ ስለመሆኑ እኛም አሳምረን እናውቃለን። ከተማዋ ጥቂት ጥሩዎች አልነበሯትም ማለት አይቻልም፤ አሏት፤ ይሁንና በመጥፎቿ በመሸፈናቸው መገለጫዋ ጉድለቷ ሆኖ ኖሯል። አብዛኛው የከተማዋ ክፍል ስሟን፤ የሀገሪቱ፣ የአፍሪካ ህብረት፣ የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ከተማነቷን ጨርሶ የማይመጥን ሆኖ ቆይቷል።

ከተማዋ እንደ አፍሪካ ህብረት አይነት ጉባዔዎችን ለማካሄድ ስትዘጋጅ ጎዳናዎቿ ሲጸዱ፣ ህንጻዎቿ ቀለም ሲቀቡ፣ መብራቶች ሲገጠሙላት፣ መንገዶች ሲጠገኑ፣ ዛፎችና አበቦች ሲተከሉ ዓመታት አልፈዋል። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ለሰሞን ካልሆነ በቀር ከተማዋን እንደ ስሟ አበባ ማድረግ አልቻሉም።

ለእዚህም ነው ከተማዋን እንደ ስሟ አበባ ለማስመሰል መንግሥት ቁርጠኛ አቋም ይዞ ወደ መሥራት የገባው። በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አሕመድ ዶ/ር አነሳሽነትና በከተማዋ አስተዳደር ያላሰለሰ ጥረት ይህን ውጥን መሬት ላይ ለማውረድ ባለፉት ወራት በኮሪደር ልማቱ ከፍተኛ ርብርብ ተደርጓል።

ይህን ተከትሎም ከተማዋ ዛሬ ከስሟ ጋር ሊጣፃም የሚችል ልማት ማየት ጀምራለች። ከተማዋ ሰፊ ከመሆኗ አኳያ ገና ብዙ መሰራት ያለባት ቢሆንም፣ የኮሪደር ልማቱ በተከናወነባቸው በርካታ ሥፍራዎች የታየው ለውጥ ከተማዋን እንደ ስሟ ውብ ማድረግ መጀመሩን በሚገባ አመላክተዋል። ለውጥ ስትናፍቅና ስትሻ የኖረችው ጥንታዊቷ ከተማ አዲስ አበባ እየተዋበች ፣ እያማረችና እያበበች ያለችበት ሁኔታ ይህን ይጠቁማል።

ከተማዋ ዘመኑን የዋጀች እንድትመስል ለማድረግ ሰፋፊ ሥራዎች ተከናውነዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛሉ። በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ ነዋሪዎቿን ወደ አዳዲስ መንደሮች ማዛወር ላይ በስፋት እየተሠራ ነው። በዚህ አይነት መንገድ የተለቀቁ ቦታዎችን ለመንገድና ለመሳሰሉት መሠረተ ልማቶች በማዋል ከተማዋን ባለሰፋፊ ደረጃቸውንም የጠበቁ የተሽከርካሪና የእግረኞች መንገድ ባለቤት ማድረግ ተችሏል።

የአካል ጉዳተኞች፣ የሞተር አልባ ተሽከርካሪዎች መንገዶችም ተካተውባቸዋል። ሰፋፊ አረንጓዴ ሥፍራዎች፣ መዝናኛዎች፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ ፋውንቴኖች፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች፣ የታክሲና አውቶብስ ተርሚናሎች ተገንብተዋል።

የስልክ፣ የኤሌክትሪክ፣ የፍሳሽ ቆሻሻና የመጸዳጃ ቤት ፍሳሽ መስመሮች ከመዝረክረክ ወጥተው ከምድር በታች በስርአቱ እንዲዘረጉ መደረጉ፣ የድህንነት ካሜሪዎች ተገጥመዋል፤ የመሬት ውስጥ የእግረኞች ማቋረጫዎች፣ ወዘተ ተገንብተዋል።

«አይን አይቶ ልብ ይፈርዳል» እንዲሉ አበው አዲስ አበባ ከተማ በእርግጥም እንድትለወጥ እንድታሸበርቅ ተደርጋለች። አምራም፣ ተለውጣም፣ አሸብርቃም በአይናችንን በብረቱ ተመልክተናል፤ ለእዚህ የአይን ምስክሮች ነን። ባማረው ባሸበረቀው የከተማዋ ክፍል እየገባን እየወጣን ልማቱን ማጣጣም ከጀመርን የቆየንም ነን። አዲስ አበባን እንደ ስሟ ይሏል እንዲህ ነው!

ለውጡን አይቶና ተመልክቶ ሳያደንቁ ማለፍ ተገቢ አይደለም፤ የውጭ ዜጎችን ጨምሮ መላው ህብረተሰብ የመሰከረለትን ይህን ታላቅ ተግባር አለማድነቅ ተገቢ አይደለም፤ የአዲስ አበባን አዲስ መሆን መጀመር አድንቀናል። አዲስ አበባ ሰፊ፣ ችግሮቿም እጅግ ውስብስብ እንደመሆናቸው የተጀመረው ከተማዋን ውብና ለነዋሪዎቿ፣ ለጎብኚዎቿና እንግዶቿ ምቹ የማድረጉ ሥራ በሁለተኛው ምእራፍ የኮሪደር ልማት ተጠናክሮ እንዲቀጥልም ተመኝተናል።

የኮሪደር ልማቱ ከተካሄደባቸው ጎዳናዎች አብዛኞቹ ሕዝብ በብዛት የሚንቀሳቀስባቸው እንደመሆናቸው በባለጉዳዮች፣ በባለአሽከርካሪዎች ብቻ የሚታወቁ አይደሉም፤ ለጤና ብለውም ይሁን ለሌላ ጉዳይ የእግር ጉዞ በሚያደርጉም በሚገባ የሚታወቁ ገዝፈው የሚታዩ ሀውልቶች ሊባሉ የሚችሉ ናቸው።

አሁን አዲስ አበባ እንዲህ ተውባና ደምቃ መታየት ጀመረች እንጂ የቀድሞ ገጽታዋ የአፍሪካ ህብረት ዋና መዲናና የዲፕሎማቶች መቀመጫ ለሆነችው አዲስ አበባ ፍጹም የማይመጥንና ከዘመኑ ጋር አብሮ የማይሄድ ነበር። የጽዳት ጉድለትን በመጥቀስ በተደጋጋሚ ሲያስወቅሷት አልፎም ተርፎ ይህን የአፍሪካ ህብረት መዲናነቷን ሊቀሟት የዳዳቸው እንደነነበሩም ይታወሳል።

በወቅቱ በተደረጉ የዲፕሎማሲ ሥራዎች ከተማዋ የአፍሪካ ህብረት ዋና ከተማ ለመሆን በቅታለች። ይህን እውነታ በመረዳት በከተማዋ ላይ ለውጥ ለማምጣት በቀደሙት አመታት የከተማዋን መሠረተ ልማት፣ ጽዳትና ውበት የተመለከቱ ሥራዎች ቢካሄዱም፣ መሰረታዊ ለውጥ ያመጡ ግን አልነበሩም።

ከለውጡ በኋላ በተለይ ካለፈው ዓመት ጀምሮ ከተማዋን ለማደስና ለማዘመን የሚያስችልና ማስቻልም የጀመረ የኮሪደር ልማት ሥራ ውስጥ በሰፊው ተገብቷል። ልማቱ በምዕራፍ ተከፋፍሎ እየተከናወነ ከመሆኑም በላይ የከተማዋን ገጽታ መቀየር ያስቻለ ሥራ ተሰርቶበታል፤ እየተሠራበትም ነው። በተጠናቀቀው የመጀመሪያው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራ ከፍ ሲል የጠቀስኳቸውን ስኬቶች ማጣጣም ተችሏል፤ የሁለተኛው ምዕራፍ ሥራም በፍጥነት እየተከናወነ ይገኛል።

ይህ ስኬታማ ተግባር በዜጎች፣ በከተማ ልማት ባለሙያዎች፣ በዲፕሎማቶች፣ ወዘተ አድናቆት እየተቸረው ሲሆን፣ አድናቆቱ ከሀገር ውጭ ጭምር እየመጣ ነው። በቅርቡም የአዲስ አበባ ከተማ የአፍሪካ ስማርት ከተሞች አዋርድ ተሸላሚ የሆነችበት ሁኔታም ይህንን ያመለክታል። ከተማዋ ከሌሎች ስማርት የአፍሪካ ከተሞች ጋር ተወዳድራ ነው ተሸላሚ ለመሆን የበቃችው።

ለከተማዋ ይህ ሽልማት ሊሰጥ ከቻለባቸው ዋንኛዎቹ ምክንያቶች መካከል በኮሪደር ልማት ለነዋሪዎቿ ምቹ እና ተስማሚ ከተማ መልሳ ለመገንባት ያከናወነችው ሥራና የተገኘው አመርቂ ውጤት አንዱ መሆኑ ተጠቁሟል፤ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር የአየር ለውጥ ተጽዕኖን ለመቀነስ እየተተገበረ ያለው ተምሳሌታዊ ተግባርም ሌላው ምክንያት መሆኑ ተመላክቷል።

በተመሳሳይ የአፍሪካ ሀገራት ከተሞችን የዕድገት ደረጃ የሚገልጸው ኢኮኖሚስት ኢንተለጀንስ ዩኒት የተሰኘው ድርጅት በ2024 ባወጣው ሪፖርትም እንዲሁ አዲስ አበባ ከተማን በፈጣን ዕድገት ላይ የምትገኝ ሲል ጠቅሷታል።

ይቺ በእድገት ጎዳና ላይ ያለች ከተማ የዓለምን ቀልብ እየሳበች በመሆኗ በርካታ አህጉርና ዓለም አቀፍ ሁነቶችን ለማስተናገድ እድሉ ተፈጥሮላታል። በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ብቻ ከ30 በላይ አህጉርና ዓለም አቀፍ ሁነቶች በብቃት ማስተናገድ ችላለች። በዚህም ብዙ ሁነቶች የማስተናገድ አቅምና ብቃት እንዳላት እያስመሰከረች ትገኛለች። ከወራት በኋላም እንዲሁ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔን በተሻለ ሁኔታ ለማስተናገድ እየተዘጋጀች ስለመሆኗ መረጃዎች ያመላክታሉ።

ከተማዋ ከሌሎች ከተሞች ይልቅ እነዚህን አህጉርና ዓለም አቀፍ ሁነቶች እንድታስተናግድ የተመረጠችባቸው ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም፣ የከተማዋን ገጽታ ለመቀየር እየተከናወኑ የሚገኙ ተግባሮችና እነሱን ተከትሎ የታዩ ለውጦች ናቸው። በቀጣይም ከተማዋን የቱሪዝምና የኮንፈረንስ ማዕከል ለማድረግ የተጀመረውን ሥራ አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል። በተለይ ኢትዮጵያዊ ጨዋነትንና እንግዳ ተቀባይነታችንን አጉልተን በማሳየት፣ የቱሪዝም መስህቦቿ እንዲተዋወቁ ማድረግ ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል።

ከተማዋ ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅባታል፤ ይህ በእንዲህ እንዳለም የተሠሩትንና እየተሠሩ ያሉትን ውጤቶች አስጠብቆ ማስቀጠል ሌላው ሥራ ሊሆን ይገባል። ይህ እንዲሆን የሚመለከታቸው አካላት ቀጣዩን ሥራቸውን ማወቅና መሥራት ይኖርባቸዋል።

በከተማዋ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት የተጀመረው በኮርደር ልማቱ ስለመሆኑ የተከናወኑ ተግባሮች ይናገራሉ። ከተሞች ዘመናዊነትን መላበስ ባለባቸው በዚህ ወቅት ከተማ ማደስ ብቻ በቂ ላይሆን ይችላል፤ በርካታ ከተሞች ዘመኑን የዋጀ አዲስ ከተማ እስከመገንባት ደርሰዋል። የኢትዮጵያ መንግሥትን በጫካ ፕሮጀክት ስማርት ከተማ እየገነባ መሆኑ ይታወቃል። ይህን ሲያደርግ ግን አብዛኛው ሕዝብ ያለባትን ከተማ ወደ ጎን መተው አልፈለገም። አብዛኛው ሕዝብ የሚኖርባቸውን የከተማዋን ክፍሎች ማደሱን በስፋት ተያይዞታል።

በመልሶ ልማቱ መሠረተ ልማት ብቻ ሳይሆን የለማው ሰውም ጭምር ነው። በደካከሙ ቤቶች ይኖሩ የነበሩ የከተማዋን ነዋሪዎች በዘመናዊ ቤቶች መኖር የሚያስችላቸውን ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል። ልማቱ ሰው ተኮር የተባለውም ለእዚህ ነው።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካሳቸው ቀንሰው የሴሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ከነገ ማዶ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

### ከዓመታት በፊት...

ወይዘሮዋ ነፍሰጡር መሆኗን አውቃለች። ይህ እውነት ለውስጧ ደስታን አቀብሏል። ነገ ስለምትወልደው ልጅ እያሰበች ነው። ሁሌም እንደ እናት መሆን የሚገባትን ታልማለች። የልጇ መልካም እድገት፣ የወደፊት ሕይወት ውል ይላታል። ይሄኔ ፊቷ ይፈካል፣ ውስጧ ይፍታታል።

እሷ ማርገዟን ካወቀች ወዲህ ስለራሷ ያላት ግምት ተቀይሯል። ዘወትር ታስባለች። ነገ ልጇን ወልዳ ስታቅፍ የሚያስፈልጋትን አታጣውም። ይህ እንዲሰምር ጤናዋን ትጠብቃለች፣ ጆሮዋ ሁሌም ለሌሎች ምክር ክፍት ነው። መልካም ሃሳቦች ይስቧታል። ውስጧ ነገን ሲያስብ አርቆ ያልማል። ነገ ለእሷ መልከ ብዙ ነው።

### ሶስት ጉልቻ...

ጥንዶቹ በአንድ ጣራ ስር መኖር ከጀመሩ ቆይተዋል። እስከዛሬ «አንተ ትብስ አንቺ» ይሉት እውነት በእነርሱ እውን ሆኗል። ለትዳራቸው ይተሳሰባሉ። አባወራው ከውጭ ሰርቶ ይገባል፣ ወይዘሮዋ የጓዳዋን፣ የቤቷን ጎዶሎ ትሞላለች። አሁን ደግሞ ፍሬ ሊያዩ በልጅ ሲሳይ ሊባረኩ ነው። ሁለቱም ደስ ብሏቸዋል።

ጊዚያት እየተቆጠሩ ነው። ጥንዶቹ ስለቤታቸው ድርሻቸውን አልዘነጉም። ዛሬን አልፈው ነገ ላይ ሲቆሙ የሚያሻቸውን ያውቃሉ። ነገ እንደትናንት አይደለም። ቤተሰብ ሲጨምር ቀዳዳው ይበዛል። መሸቶ በነጋ ቁጥር ኃላፊነቱ ይከብዳል።

ሙሉ ላቃቸው የሕይወት አጋጣሚ ከጎኗም አዲስ አበባ ካመጣት ወዲህ ኑሮዋ «ፉሪ» ከሚባለው ሰፈር ሆኗል። አካባቢው ለእሷና ለባለቤቷ መልካም የሚባል ነው። በእነሱ መንደር ጉርብትና ትርጉም አለው። ሁሉም ተግባብቶ፣ ተስማምቶ ያድራል። በክፉ ቀናት ፈጥኖ ደራሹ፣ ዕንባ አባሹ ይበረክታል። ደስታ ባጋጠመ ጊዜ ስሜቱ የጋራ፣ ሆኖ ይከርማል።

አሁን የወይዘሮዋ መውለጃ ቀን ቀርቧል። ለቤቷ ፣ ለእንግዶቿ ፣ ለአራስ ጎኗ የአቅሟን አዘጋጅታለች። ከዚያ በፊት ግን ተጨማሪ ምርመራዎች ይቀሯታል። ቀጠሮዋን አስታውሳ ቀኑን አንድ ሁለት ብላ ቆጠረች። ጣቶቿ ዕለቱን አላዛቡም። በትክክል ከቀጠሮ ቀኗ አደረሷት።

አንድ ማለዳ እንደ ልምዷ ራሷን አዘጋጀች። የቀጠሮ ቀኗ ነበር። አላረፈደችም። በሰዓቱ ከጤና ጣቢያው ደርሳ ተራ እስኪደርሳት ተቀመጠች። ከጎኗ ያሉ እናቶች እርስ በርስ ያወጋሉ። ስለራሳቸው፣ ስለባሎቻቸውና ስለሌላም። ሁሌም የዚህ ቦታ ጨዋታ ተመሳሳይ ነው። ከእሷ የሚቀድሙ ምርመራቸውን አጠናቀው እየወጡ ነው። ሙሉ ስሟ እስኪጠራ ጆሮዋን ጥላ አዳመጠች።

አሁን ተራዋ ደርሶ ወደ ውስጥ ዘልቃለች። በየወሩ ሐኪም ባገኛት ቁጥር ከፊቷ እፎይታ ይነበባል። የነርሶቹ፣ የሐኪሞቹ ፈገግታ ፈገግታዋ ነው። ዕለቱን ግን ከምርመራዋ በኋላ ያየችው ገጽታ ፈጽሞ አላማራትም። ሐኪሙ በእጁ የደረሰውን ውጤት አተኩሮ እያየ ነው። ውስጡ ጥሩ አልመስል ቢላት መጨነቅ ያዘች።

ጥቂት ቆይቶ ሐኪሟ እውነታውን ገለጸላት። በሆዷ ያለው ጽንስ ችግር እንዳለበት ባሳወቃት ጊዜ በድንጋጤ ክው አለች። ሐኪሙ የምርመራውን ሐቅ አንድ በአንድ ለማስረዳት አልዘገየም። ሙሉ ስለ እርግዝናዋ እክል እውነቱን ካወቀች በኋላ አማራጩ ወዲያው ቀርቦላታል።

በሕክምና ታግዛ ጽንሱን ማስወገድ እንደምትችል ሰምታለች። እሷ ግን ይህን አማራጭ «እሺ» ብላ ለመወሰን ልቦናዋ አልፈቀደም። ይህን ማድረግ በፈጣሪ ሥራ መግባትና እያወቁ ነፍስ ማጥፋት መሆኑን አምናለች። ልጇ በሕይወት ከተወለደ በይሁንታ ተቀብላ ለማሳደግ የወሰነችው ወዲያው ነበር።

ይህ የምርመራ እውነት በተለይ ለመጀመሪያ ጊዜ እናት ለምትሆን ሴት በእጅጉ ይከብዳል። ሙሉም ብትሆን ውስጧ ከዚህ ስሜት አልራቀም። እስከ ዛሬ «ወልጄ ጤነኛ ልጅ አቅፋለሁ፤ እስማለሁ» ስትል ቆይታለች። እስከ አሁን በነበራት ምርመራም ጽንሱ ችግር እንዳለበት አልተነገራትም።

ነፍሰ ጡሯ ወይዘሮ ቤቷ ስትመለስ እንደ ቀድሞው እፎይታ ከእሷ አልነበረም። በሆነባት፣ በተነገራት ጉዳይ ተጨንቃና ተከዛ ነበር። ሙሉ ባለቤቷ ወደ ቤት ሲመለስ ከሐኪሞች የሰማችውን እውነት አንድ በአንድ ነገረችው። አባወራው ይህን በአወቀ ጊዜ ድንጋጤ ወረረው።

### ከምክር በኋላ...

አሁን ባልና ሚስት ምክክር ይዘዋል። ይህ ጉዳይ የአንዳቸው ብቻ አይደለም። የጋራ ሕይወታቸውን፣ ቤት ትዳራቸውን ይቃኛል። ባል ሃሳቡ ልክ እንደሚስቱ ሆኗል። እግዜር በሰጣቸው ፍጡር ላይ «ይሙት በቃ»ን መወሰን አይሻም። ከፈጣሪ የተቸረን ስጦታ በምስጋና መቀበል ግድ ይላል።

ሚስት ሁሌም ባለቤቷን አክባሪ ናት። መቼም ከቃሉ አትወጣም። የሚላትን ትሰማለች። ለሃሳቡም ትገዛለች። ዛሬ ደግሞ ባሏ የእሷን ሃሳብ በጽኑ ደግፏል። ከጎኗ ሊቆም፣ «አይዞሽ፣ አለሁሽ» ሊላት ቃል ገብቷል። ጥንዶቹ ልጃቸው ምንም ይሁን ምን በሰላም ተቀብለው ሊያሳድጉት ወስነዋል።

እነሆ የመጨረሻው ቀን ነው። የተረገዘው ሊወለድ ጊዜው ደርሷል። እናት ሙሉ ከሆስፒታል ገብታለች። ሴት ልጅ መውለዷን ባየች ጊዜ ስለሚሆነው ሁሉ አልጨነቃትም። አስቀድማ ሁሉን አውቃለችና ራሷን አዘጋጅታ ልጇን በፈገግታ ተቀበለች። ከምንም በላይ ጸሎት ምስጋናዋን አልተወችም። ሁሉም የሆነው በፈጣሪ ፈቃድ መሆኑን አምናለች።

### ሕክምናው ...

ሙሉ የልጇ ሕክምና የጀመረው ውሎ ሳያድር ነበር። ለቀናት ከሆስፒታል አልጋ የከረመችው እናት እንደ ወጉ ወደቤቷ በክብር አልገባችም። ስለልጇ ጤንነትና በሕይወት መኖር ጊዜያትን ከፍላ በቆይታ አሳለፈች። የትንሽዋ ልጅ የጤና ችግር በእርግዝና ወቅት የሚያጋጥም የፎሊክ አሲድ እጥረት መሆኑ ተነግሯታል።

በአብዛኛው ይህ ዓይነቱ ችግር መኖሩ የሚታወቀው በእርግዝና የመጨረሻ ጊዜያት መሆኑ በጽንሱ ህልውና ላይ ለመወሰን የሚያስቸግር ይሆናል። ብዙ ጊዜ እንደ ሙሉ እውነታውን የሚያውቁ እናቶች በልጆቻቸው ሕይወት ላይ ለመወሰን ይቸገራሉ። ጥቂት የማይባሉትም ልጆቻቸው ወደ ምድር በሕይወት እንዲመጡ ይፈቅዳሉ። እንዲህ በሆነ ጊዜ ሕፃናቱ ከተወለዱ በኋላ በተገቢው ሕክምና እንዲታገዙ ማድረግ የግድ ይሆናል።

የነርቭ ዘንግ ክፍተት /ስፓይና ቢፊዳና ሀይድሮሴፋለስ/ ሕፃናት በእናታቸው ሆድ ሳሉ የሚከሰት የጤና ችግር ነው። በእርግዝና ወቅት ከሕፃኑ ጀርባ የመሀለኛው፣ የላይኛውና የታችኛው ክፍል፤ በጊዜው መዘጋት የነበረበት የሕፃኑ የራስ ቅልና የህብለሰረሰር ዘንግ ክፍተት ችግሩ እንዲከሰት ምክንያት ይሆናል። በጭንቅላት ውስጥ ከመጠን ያለፈ ፈሳሽ ሲኖርና ኢንፌክሽን ሲፈጠርም ይህ ችግር የሚያጋጥም ይሆናል።

ወደ ገጽ 17 ዞሯል

---

የአዲስ አበባ ሴቶች ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ
Addis Ababa Bureau of Women, Children & Social Affairs

## ከአዲስ አበባ ሴቶች ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጋር በመተባበር የየሳምንቱ የሚታተም

## ሴቶች ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት !

**ሶሎሞን በየነ**

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 1998 ዓ.ም ባካሔደው ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባው ላይ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የጸደቀበት ኅዳር 29፤ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ተብሎ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲከበር ወሰነ። ውሳኔው ኢትዮጵያዊያን ሕገ-መንግሥቱ ያስገኘላቸውን ጥቅሞች እንዲያስቧቸው፤ መብቶችና ነፃነቶቻቸውን ጠብቀው ማቆየት ብቻ ሳይሆን አንዱ የሌላውን ባሕል እንዲያውቅ እና እውቅና እንዲሰጥ ለማድረግ ነው።

ይህንን መሠረታዊ ዓላማ በማንገብ የመጀመሪያው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በ1999 ዓ.ም በፌዴሬሽን ምክር ቤት አዘጋጅነት "ሕገ-መንግሥታዊ ቃል ኪዳን የአብሮነታችን መገለጫ ነው" በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ መከበሩ ይታወሳል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በየዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ቀኑ በአንድነትና በእኩልነት በደማቅ ሥነ ሥርዓት እየተከበረ ይገኛል። እነሆ ዘንድሮም 19ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል "ሀገራዊ መግባባት-ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ የፊታችን ኅዳር 29 በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በአርባ ምንጭ ከተማ ይከበራል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኅዳር 29 የሚከበረውን 19ኛውን የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በዓል ታሳቢ በማድረግ "ሀገራዊ መግባባት - ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ሃሳብ የመዲናዋ ሴቶች ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ በተለያዩ መርሃ ግብሮች የሚያከብሩበትን መድረክ አመቻችቶ፤ በሁሉም ወረዳዎችና ክፍለ ከተሞች በድምቀት ሲከበር ቆይቷል። በመጨረሻም ክብረ በዓሉን ታሳቢ ያደረገ የሴቶች የማጠቃለያ መርሃ ግብር ከሰሞኑ ቢሮው ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በመተባበር አዘጋጅቷል።



በመድረኩ የተሳተፉ የከተማ ሴቶች፤

በመድረኩም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልከድር፣ የከተማዋ ከፍተኛ አመራሮች፣ ከየክፍለ ከተማው ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ ከሁለት ሺህ በላይ ሴቶች ተሳትፈዋል።

አፈ ጉባኤዋ ወይዘሮ ቡዜና በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ባደረጉበት ወቅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ ሁሉንም ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሚያሳትፍ፤ በፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ አካታች አስተዳደር ሥርዓት ለመገንባት በተደረጉ ጥረቶችና በተገኙ ውጤቶች ዙሪያ እንዲሁም የለውጡ ቱርፋቶችን አጎልብቶ ለማስቀጠል የሚያግዝ የጋራ አረዳድ ለመፍጠር ክብረ በዓሉን ታሳቢ በማድረግ በየደረጃው የሴቶች የውይይት መድረክ ሲካሄድ ቆይቷል።

ከማዕከል እስከ ወረዳ ሲካሄድ በቆየው የሴቶች የውይይት መድረክ፤ ሀገሪቱ እየገነባች ባለችው እውነተኛ አካታች ህብረ ብሔራዊና ዲሞክራሲያዊ ፌዴራል ሥርዓት፤ ሥርዓቱን በፅኑ መሠረት ላይ ለማቆም በለውጡ እየተወሰዱ ያሉ አበረታች ርምጃዎች እንዲሁም ሴቶችን ከማሳተፍና ተጠቃሚነታቸውን ከማረጋገጥ አንጻር በተወሰዱ የሪፎርም ሥራዎች የተመዘገቡ ውጤቶችና ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ የሃሳብ ልውውጦች መደረጉን ተናግረዋል።

ሴቶች ወቅታዊ ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን በመገንዘብ ለተሻለች ሀገር ግንባታ የበኩላችን ኃላፊነት መወጣት እንዲችሉ መሰል በስፋት የሚሳተፉበት መድረኮች በቀጣይም መዘጋጀት እንዳለባቸው አፈ ጉባኤዋ አመላክተው፤ ለውጡ ሴቶችን ወደ አመራርነትና ውሳኔ ሰጭነት በማምጣት ረገድ የወሰደው ርምጃ አንዱ ትልቁ ውጤት ነው። ዛሬ ላይ ሴቶች ከምንጊዜውም በላይ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች ቁልፍ ውሳኔ በሚሰጥባቸው የመንግሥት ኃላፊነት ቦታ ይዘዋል።

ሌላው ሴቶች ባለባቸው የቤተሰብ ኃላፊነት ለተደራራቢ ችግሮች ተጋላጭ መሆናቸው ይታወቃል። ይህንን ታሳቢ በማድረግ በትምህርት ቤቶች የሚካሄደው የምገባ ፕሮግራም፣ የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ... ወዘተ በዋናነት የሴቶችን ጫና ለማቃለል ያለሙ ናቸው። በከተማዋ ከተሠሩ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለነገዋ የሴቶች ማዕከል፣ የእንጦጦና የለሚ እንጀራ ፋብሪካን ለአብነት ብንወስድ፤ የሴቶች ተጠቃሚነትና ማህበራዊ ፍትህ የተረጋገጠባት፣ ልማቱ አካታች የሆነ የብልጽግና ተምሳሌት ከተማ ዕውን ለማድረግ መንግሥት ቁርጠኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ወይዘሮ ቡዜና፤ በመንግሥት በኩል የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተጀመሩ ሰፊ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በሚታቀዱ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ሴቶች የነቃ ተሳትፎ በማድረግ አርአያ ሊሆኑ እንደሚገባ አሳስበው፤ የሰላም እጦት፣ ግጭትና ጦርነት የልማት እንቅፋት ብቻ ሳይሆኑ በሕገ-መንግሥቱ የተረጋገጡ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ጭምር እንዲጣሱ የሚያደርጉ ናቸው። በተለይ ሰላም ሲደፈርስ ቅድሚያ ተጠቂዎች ሴቶች ናቸው። ይህንን በመገንዘብ መንግሥት በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ለማስፈንና የተዛቡ ትርክቶች በውይይትና በሀገራዊ መግባባት ለመፍታት የሚያደርጋቸው ጥረቶች እንዲሳኩ ሴቶች ሊደግፉና ለሰላም ዘብ ሊቆሙ ይገባል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ወይንሸት ዘሪሁን በበኩላቸው፤ በወል ጉዳዮቻችን ላይ መግባባትን በመፍጠርና የሁሉም ሕዝቦች መብትና ጥቅም የተከበረባት ሁለንተናዊ ብልጽግና የተረጋገጠባት ጠንካራ ሀገር ለመገንባት በአብሮነት የመቆም የጋራ ኃላፊነት አለብን ሲሉ አሳስበዋል።

ሀገራዊ አንድነትን ለማምጣት የሴቶች ሚና ትልቅ ነው የሚሉት ኃላፊዋ፤ ሴቶች ተፈጥሮ የቸራቸውን የፍቅር እና የርህርሄ ኃይል ተጠቅመው በመከባበር ላይ የተመሠረተ አንድነትን፣ ፍቅርን፣ መከባበርን እንዲሁም የእህትማማችነት፣ የወንድማማችነት ስሜትን የሚያጎለብቱ፤ በአንጻሩ ጥላቻና መከፋፈልን የሚያርቁ ሀገራዊ የመፍትሔ ምክረ ሃሳቦችን በማፍለቅ ለሀገር ሰላምና አንድነት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አቅርበዋል።

"ለውጡ ለኛ ለሴቶች ልዩ እድል ነው" ያሉት ወይዘሮ ወይንሸት፤ በለውጡ የተመዘገበው የሴቶች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትና ተሳትፎ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሴቶች ለሰላም፣ ለልማት፣ ለአንድነት ዘብ ሊቆሙ እንደሚገባ ተናግረዋል።

የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ሴቶች ማኅበር ሰብሳቢ ወይዘሮ መቅደስ ተክሉ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ በሰጡት አስተያየት፤ ኅዳር 29 የብሔር ብሔረሰቦች ቀን መከበሩ ሰላምና አንድነትን የሚያረጋግጥ፤ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን የሚያዳብር ነው ብለዋል፡፡

ልዩነታችን የሚያጣላንና የሚያጋጨን ሳይሆን ውበታችን ነው፤ ውበታችን የሆነውን ልዩነታችንን በማቻቻል፤ በአንድነት እንድንኖር እሴቶቻችን፤ ባሕላችን መከበር አለባቸው፤ ጠብና ንትርክን ትተን በሰላምና በአንድነት መኖር አለብን ይላሉ፡፡

# ከነገ...

ከገጽ 16 የዞረ

ሙሉ ከወለደች በኋላ ሆስፒታል በቆየችባቸው ጊዚያት ሕፃኗ ተገቢውን ሕክምና እንድታገኝ ሆነ። ሕክምናው ግን ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ አልነበረም። ተደጋጋሚ ምልልስና ክትትልን ይፈልጋል። እናት አስቀድማ ራሷን አዘጋጅታለችና ይህን ማድረጉ አልከበዳትም። ስለ ልጇ መሆን የሚገባውን ሁሉ ለማድረግ ዋጋ እየከፈለች ነው።

ባለቤቷም ቢሆን ከሚስቱ ጋር ውሳኔውን በእኩል አሳልፏል። ልጃቸው ወደዚህች ምድር እንድትቀላቀል የፈቀደው በሙሉ ልብ ነው። አሁን ውሎ አዳር በሆስፒታል ሆኗል። እናትና ልጅ አልጋ ይዘው ወራትን ቆጥረዋል። ሙሉ በየዕለቱ በልጇ ላይ ለውጥ ማየት ጀምራለች። የሕፃኗ የጭንቅላት ክፍተት እየቀነሰ መሆኑ በባለሙያዎች ተነግሯታል። ይህን ባወቀች ጊዜ እፎይታ ይሰማት ይዟል።

ባለቤቷ የሚስቱና የሕፃኗ የሆስፒታል ቆይታ የተመቸው አይመስልም። ሕክምናው ጊዜ ፈጅቶ ወራት ማስቆጠሩ እያሳሰበው ነው። አስቀድሞ በልጁ ሕይወት ላይ ሲወስን ይህን ያህል ይከብድ አልመሰለውም። አሁን ግን ሁኔታዎች እያሳሰቡት መጨነቅ፣ መበሳጨት ጀምሯል።

## የአባወራው ነገር ...

ሙሉ የልጇን ሕክምና ጨርሳ ወደቤት ስትመለስ ባለቤቷ እንደቀድሞው አልቆያትም። በፍቅር አልባ ገጽታ ተቀበላት። ሁኔታው ፈጽሞ አልገባትም። በየምክንያቱ ያኮርፋል፣ ይናደዳል። የሕፃኗ ጤና ማጣት ባሰበው ልክ አለመሆኑ ሰላም ነስቶታል። ይህ እውነት በእሱ ውስጥ ብቻ አልቀረም። በሆነው ሁሉ ምክንያቱን በሚስቱ አሳቦ ተጠያቂነትን እየሸሸ ነው።

ሙሉ የባሏ አዲስ ባህሪ ቢከብዳትም ለምን አላለችም። ሁሉን ችላ ስሜቱን ልትረዳው ሞከረች። ሕፃኗ ከተወለደች ጀምሮ የቤቱ ሰላም ተናግቷል። ሳቅ ጨዋታ ጠፍቷል። የሕክምናው ውጤት በሕፃኗ ጭንቅላት ላይ መልካም ቢሆንም የጀርባዋ ላይ ክፍተትና ቁስል በቶሎ አልገጠመም። በየጊዜው ሆስፒታል የምትመላለሰው እናት ደከመኝ፣ ሰለቸኝ አላለችም። ጊዜና ጉልበቷን፣ ኑሮና ሕይወቷን ለልጇ አበርክታለች።

ሕፃኗ ስድስት ወር እንደሞላት አባወራው ቤቱን ጥሎ ወጣ። ምክንያቱን አሳምራ የምታውቀው ሚስት ‹‹አባክህ ፣ተመለስ›› አላለችውም። ውስጧ እያነባ፣ አንጀቷ እያረረ በዓይኖቿ ሸኘችው። አባወራው ትዳሩን በትኖ ከሄደ በኋላ ሙሉ የብቸኝነትን ሕይወት ጀመረች። ይህ ጊዜ የታመመች ልጅ ለያዘችው እናት ቀላል የሚባል አልሆነም።

ወይዘሮዋ በየጊዜው ሆስፒታል መመላለሱ አቅሟን ፈተነው። እሱን ትታ ጤና ጣቢያ ላይ ጀመረች። የቤት ኪራዩ፣ የዕለት ወጪው ጭንቀት ሆነባት። በወጉ ቁስሏ ያልደረቀ ልጇን አዝላ በየሰው ቤት መሥራት ጀመረች። የሕፃንዋ ህመም የዋዛ አልሆነም። የእናቷ ምኞት አልባ ኑሮ በየቀኑ እየፈተነ አሰቃያት።

## የእናት ጉጉት...

ትንሸዋ ልጅ ማደግ ጀምራለች። እንደ ሕፃን ‹‹እማማ፣ አባባ›› ማለት እየሞከረች ነው። እናት አንድ ዓመት ሊሞላት አካባቢ እንደ እኩዮቿ መዳህ፣ መቆሟን ናፈቀች። እጆቿን ይዛ፣ ወገቧን ደግፋ ልታራምዳት ሞከረች። ምኞቷ ሁሉ ከንቱ ነበር። ሕፃንዋ እንዲህ ልትሆን አልታደለችም። እናት የልቧ፣ የሃሳቧ አልሞላም። ሙሉ የሕፃንዋ የጀርባ አጥንት በቀዶ ሕክምናው ወቅት መዛባቱን አውቃለች። መፍትሔ አልባው ችግር አብሯት ቀጥሏል።

የልጇ እድሜ ከፍ ማለት ሲይዝ የጀርባዋ ቁስል እየከፋ ሄደ። አተነፋፈሷና የሆዷ ቅርጽ እንደተለመደው አልሆነም። የሆዷ አቀማመጥ እንደተለመደው አይደለም። ተዛብቷል። የቤት ኪራይና የዕለት ጉርስ ጥያቄ አርፎ የሚያስቀምጣት አልሆነም። ስለኑሮ ግዴታ ልጇን አዝላ በየሥራው መንከራተቷን ያዘች። እንዲያም ሆኖ እናት ሙሉ ስለልጇ ሕክምና አብዝታ ትጨነቃለች።

ብዙ ጊዜ ሁኔታዋን ያዩ ጎረቤቶቿ ልጇን ትታ እንድትሄድ ይጠይቋታል። እሷ ግን ምን ቢቸግራት ይህን ለማድረግ አትወሰንም። የጭንቅላቷና የጀርባዋ ችግር የእሷን ጥንቃቄ ስለሚሻ አምና ጥላት ለመሄድ ይቸግራታል። እየጨነቃት ታመሰግናቸዋለች።

## አንዳንዶች...

ሙሉ ልጅ ከወለደች ወዲህ የቅርብ የምትላቸው ዘመዶቿ ሳይቀሩ ፊታቸውን እያዞሩባት መሆኑን ተረድታለች። አንዳንዴ ለሰላምታ ስልክ በደወለች ጊዜ ሊያነሱላት አይወዱም። የእሷ ፍላጎት ገንዘብ ሊሆን ይችላል ያሉ በርካቶች ተደጋጋሚ ጥሪዋን እንዳላየ ያልፉታል። ሙሉ እንዲህ በአጋጠማት ጊዜ በልጇ ላይ ያሳለፈችው ውሳኔ ልክ አለመሆኑን እያሰበች ራሷን ትወቅሳለች።

ውሎ አዳሯ ከሆስፒታል አልጋ የሆነው እናት ኑሮ እየከበዳት ነው። ተከታታይ ሕክምና የሚሻው የልጇ አካል ያለእሷ ዋስትና አላገኘም። ችግሩ ሲከፋ፤ ኑሮ ሲወደድ ‹‹ነገን ምን እሆናለሁ›› ይሉት ሃሳብ እያስጨነቃት ነው። አንዳንዴ የልጇ አባት ዘንድ ደውላ ሁኔታውን ልታስረዳው ትሞክራለች። እሱ ገና ድምጽዋን ሲሰማ ጆሮዋ ላይ ይዘጋባታል።

ባል ከሚስቱ ከተለየ ጥቂት ጊዜ በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ቤት መኖርና መመላለስ ጀምሮ ነበር። ያልተመቸው ሕይወት ግን አብሮ ሊያዘልቀው አልቻለም። ሁሌም እሷን ብቻ ተጠያቂ ከማድረግ የማይዘለው አባወራ እናት ልጇን መጠቀሚያና መለመኛ እንዳደረገቻት ጭምር ያስባል። ለሙሉ ይህ ዓይነቱ ንግግር አብዝቶ ልቧን ይሰብረዋል። በየጊዜው አምርራ ታዝናለች፣ ትከፋለች።

አሁን ልጇ ሁለት ዓመት አልፏታል። ደስ ባላት ቀን በሳቅ እየፈካች ታጫውታለች። ባመማት ጊዜ ህመሟ የእናቷ ጭምር ነው። ቁስሏ ያደማታል፣ ስቃይዋ ይሰማታል። አንዳንዴ በእሷ ዕድሜ ያሉ ልጆችን ስታይ እንደ እነሱ መራመድ ፣ መሮጥ ያምራታል። እጇን ፊት ለፊት እየጠቆመች ታሳያታለች። እናት ሙሉ የሆዷን በሆዷ አድርጋ ፈገግ ትልላታለች።

ልጇ መቼውንም ቆማ መሄድ እንደማትችል የምታውቀው እናት ፍላጎቷ ሲገባት ስለእሷ ዕንባ ያንቃታል፣ የእናትነት አንጀቷ ይላወሳል። እንዲያም ሆኖ በሆነባት ነገር አምርራ አታዝንም። ልጇ የጀርባዋ ቁስል ከዳነና አዕምሮዋ ጤነኛ ከሆነ ‹‹ተመስገን›› ማለትን ትወዳለች። የእግሮቿ ጉዳይ ሌላው ችግር ቢሆንም ወደፊት በዊልቸር መጠቀም መቻሏ ያጽናናታል።

ሙሉ የልጇ አባት ቢከፋባትም ቤተሰቦቹ መልካም ናቸው። ችግሯን ይረዳሉ። ባላቸው አቅም ከጎኗ ሆነው ጎዶሎዋን ይሞላሉ። በተለይ ታላቅ ወንድሙ ስለእሷ ሀዘኔታው ይለያል። የወንድሙ ድርጊት ስለሚያበሽቀው አብዝቶ ተቃዋሚው ነው። ሁሌም ከልጆቹ አፍ ነጥቆ፣ ከቤት ከጓዳው አጉድሎ ያካፍላታል።

አንዳንዴ ሙሉ ለቤት ኪራይ እጅ ሲያጥራት ሀገር ቤት ያሉ ቤተሰቦቿ ዘንድ ትደውላለች። ችግሯን አስተዛዝና ስትነግራቸው አይጨክኑም። ያላቸውን አሰባስበው ይልኩላታል። ካገኘችው ብር ለቤት ኪራይ ከፍላ ጥቂት የሚቀራትን ለልጇ ፍላጎት ታውላለች።

## መልካም ጎረቤቶች ...

ሙሉ መልካም ጎረቤቶቿ የከፉ ቀናት አጋሮቿ ናቸው። በከፋት፣ ባዘነች ጊዜ ከጎኗ አይርቁም። ሕይወት ኑሮዋን ለመረዳት፣ ችግር ፈተናዋን ለመካፈል ወደኋላ አይሉም። የኑሮ ደረጃቸው ተመሳሳይ ቢሆንም ከእሷ ራሳቸውን ማስቀደም ልምዳቸው አይደለም። ወጥታ ስትገባ ቤቷን ከፍተው ይጠብቋታል። ይህን ስታይ ሙሉ ድካሟ ይጠፋል። እንደ ሁልጊዜው ደጋግማ ፈጣሪዋን ‹‹ተመስገን ›› ትላለች።

እናት ሙሉን የመሰሉ በርካታ ሴቶች ስለልጆቻቸው መኖር ሻማ ሆነው መቅለጣቸው ዕሙን ነው። ሁሉም ባይባሉም በርካቶቹ አባቶች የጤና ችግር ካለባቸው ልጆች ጋር መዝለቅን አይሹም። ቤታቸውን ትተው፣ ትዳራቸውን በትነው ሌላ ሕይወት ለመመስረት ይፈጥናሉ። እናት ሙሉ የመጀመሪያ ልጇ የሆነችውን ሕፃን ይዛ ዛሬም ስለጤናዋ፣ ስለሕይወቷ መትጋቷን ቀጥላለች። ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣ አታውቅም። ዘወትር መጪውን ጊዜ በሃሳብ እየሳለች ከነገ ማዶ ያለውን ተስፋ ታልማለች። ብርቱዋ ፣ ብቸኛዋ እናት ሙሉ ላቃቸው።


## ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

በአርሲ ዞን ማረሚያ ቤት ውስጥ ለሚገኙት የሐግ ታራሚዎች የበሰለ ምግብ ወይም ለምግብ አቅርቦት የሚውል ጥሬ እህል እና የተለያዩ ማጣፈጫዎችን እንዲሁም የማገዶ እንጨት የ2017 ዓ.ም በጀት ከጥር 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30/2017 ዓ.ም ለ6/ስድስት/ ወር ለሚቆይ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሠረት ማንኛውም ጨረታውን ለመካፈል የሚፈልግ ድርጅት ወይም ግለሰብ

1. ተወዳዳሪዎች የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ወይም ቢሮ ወስጥ የተመዘገቡና የዘመኑን የሥራ ግብር የከፈሉ ለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ እና አግባብነት ያለው የ2017 የታደሰ የንግድ ሥራ ፍቃድ ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) የተመዘገቡ ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሚያቀርቡ መሆን አለባቸው፡፡
3. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 500 /አምስት መቶ/ ከፍሎ ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት ከዞን ማረሚያ ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ሰነዳቸውን በሰም በታሸገ ፖስታ በማድረግ በማረሚያ ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት ውስጥ ለዚህ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በማስገባት መወዳደር አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾቹ የጨረታ ማስከበሪያ ከመቶ 2% በጥሬ ገንዘብ ወይም በተመሰከረለት ቼክ እና የምግብ እህል ናሙና ከጨረታ ሰነድ ጋር አያይዞ ማቅረብ አለባቸው፡፡
6. በጥቃቅን እና አነስተኛ ተደራጅቶ የበሰለ ምግብ ለማቅረብ የሚቀርቡ ማህበራት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ካልተገኘ በጥሬ እህል እናወዳድራለን፡፡
7. ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀን በአየርላይ ውሎ በ16ኛው ቀን በሥራ ቀን ከረፋዱ በ4፡00 ሰዓት በዞን ማረሚያ ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው እንዲሁም የሕግ ታራሚ ኮሜቴዎች እና የማረሚያ ቤቱ ጨረታ ኮሚቴ አባላት በተገኙበት ይከፈታል፡፡
8. የዞኑ ማረሚያ ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
9. በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅቶ የበሰለ ምግብ ለማቅረብ የሚቀርቡ ማህበራት በማረሚያ ቤቱ ውስጥ በተዘጋጀ ማብሰያ ቤት ውስጥ በተዘጋጀ ማብሰያ ቤት ውስጥ ምግብ አብስሎ ማቅረብ የሚችል፡፡
10. ማረሚያ ቤቱ የሚገኝበት ከተማ በአርሲ ዞን አሰላ ማረሚያ ቤት

ለበለጠ መረጃ፡- በስልክ ቁጥር 0223311040/0913439972

**በኦሮሚያ ማረሚያ በቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን አርሲ ዞን ማረሚያ ቤት**

**አሰላ**

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የሪል ስቴት ዘርፉን በሕጋዊ ማዕቀፍ

በኃይሉ አበራ



በረቂቅ አዋጁ ላይ በተደረገው ውይይት ገንቢ ሃሳቦች ተገኝተዋል

በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች በፍጥነት እያደገ ከመጣው የመኖሪያ ቤት ፍላጎት ለመመለስ መንግስት ከሚያካሂደው የቤቶች ልማት በተጨማሪ የግሉ ዘርፍ ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይታመናል። ለእዚህም የሚጠበቀውን ያህል ባይሆንም፣ የሪልስቴት ዘርፍ በቤቶች ልማት ላይ የራሱን ሚና እየተጫወተ መሆኑ ይታወቃል። ዘርፉ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉበት የሚገለጽ ቢሆንም፣ ከእነ ችግሮቹም ሆኖ በተለይ በአዲስ አበባ ቤቶችን ገንብቶ በማቅረብ በኩል እየሰራ ቆይቷል።

የሪልስቴት ዘርፉ ችግሮች ውስብስብ ስለመሆናቸው ይገለጻል፤ ገንዘብ ከፍለው ቤት ያላገኙት ወይም ገንዘብ ከፍለው ቤት ማግኘት ጣር የሆነባቸው፣ ሪል ስቴት እናለማለን ያሉ አካላት ገንዘብ ሰብስበው እብስ ያሉበት ሁኔታ ጥቂት አለመሆኑ ሲታሰብ ዘርፉ ውስብስብ ችግሮች ያሉበት ስለመሆኑ መረዳት አያዳግትም።

መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ በዓለም ከ90 በላይ ሀገራት የሪልስቴት ዘርፉን ሥርዓት ዘርግተው እየመሩ ይገኛሉ። የደቡብ አፍሪካ እና ሕንድ የዘርፉ ኢንዱስትሪ በንብረት ግመታ እና በማዘጋጃ ቤታዊ የንብረት ተመን አዋጆች ይመራል።

መንግስትም የዘርፉ ባለሙያዎችም ዘርፉ በሕግ እንዲመራ ሊደረግ ይገባል በማለት ሲወተውቱ ቆይተዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመንግስት በኩል ዘርፉ በአግባቡ እንዲመራ በማድረግ የአገርንም ሆነ የማህበረሰቡን የቤት ፍላጎት በመመለስ በኩል ዘርፉ ሚናውን እንዲጫወት ለማድረግ እየተሰራ ነው።

በቅርቡም በሪልስቴት ዘርፉ የሚታየውን ይህን ችግር ለመፍታት እና በዘርፉ የሚንቀሳቀሰውን ኢኮኖሚ በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለውይይት ቀርቧል። በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማና መሰረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ለውይይት በቀረበው ‹‹የሪልስቴት ልማት እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ ረቂቅ አዋጅ›› ላይ ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎበታል።

በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የቤቶች ልማት መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀጋዬ ሞሹ በረቂቅ አዋጁ ላይ ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንዳሉት፤ ሪልስቴት የሚለው ለመኖሪያነት፤ ለኢንዱስትሪ፤ ለማህበራዊ እና ለሌሎች አገልግሎት የተገነባ ህንፃና ተጓዳኝ ግንባታዎችን ያካትታል። “የሪልስቴት አልሚ” ማለት በአዋጁ ከተፈለገበት ትርጉም አንጻር ሲታይ ከ50 ቤቶች በላይ በግሉ ወይም ከመንግስት ወይንም ከሌሎች አካላት ጋር በአጋርነት የሚገነባና በሽያጭ ወይንም በኪራይ ለተጠቃሚ የሚያቀርብ ማንኛውም አካል ማለት ነው።

ሁሉም አይነት ህንጻ ወይንም ቤት ግንባታ ሪልስቴት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አልሚ የሚባለው ሰፊ ስራ የሚሰራ መሆን እንዳለበት ተጠቁሟል፤ በአነስተኛ ከተማ ደረጃ የቤት ችግርን ከመፍታት አንጻር ትርጎም ያለው ቤት ብዛት ሰንት ሊሆን ይቻላል በሚል ያለውን ክፍተትና ዓመታዊ ፍላጎት ከግምት በማስገባት የሚገነቡ ቤቶች ቁጥር መቀመጡም ተብራርቷል።

በአዋጁ የተጠቀሱትን የሪልስቴት ልማት እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ ስርዓት ለማስያዝ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመፈጸምና ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው በፌዴራል ወይም በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር የከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ መሆኑን አመልክተዋል።

የአዋጁ ክፍል ሁለት የሪል ስቴት አልሚዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድና የይዞታ ማስረጃ አሰጣጥን የያዘ ሲሆን፣ በስድስት አንቀጻች የተከፋፋለ ነው። የዚህ ክፍል አንቀጽ አምስት ስለ ሪል ስቴት አልሚዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚዘረዝር ሲሆን፣ ማንኛውም የሃገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሃገር የሪል ስቴት አልሚ በዘርፉ ለመሰማራት ፈቃድ ማውጣት አለበት።

አቶ ፀጋዬ የቤት እጥረት የከተሞችን አቅምና የዜጋውን ኑሮ በከፍተኛ ሁኔታ እየፈተነ እንደሚገኝ ጠቅሰው፣ በዚህ ዘርፍ የሚሰማሩ አካላትን ለይቶ መደገፍ ያስፈልጋል ብለዋል። ቤት ፈላጊዎችንም በእጥረት እና በገበያ ግልጽነት መጓደል ምክንያት ከሚደርስባቸው ጫና ለመታደግ አልሚዎች ፈቃድ እንዲያወጡ በማድረግ ሂደቱን መምራት አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ተናግረዋል።

የቤት እጥረቱ አጠቃላይ ሀገራዊ እድገቱን ሊያናጋ በሚችል ደረጃ የሠፋ መሆኑን ጠቅሰው፣የሀገራዊ ካፒታል አቅም ዝቅተኛ መሆን፣ የቴክኖሎጅ እጥረት እንዳለም ገልጸዋል። እነዚህን ችግሮች ለማቃለል በሚያግዝ መልኩና የውጭ ምንዛሬ አቅም በማይፈትን ሁኔታ በቤት ልማቱ የውጭ ባለሀብትን ማስገባት አስፈለጊ ሆኖ መገኘቱንም ጠቁመዋል።

የቤት ገዥውን ስጋት እንዲሁም የሀገራዊ ባለሀብቱን የገንዘብ እጥረት የሚቀንስ እንዲሁም ቁጠባን የሚያበረታታ ስልት በመከተል ችግሩን ማቅለል ተገቢ መሆኑ እንደታመነበት አስታውቀው፣ ለሃገር ውስጥ የሪል ስቴት አልሚ የቅድመ ሽያጭ አሰራር በረቂቅ አዋጁ መካተቱን አመልክተዋል።

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 6 የሪልስቴት አልሚ የቦታና የተናጠል ይዞታ ማረጋገጫ አሰጣጥ ተመላክቷል። በከተሞች ለሪል ስቴት ልማት የሚውል ቦታ በከተማ መሬት ሊዝ ሕጉ በተደነገገው መሰረት ይቀርባል። እንደ ከተሞቹ ስፋት ቁጥሩ የተወሰነ ቤት ሰርቶ ለማስተላለፍ የሚፈልግ የሪልስቴት አልሚ መሬት ቅድሚያ ተሰጥቶት በስፋት በከተማ መሬት ሊዝ ሕጉ መሰረት እንዲቀርብለት እና እንዲበረታታ እንደሚደረግ ተቀምጧል።

በአንቀጽ ሰባት እንደተመለከተውም የሪልስቴት አልሚ በውል ሰነዱ፣ በሕንጻ አዋጁ እና በሌሎች የሕግ ማሕቀፎች የተመላከቱ ግዴታዎችን ማክበር ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የቤቱ ግንባታ ከ80 በመቶ ሳይጠናቀቅ ለደንበኛ ማስተላለፍ አይችልም። ደንበኛውም ለከፈለው ገንዘብ ሕጋዊ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ አለበት።

በረቂቅ አዋጁ እንደተመለከተው፤ የሪል ስቴት አልሚው የመሬት ይዞታ ማረጋገጫና የግንባታ ፈቃድ ከሚመለከተው አካል ከመረከቡ በፊት ደንበኞችን መመዝገብ እና ቅድመ ክፍያዎችን መሰብሰብም አይችልም። በሕጋዊ መንገድ የተረከበውን መሬት ማስተናገድ ከሚችለው ቤት በላይ የደንበኛ ቁጥር መመዝገብ አይኖርበትም። የሪልስቴት ልማት፣ ግብይትና ግመታን ለሚመለከቱ መመሪያዎች ተገዢ መሆን አለበት።

አንቀጽ ስምንት የሪልስቴት ቤት ገዥ ግዴታዎችን ይዟል። በዚህም አንድ ቤት ገዢ በገባው ውል መሰረት የሚጠበቅበትን ክፍያ በወቅቱ መፈጸም አለበት። ገዢውም የቤት ግንባታ እና የውል ሂደትን ለማጠናቀቅ የሚፈለጉ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል። የጋራ መብትን ለማስጠበቅና ግዴታን ለመወጣት እንዲረዳ የመኖሪያ ቤት ገዢ ባለቤቶች ማኅበር እንዲመሰረትና እንዲጠናከር መሳተፍና የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንደሚኖርበት በአንቀጹ ሰፍሯል።

በአንቀጽ ዘጠኝ ደንበኞች የሚደርስባቸውን እንግልትና ኪሳራ ለመቀነስ በማሰብ ሀገር በቀል አልሚዎች ቤቱን ሳይገነቡ ለቤት ፈላጊዎች በቅድሚያ በሚሸጡበት ወቅት ሊከተሉት ስለሚገባ ስርዓትም ተቀምጧል። ከቤት ገዥዎች የሚሰበሰበውን ገንዘብ እና የባንክ ሂሳብ ገቢ ወይም ወጪ አሰራሮችና ሊከተሉት በሚገባቸው የዋስትና ቅድመ ሁኔታዎች ላይ አስገዳጅ ሁኔታዎች ተካተዋል።

አንቀጽ 10 አግባብ ያለው አካል የቤት ገዥዎች በጋራ ሕንጻ ቤት ባለቤትነት አዋጅ እና በሕብረት ስራ ማህበራት አዋጅ መሰረት በማህበር እንዲደራጁ ድጋፍ በማድረግ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቻቸውን በጋራ የሚከታተሉበት ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት ያስቀምጣል። የሪል ስቴት አልሚው የቤት ገዥዎችን የህንጻ መግለጫና ሌሎች አስፈለጊ መረጃዎች ለቤት ገዥዎች ማስረከብ እንዳለባቸው ተገልጿል።

በረቂቅ አዋጁ ላይ ማብራሪያ ከተሰጠ በኋላ የውይይቱ ተሳታፊዎች ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን አንስተዋል። አቶ ፀጋዬ ሞሼም ለጥያቄዎቹ ምላሽ በሰጡበት ወቅት እንዳስታወቁት፤ የውጪ አልሚዎች በሪል ስቴቱ ልማት ተሳትፎ ለማድረግ ቀደም ሲል 20 ሚሊየን ዶላር ማምጣት ይጠበቅባቸው ነበር። በዚህ አዋጅ ግን ይህ የቀረ ሲሆን፣ 50 ቤቶችን ግን መስራት ይጠበቅባቸዋል። ገንዘብ ከማህበረሰቡ ሰብስበው መስራት የተከለከለ መሆኑን ጠቅሰው፣ የወጭ አልሚዎቹ የራሳቸውን ፋይናንስ በመያዝ 50 ቤቶችን መስራት የሚችሉ ከሆነ በሪልስቴት ዘርፉ መሰማራት ይችላሉ ብለዋል። ይህም ልማቱን እንዲያበረታታ በሚል ገደቡ ክፍት መደረጉን አመላክተዋል።

የሀገር ውስጥ ባለሀብቱም ከውጭ ባለሀብቶች ጋር አብረው ማልማት እንደሚችሉም ተጠቁሟል፤ ይህም ለቴክኖሎጂ ሽግግር ፋይዳ እንዳለው ጠቁመዋል። በመሆኑም የሪልስቴት ገበያው ሰፊ መሆኑን ጠቅሰው፣ የውጭ አልሚዎች ቢመጡ የተሻለ መሆኑን ተናግረዋል። በዘርፉ ለመሰማራት ለሚመጡ የውጭ አልሚዎች ግብኣት ላይ የተጣሉ ታክሶችን በሚያበረታታ መልኩ ማስቀመጡ ለአፈፃፀም የሚመች መሆኑን ጠቅሰው፣ እንደሚታይ ጠቁመዋል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች 50 ቤቶች ብሎ ከማስቀመጥ በመጠን በሄክታር ይሁን የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል። በዚህ ላይ በሰጡት ምላሽም በከተማ ቤት ላይ ከፍተኛ ችግር ፈቺ ሆኖ የመጣው አነስተኛ ቤቶችን በብዛት መስራቱ መሆኑን ጠቅሰው፣ ብዙ ሰዎች ትንንሽ ቤት እየሰሩ የቤት ችግሩን እየቀረፉ ነው ብለዋል።

ብዙዎቹ የከተማ ነዋሪዎች ከ60 በመቶ በላይ ተከራይ ናቸው። አብዛኛዎቹም የተከራዩት ከግለሰብ ነው። በመሆኑም የግለሰብ ቤትን ማበረታታት ተገቢ ነው ሲሉ አብራርተው፣ ሁለት ወይም ሶስት ቤት የሚገነቡትን ሁሉ የሪልስቴት ፍቃድ አውጡ በማለት ማስገደድ ልማቱን ወደኋላ እንደሚጎትተው አስታውቀዋል።

የሪልስቴት አልሚው ፍቃድ አለኝ በሚል ከግለሰብ አልሚዎች ጋር ግዴታ ሊጣልበት የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ጠቅሰው፣ በቤት ቁጥር ወይም በካሬው መጠን ማስቀመጥ ተገቢነት ያለው መሆኑን አመልክተዋል። ቤቱም በፕሮጀክት የተወሰነ መሆኑን ተናግረው፣ አዲስ አበባ ላይ ፍቃድ የተሰጠው ድሬዳዋ ላይ ልስራ ማለት አይችልም ብለዋል። 50 ቤቶች ሲባልም አንድ ቦታ ላይ ስለሚገነቡ ቤቶች እንጂ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ስለሚገነቡ ቤቶች እንዳልሆነ አስገንዝበዋል።

የሪል ስቴት አልሚው 80 በመቶ የተጠናቀቀ ቤት ማስተላለፍ እንደሚኖርበት የተገለጸውን አስመልክተው ሲያብራሩ እንደገለፁት፤ የሪል ስቴት አልሚዎች ለነዋሪዎች የተጠናቀቀ ቤት ማስተላለፍ አለባቸው። የተጠናቀቀ ቤት ሲባልም ከደንበኛው ጋር በሚደረገው ስምምነት መሰረት ቢያንስ 80 በመቶ የተጠናቀቀ እና በተጨማሪም ኤሌክትሮ መካኒካል የቧንቧ ስራዎች፣ የንፅህና ስራዎች የተሟሉለት ቤት ማቅረብን ይመለከታል።

ረቂቅ አዋጁ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ሲንከባለል የመጣ መሆኑን አስታውሰው፣ 40 በመቶ የማህበረሰብ ክፍልን ተጠቃሚ ለማድረግ የወጣ መሆኑን ተናግረዋል። በሳይንሳዊ መንገድ ተሰልቶ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ ዝቅተኛ ገቢ፣ መካከለኛ ገቢ ያለው ማነው የሚለውን ታሳቢ በማድረግ 40 በመቶውን የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ለማድረግ እንደሚሰራበት ገልፀዋል።

እስከ አሁን ባለው አሰራር ቤት ገዢዎች ገንዘብ ሰጥተው፣ ቤት ይሰራላችኋል ተብለው ቤቱን የማያገኙበት ሁኔታ መኖሩን ጠቅሰው፣ በቀደመው አሰራር ቅድመ ሽያጭ ሙሉ በሙሉ ይከለከል እንደነበር ተናግረዋል። የሌሎች አገሮች ልምድ ሲታይ ገንዘቡ ላይ ቁጥጥር እየተደረገ ስርዓት ተደርጎለት ለልማት እንደሚውል ጠቅሰው፣ አንዱ መፍትሔ የሚሆነው ፈጥኖ ቤቱን መገንባት መሆኑን አመላከተዋል።

የሪል ስቴት ቤት አልሚው ለቤት ግንባታ የሚሆን የቤት ልማት ግብኣት ሀገር ውስጥ የሚያመርት ከሆነ ለእዚህ ስራ /ለማኑፋክቸሪንግ/ የሚሆን መሬት በተጨማሪ ሊቀርብለት እንደሚችልም ጠቁመዋል። ለተጠያቂነትና ግልፅነት ሲባልም ራሱን የቻለ አማካሪ፣ ስራ ተቋራጭ ሊኖረው እንደሚገባም አስገንዝበዋል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሄለን ደበበ እንደተናገሩት፤ የሪል ስቴት ኢንዱስትሪው በሕጋዊ ማሕቀፍ መምራት እንዳለበት አስገንዝበው፣ ረቂቅ አዋጁ ይህን ማድረግ የሚያስችልና የሚያሰራ እንዲሆን ከባለድርሻዎች ገንቢ ሀሳቦች መገኘታቸውን አስታውቀዋል። በቴክኖሎጂ ድጋፎችና የማበረታቻ ስራዎች ላይ በትኩረት እና በስፋት እንደሚሰራም ጠቁመው፣ የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሰፊ ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

ወይዘሮ ሄለን እንዳስታወቁት፤ የቤት አቅርቦት ስራ ላይ በየትኛውም አገር ቴክኖሎጂውን የሚያቀርበው መንግስት ሳይሆን ባለሀብቱ ነው። የሀገር ውስጥ አልሚ ባለሀብቶች የፋይናንስ እና የቴክኖሎጂ አቅም ማደግ አለበት።

ከውጭ ባለሀብት ጋር በተያያዘ ሲያብራሩም የቤት አቅርቦት ዘርፉ ማደግ እንደሚገባው አስታውቀው፣ ለእዚህም ሲባል ዘርፉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጉን ገልጸዋል። የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለማንኛውም የውጭ ዜጋ ክፍት በሆነበት ሁኔታ ከመሸጥና ከመግዛት በላይ በሆነው የቤት ዘርፉም ሚናው ከፍተኛ መሆኑን አመልክተዋል። ዘርፉ ሰፊ ትኩረት ይፈልጋል፤ መገደቡ አደጋ አለው ሲሉ ጠቅሰው፣ አገራችንም በዘርፉ ዓለም አቀፍ ገበያ ለመግባት ከምታደርገው ጥረት ጋር ተናባቢ እንዲሆን ለማድረግ እንደሚሰራበት አመላከተዋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የከተማና መሰረተ ልማት እና የትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ አቶ እሸቱ ተመስገን በበኩላቸው የመጨረሻ ተጠቃሚ የሆነው የማህበረሰብ ክፍልን ተደራሽ በሚያደርገው የቤት ጉዳይ ላይ የተነሱት ሀሳቦች ገንቢ መሆናቸውን አመላከተዋል።

ለዘርፉ ልማት አስፈላጊ የሆነው የሞርጌጅ ባንከን በተመለከተ ሲያብራሩም፤ አቢድ ግሩፕ፣ የጎህ ባንክ፣ አፍሪካን ሆልዲንግ በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፣ በተናጠል ከመስራት ይልቅ በጋራ አንድ ጠንካራና ግዙፍ የቤት ልማቱን የሚያግዝ የሞርጌጅ ባንክ ቢፈጠር የተሻለ ስለመሆኑም ጠቁመዋል።

በመንግስት በኩል በቤት ዘርፉ ለሕዝቡና ለአገሪቱ ጥያቄዎች በቂና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የአገራትን ምርጥ ተሞክሮ መውሰድ ላይ ዝግጁነት መኖሩን ጠቁመዋል። የአርክቴክት፣ የፕላን፣ የሲቪል ኢንጂነሮች እና የመሳሰሉ ማህበራት እንዲሁም የስራ ተቋራጮች ማህበር ገንቢ ግብአቶችንና ስልጠናዎችን ለመውሰድ ዝግጁነቱ እንዳላቸውም አስታውቀዋል።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ነፃ ሃሳብ

# ተጠያቂነት ያልሰፈነበት የሪል ስቴት ዘርፍ

**መኮንን ፀጋው (ኢንጂነር)**

የቤት ባለቤት መሆን የተረጋጋ ሕይወት ለመኖር ዋናው እና መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ መቼም ለማንም ግልጽ ነው። ይህን ፍላጎቴን ለማሟላት ደግሞ ወደዛ ወደዚህ ስል አንድ (ስሙን መጥቀስ የማልፈልገው) ሪል ስቴት ቦሌ መድኃኒዓለም አካባቢ በሚገኘው የሽያጭ ማዕከሉ ጋብዞኝ በክብርና በትህትና አስተናገደኝ። ሠራተኞቹ ሪል ስቴቱ የሚሠራውን ለማስረዳት እና ለመሸጥ የሚያደርጉት መስተንግዶ የሚደነቅ ነው። እኔም ማድነቅ ብቻ ሳይሆን ለሠራተኞቹ ያለኝን አድናቆትና ምስጋና ከፍ ያለ መሆኑን ገለጽኩላቸው።

በአጠቃላይ ከሪል ስቴቱ የተገለጸልኝ ነገሮች፤ መሀል አዲስ አበባ ላይ የተለያየ መጠን ያላቸው አፓርትመንቶች ለሽያጭ ማቅረባቸውን፣ የሽያጭ ዋጋቸው በካሬ ሜትር 1026 የአሜሪካ ዶላር መሆኑን። ክፍያ ሲፈፀም ክፍያ በሚፈፀምበት ዕለት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዶላር በሚሸጥበት ምንዛሬ ታስቦ እንደሆነ። እንዲሁም ቅድሚያ ክፍያ 15 በመቶ ሲሆን ቀሪውን ቤቱ ተሰርቶ እስከሚያልቅ በተያዘለት ፕሮግራም መሠረት በሰላሳ ወራት ስለመከፈሉ አብራሩልኝ።

በተጨማሪም በረጅም ጊዜ ክፍያ መግዛት ለሚፈልግ ግለሰብ ደግሞ 60 በመቶ እና በ40 በመቶ የሽያጭ አማራጮችን ስለማቅረባቸው አስረዱኝ። ይህም 60 በመቶውን በ30 ወራት ከፍሎ ቀሪውን 40 በመቶ ደግሞ ከ20 እስከ 30 ዓመት ብድር ከ9.5 በመቶ ወለድ ጋር የሚከፈል ማለት ነው አሉኝ። ሪል ስቴቱ የቤት መሥሪያ ቁሳቁስ ስፔስፊኬሽን ማዘጋጀቱንም አከሉልኝ።

መቼም ለእንደኔ ዓይነት ቤት ፈላጊ ከላይ በገለፃ የተዘረዘሩት መልካም የሚባሉ ቢሆኑም አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑልኝ ጉዳዮች ነበሩ። ለዚህም ገለፃቸውን ሲጨርሱ ጠብቄ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ጀመርኩኝ። ለምከፍለው ቅድመ ክፍያ የባንክ ዋስትና አለው ወይ? ቤቱን የምትሠሩት ሁሉንም ወጪያችሁን በውጭ ምንዛሬ የማትገዙት ስለሆነ እንዴት 100 በመቶ በውጭ ምንዛሬ ሂሳብ ትሸጣላችሁ? የቤት መሥሪያ ወጪያችሁን ለመሬት፣ ለቁሳቁስ ለዲዛይን ለሠራተኛ ዓይነት በዓይነት ዘርዝራችሁት ከoverhead እና profit (የትርፍ ህዳግ) ጋር ልታሳውቁኝ ትችላላችሁን? የሚሉ ነበር።

እነርሱም በጥያቄዎቹ ደስተኛ ባይሆኑም ያው መልስ መመለስ ስለነበረባቸው እያቅማሙ ተከታዩን መልስ ሰጡኝ፤ በቅድመ ክፍያ ለተከፈለው ብር የምንሰጠው ጋራንቲ (ዋስትና) የለም። ሁሉም ገዥዎች ድርጅቱን አምነው ነው የሚገዙት አሉኝ። ይህ ማለት ድርጅቱ ወይም ሪል ስቴቱ ከከሰረ አብረው ይከስራሉ ማለት ነው ሲሉ ገለጹልኝ። እኔም መንግሥት የመገንባት ፈቃዱን ቢሰርዝበት አብረው ይከስራሉ ማለት ነው ብዬ ስጠይቅ በአዎንታ እራሱን ነቀነቀልኝ። ይህ ማለት ለእንደኔ ዓይነት ያለችውን ጥሪት አሟጦ ቤት ለሚገዛ ግለሰብ ከባድ አደጋ ወይም ጉዳት ያስከትላል ማለት ነው የሚል ድምዳሜ አለው።

ሌላው ደግሞ ቤቶቹን ለምን መቶ በመቶ በውጭ ምንዛሬ ሂሳብ ስለሚሸጡ ግልጽ አይደለም። ሲጀመር በውጭ ምንዛሬ ወይም በዶላር መሸጥ ተገቢ አይደለም፣ ሲቀጥል ለመሬት በብር የሊዝ ከፍሎ፣ ለሠራተኛ በብር ደመወዝ ከፍሎ፣ በቀላሉ ለአሸዋ፣ ሲሚንቶና ለጠጠር በብር ከፍሎ አሰርቶ ሁሉን ነገር ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ አስገብቶ የሚሠራ ይመስል በዶላር ማድረግ ከሕገ ወጥ ግብይቱም በላይ ዜጎችን መዝረፍ ነው የሚል ድምዳሜ አለኝ። ከሁሉም በላይ ግን በይፋ እንደዚህ ሲሰሩ የመንግሥት ዝም ማለት የሚለው ግርምት ፈጠረብኝ።

ምክንያቱም መታለፍ የሌለበት ጉዳይ የአልሚው ወጪ በዝርዝር በማይታወቅበት ሁኔታ ይህን የመሰለ የብዙ ሚሊዮን ብር ግዥ ያውም አልሚው ሰርቶ ሊያስረክብ ቃል በገባበትና ገዥው በተባለው ጥራት በተባለው ጊዜ ለመሠራቱ ውል ሲዋዋል ተስፋ ከማድረግ ውጭ ርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ እንዲሁም የጥራት መጓደል እና የመሳሰሉት ችግሮች ቢያጋጥም በገዥ ላይ የሚደርስን ጉዳት ለመገመት አስቸጋሪ ነው። ለምሳሌ ሪል ስቴቱ ቃል የገባውን ተለዋጭ ጄኔሬተር ባያቀርብ ወይም አቅሙ ዝቅተኛ የሆነ ቢያቀርብ ሻጭ ለገዥ ምን ያደርግለታል የሚለው መልስ የለውም። ምክንያቱም ሪል ስቴት አልሚው እመኑኝ ብቻ ነው እያለ ያለው።

ይህ አሠራር ሲበዛ ኋላቀርና ዘመናዊነት ያልነካው አሠራር ነው። በተጨማሪም አሠራሩ ዜጎችን ለዘረፋ የሚያጋልጥና ጥበቃ የማይደረግበት ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ሪል ስቴት አልሚዎች በራሳቸው ገንዘብ ሰርተው የሚሸጡ ባለሀብቶች ሳይሆኑ በመሬት ባለቤቱ መንግሥትና በመሬት ፈላጊው ቤት ሠሪ መሀል ያሉ ደላሎች ሆነው የሚንቀሳቀሱ ናቸው ማለት ይቻላል።

ምክንያቱም ቤቱ የሚገነባው ገዥው በየጊዜው ለአልሚ ነኝ ባዩ የሚከፈል ገንዘብ ስለሆነ የሪል ስቴት ባለቤት ነኝ ባዩ የሚያወጣው ቅንጣት ገንዘብ የለም። በጥሩ ምላስ ከከተማ አስተዳደሮች ወይም ክፍለ ከተማዎች ጋር ተግባብቶ በምትኩ መሬት ተረክቦ እና በተዘዋዋሪ መንገድ ሸጦ የሚበለጽግ ጥገኛ ነው።

በሀገራችን ለቃላቸው የታመኑ ሪል ስቴት አልሚዎች ቢኖሩም በዘርፉ የሚሠራውን ሥራ ቀርቦ ወይም ተጠግቶ ለታዘበ ሰው አብዛኛዎቹ ሪል ስቴት አልሚዎች ነን የሚሉት ትላልቅ ደላላዎች ናቸው ቢባል የተሳሳተ አይሆንም። ከታናናሽ ቤት አሻሻጭ ደላላዎች የሚለዩት በመንግሥት የታወቁ፣ በጠበቃ የሚወከሉ፣ ቋሚ አድራሻ ያላቸው መሆናቸው ነው።

ለሚቀበሉት ገንዘብ ዋስትና የማይሰጡ፣ በአብዛኛው ማለትም ከ70 እስከ 85 በመቶ በሀገር ውስጥ ምርት የሚሠራን ቤት በዶላር አስበው የሚሸጡ ናቸው። በዶላር ባይሸጡም እንኳን አብዛኛው አልሚ ትርፍ ለማግበስበስ እንጂ ሀገር ለመጥቀም የሚሰሩ አይደለም ቢባል ማጋነን አይሆንም።

የሪል ስቴት ገበያ በኢትዮጵያ አዲስ አሠራር ስለሆነ ህብረተሰቡ መሠረታዊ የሆነ የግንዛቤ ችግር ቢኖርበት የሚገርም አይደለም። በአሁኑ ወቅት በዘርፉ የሚሰማው ሮሮ እና ምሬት አንድ የሪል ስቴት አልሚ የራሱ መሬት፣ ገንዘብ፣ ካፒታል እና ቴክኖሎጂ ኖሮት ቤት ጨርሶ ገንብቶ ቢፈልግ በኪራይ ቢፈልግ ደግሞ በሽያጭ ለሌላ የሚያስተላለፍ ተቋም ደረጃ የደረሰ ተቋም ያለ አይመስልም።

ሁሉም ሪል ስቴት በሚባል መልኩ ስም አለን፣ ታማኝ ነን፣ የተመሰከረልን ይሉና በማግስቱ ክህደት ሲፈጽሙ ይታያሉ። ሰው ያለውን ገንዘብ አሟጦ ከሰጣቸው በኋላ አንዴ ለቤት አይደለም አክሲዮን ነው የገዛኸው ይሉታል። አንዳንዱ ሪል ስቴት ደግሞ በ18 ወር ገንብቼ የቤት ባለቤት አደርጋለሁ ይልና እንኳን በ18 ወር በ12 ዓመትም ቃሉን መጠበቅ ተስኖት ይታያል።

ሌላው ህብረተሰቡ የግንዛቤ ችግር አለበት ሲባል በሁለት መንገድ ማስረዳት ይቻላል። አንደኛ፣ የሪል ስቴት መንደሮች በሚገነቡበት መንደር ውስጥ የጋራ መጠቀሚያ እንደ አዳራሽ፣ የጽሕፈት ቤት ወዘተ ዓይነት አገልግሎት መስጫዎች ተካተው ይሠራሉ። እያንዳንዱ የቤት ገዥ ለእነዚህ የጋራ መጠቀሚያዎች በመንደሩ ውስጥ ለራሱ ከገዛው ቤት አንፃር ተነፃፃሪ የሆነ ባለቤትነት አለው።

ሁሉም ቤቶች ከተሸጡ አልሚው በእነዚህ የጋራ መጠቀሚያዎች ላይ ምንም ዓይነት የባለቤትነት ድርሻ አይኖረውም። ምክንያቱም ገዥዎች በየድርሻቸው

**ቤት አልሚ ነን የሚሉት ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የመንግሥት እና ሕዝብ ገንዘብ የሆነውን መሬት ወስደው የሚሰሩት የሪል ስቴት ሥራ ሕጋዊ ቢመስልም ከላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች ተጠያቂነታቸው ያልሰፈነበት አሠራር ነው ማለት ይቻላል**

ቤት ሲገዙ ተከፋፍለው የከፈሉበት ስለሚሆን። ይሁን እንጂ የቤት ገዥዎች በጋራም ይሁን በተናጠል መብታቸውን ስለማያውቁ፣ አልሚዎች ሁሉንም ቤቶች ሸጠው የጋራ መጠቀሚያውን በስማቸው በማድረግ ለብቻው ለባንክ ብድር ወይም ለኢንሹራንስ ዋስትና እንደሚያሲዙት በግልፅ የምናይበት ሁኔታ ነው።

የሚገርመው ገዥዎች የሕግ ዕውቀት ማነስ ገጥሟቸው ወይም እርስ በእርስ መነጋገር አቅቷቸው ሕጋዊ ርምጃ መውሰድ አቃታቸው ብንል እንኳን የተደራጀ ቀጥተኛ የሕግ አገልግሎት ያላቸው ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች በተለይም ደግሞ ከተማ አስተዳደሮች እንዴት በቤት ገዥዎች ጀርባ ይህን ዓይነት ደባ ይፈጽማሉ ብሎ ሲቆጣጠር አይታይም።

ሌላው ከላይ እንደገለጽኩት አልሚው በራሱ መሬት እና ገንዘብ ቤቶቹን ገንብቶ አጠናቆ ለግዥ ወይም ለኪራይ ማቅረብ ሲኖርበት ነገር ግን ግንባታ ዕውቀትም ሆነ ገንዘብ በበቂ ሁኔታ ስለሌለው አማላይ ማስታወቂያ በማስነገር (በርግጥ ማስታወቂያዎች አማላይ ብቻ ሳይሆኑ የሚያስፈራሩም ናቸው ለምሳሌ ኢንፍሌሽንን እንደ አንድ ማሳመኛ የሚጠቀሙ አሉ) ከቤት ፈላጊዎች በቅድመ ክፍያ ዓይነት ገንዘብ ተሰብስቦ የሚገነቡ ናቸው።

ያልተጠናቀቀ የመሬት፣ ሊዝ ዋጋ እና የግንባታ ወጪዎች በዚህ ዓይነት ከቤት ፈላጊዎች የሚሰበሰቡ ናቸው። በብዙ ሚሊዮን ብር በዚህ ዓይነት ከቤት ፈላጊዎች ሲሰበሰብ ለቤት ፈላጊዎች የሚሰጣቸው ምንም ዓይነት ዘመናዊ ዋስትና የለም። ዋስትና አለን ብለው ቢያስቡ እንኳን በከፈሉት ገንዘብ መጠን ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ መክፈል ከሚችል ከታወቀ ዋስትና ሰጪ ድርጅት፤ እንደ ባንክ፣ ኢንሹራንስ ወይም ሌሎች የገንዘብ ተቋማት ሳይሆን ከራሱ ከአልሚው ገንዘብ ተቀብያለሁ የሚል ደረሰኝ ብቻ ነው።

ይህ አሠራር ቤት በመፈለግ ገንዘብ የሚከፍሉ ሰዎችን ከፍ ያለ የገንዘብ አለመመለስ ወይም ቤት ያለ ማግኘት ስጋት ሰለባ ያደርጋቸዋል። ከአደጋዎቹ መካከል አንዱ በቤት አልሚዎቹ ላይ የሚወሰድ ሕጋዊ ርምጃ ነው። ለምሳሌ አልሚው መክፈል የነበረበትን ግብር ሳይከፍል ቢቀር ድርጅቱ ከፍተኛ ቅጣት ቢጣልበት እና ከሌላ የገንዘብ ምንጭ መክፈል ባይችል የቤት ፈላጊዎች ገንዘብ ሊከስር ይችላል።

አልሚው በንብረቱ ከፍተኛ ገንዘብ ቢበደርበት እና መክፈል አቅቶት ወይም ገንዘቡን በሌላ መንገድ ቢያሸሸው ቤት ፈላጊዎች ከባንኩ የተለየ ቅድሚያ ገንዘባቸውን የማግኘት መብት ስለማይኖራቸው ከስረው እና አልቅሰው የሚቀሩበት ሁኔታ አለ። ከአቅም በላይ የሆኑት ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው አልሚ ነኝ ባዩ ለሌላ ሰው ቤቶቹን ቢሸጣቸው እንኳን ለተስፈኛ ቤት ገዥዎች የሚኖራቸው አማራጭ አሰልቺ የፍርድ ቤት ክርክር ነው።

ስለዚህ አሠራሩ ከፍተኛ ስጋት የተደቀነበት ነው ማለት ይቻላል። በዚህ ዓይነት በሚሊዮን ገንዘብ የሚሰሩ አልሚ ነን ባዮች ከሥራ ጥራት ጋር ተያይዞ ሊከሰት የሚችለውን ስጋት ወደ አስተማማኝ ዋስትና ሰጪ ስለማያስተላልፉት ቤት ተረካቢዎች ለብዙ ጊዜ የሚቆይ ከፍተኛ የሆነ የጥገና ወጪ ይኖርባቸዋል።

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች አልሚ ነን የሚሉት በከፍተኛ ደረጃ ቤት ፈላጊዎችን የሚያጭበረብሩበት ሁኔታ አለ። ቤት ተገንብቶ ሲያልቅ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት የሚሰጡ እንደ ውሃ ቧንቧ፣ ፍሳሽ ማስወገጃ፣ ኤሌክትሪክ መስመሮች አሠራር እና የዕቃውም ጥራት ኑሮን በቤት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ሊያውክ የሚችሉበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ አደጋ እና ወጪም የሚያስከትሉ ናቸው።

ለእነዚህ እና ሌሎች የግንባታ ግድፈቶች አልሚው፣ ገንቢው ተቋራጭ እና ዲዛይኑን የሠራው እና ጥራቱን የተቆጣጠረው አርክቴክት/ኢንጂነር በጋራ እና በተናጠል ኃላፊነት ቢኖራቸውም እንደ ገንቢ ተቋራጭ፣ ዲዛይነር እና ተቆጣጣሪ ኢንጂነሮች ቤት ፈላጊዎች እንዳያውቋቸው ስለሚደረግ በሆነ መንገድ አልሚው ቢከስር አለመታወቃቸው ከተጠያቂነት ነፃ ያደርጋቸዋል።

ለማጠናቀቅ ያህል ቤት አልሚ ነን የሚሉት ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የመንግሥት እና ሕዝብ ገንዘብ የሆነውን መሬት ወስደው የሚሰሩት የሪል ስቴት ሥራ ሕጋዊ ቢመስልም ከላይ በጠቀስኳቸው ምክንያቶች ተጠያቂነታቸው ያልሰፈነበት አሠራር ነው ማለት ይቻላል። በመሆኑም መንግሥት ምንም እንኳን በገበያ ጣልቃ ባይገባም ነገር ግን ተቋም አቋቁሞ የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት።

በተለይም ቤት ፈላጊዎች ቅድመ ክፍያ ከከፈሉበት ቀን ጀምሮ ቤቱ በስማቸው ሆኖ የባለቤትነት ካርታ ኑሯቸው፣ ግንኙነታቸውም የቤት ባለቤት እና የቤት ገንቢ ተቋራጭ መሆን አለበት። ይህን አሠራር የማይከተል ወይም የማይፈልግ አልሚ ካለ ደግሞ አልሚዎች በራሳቸው ገንዘብ አጠናቀው የሚጨርሱ መሆን አለባቸው።

# ስፖርት





## ቦስተን ማራቶን የዘገየውን የአትሌቶች ሽልማት ሊሰጥ ነው

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ብዙነሽ ዳባ እኤአ በ2014ቱ የቦስተን ማራቶን ከሁለት ኬንያውያን አትሌቶች ጋር እልህ አስጨራሽ ፉክክር አድርጋ ሁለተኛ ሆና ነበር ያጠናቀቀችው። በዚያ ውድድር ኬንያዊቷ አትሌት ሪታ ጄፕቶ ቀዳሚ ሆና ማጠናቀቋ ይታወቃል። ሦስተኛ ሆና ያጠናቀቀችው ደግሞ ሌላኛዋ ኬንያዊት ኤድና ኪፕላጋት ነበረች። ይሁን እንጂ ከውድድሩ ሁለት ዓመት በኋላ 2016 ላይ ኬንያዊቷ አትሌት ጄፕቶ ውድድሩን ያሸነፈችው አበረታች ንጥረ ነገር ተጠቅማ መሆኑ ስለተረጋገጠ አሸናፊነቷን ተነጥቃለች። በዚህም ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ብዙነሽ የውድድሩ አሸናፊ መሆኗን የቦስተን ማራቶን አዘጋጆች በወቅቱ ገልፀው ነበር።

ኬንያዊቷ ጄፕቶ ውጤቷ ከመሰረዙ በፊት የውድድሩ አሸናፊ በመሆኗ 75ሺ ዶላርና የቦታውን ክብረወሰን በማሻሻሏ ተጨማሪ የ25 ሺ ዶላር ሽልማት ተቀብላ ነበር። በዚህም ውጤቷ ተሰርዞ ኢትዮጵያዊቷ አትሌት አሸናፊ ብትሆንም ሊሰጣት የሚገባው የሽልማት ገንዘብ ግን ሳይሰጣት ቆይቷል። ባለፉት አስር ዓመታትም አትሌት ብዙነሽ የሽልማት ገንዘቡ እንዲሰጣት በትዕግስት ስትጠባበቅ ብትቆይም የውድድሩ አዘጋጆች ገንዘቡን ሳይሰጧት ቆይተዋል።

የቦስተን አትሌቲክስ ማህበር ከቀናት በፊት እንዳስታወቀው፣ የኢትዮጵያዊቷን አትሌት ብዙነሽን ጨምሮ በተመሳሳይ ምክንያት ባለፉት አርባ ዓመታት እኤአ ከ1986 ጀምሮ ሽልማታቸው ሳይሰጣቸው ለቀሩ አትሌቶች የሽልማት ገንዘቡን ሊሰጥ ውሳኔ ላይ ደርሷል።

እኤአ በ2014 የቦስተን ማራቶን ቀዳሚ ሆና ያጠናቀቀችው ኬንያዊቷ አትሌት ውጤት መሰረዙን ተከትሎ ኢትዮጵያዊቷ ብዙነሽ ደረጃዋ ወደ አንደኝነት ሲሸጋሽግ



ካለፉት ስምንት የቦስተን ማራቶን ውድድሮች ስምንት አትሌቶች የዘገየ ሽልማት ይቀበላሉ ተብሎ ይጠበቃል፣

ያስመዘገበችው 2:19:59 ሰዓትም የውድድሩ ክብረወሰን ነበር። ይህም ሽልማቷ ውድድሩን በማሸነፏ 75ሺ ዶላርና ክብረወሰኑን በማሻሻሏ ተጨማሪ 25ሺ ዶላር በአጠቃላይ አንድ መቶ ሺ ዶላር ይሆናል።

የቦስተን ማራቶን የብዙነሽን ጨምሮ ለሌሎቹም አትሌቶች በውጤት ሽግሽጉ መሠረት በየደረጃው ያለውን የሽልማት መጠን ልዩነቱን በመጪው ጥር ለመስጠት እቅድ አለው። የቦስተን አትሌቲክስ ማህበር ፕሬዚዳንት በጉዳዩ ዙሪያ ባወጡት መግለጫ ላይ የዘገየውን ሽልማት ለመስጠት የተወሰነው ከአበረታች ንጥረ ነገሮች ነፃ የሆኑ አትሌቶችን ልፋት ዋጋ ለመስጠት ታስቦ ነው ብለዋል። የማይገባቸውን ሽልማት ቀደም ብለው ከተቀበሉ አትሌቶች ሽልማቶችን የማስመለሱ ሂደት ፈታኝ መሆኑ ለሚገባቸው አትሌቶች መስጠት ያለበትን ሽልማት እንዳዘገየውም ገልፀዋል።

ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ከአስር ዓመት ትዕግስቷ በኋላ ባለፈው ዓመት የውድድሩ አዘጋጆች የሽልማት ገንዘቧን እንዳልሰጧት ይፋ ማድረጓን ተከትሎ ጉዳዩ መነጋገሪያ ሆኖ ቆይቷል። "እድሌን ነጥቃኛለች፣ ብዙ ነገር አጥቻለሁ፣ የውድድሩ አሸናፊ መሆኔን ከሰማሁ በኋላ ነገሮች የሚቀየሩ መስሎኝ ነበር፣ ግን አልሆነም" በማለት በወቅቱ አትሌት ብዙነሽ ለCBS መናገሯ ይታወሳል። ይህንን ከተናገረች በኋላ የውድድሩ አዘጋጆች ለአትሌቷ የሽልማት ገንዘቧን ባይሰጧትም ጉዳዩን የሰማ አንድ ያልተጠበቀ ሰው ግን አትሌቷ የሚገባትን ክፍያ ሊሰጣት ወስኖ ነበር፡፡

የኢትዮጵያዊቷን አትሌት ቅሬታ ከወር በፊት ያቀረበው CBS News በወቅቱ ይፋ እንዳደረገው ፣ የቦስተን ኮሌጅ ተመራቂና የቢዝነስ ሰው የሆነው ዶውግ ጉየር የተባለ የፊላዴልፊያ ነዋሪ የኢትዮጵያዊቷን አትሌት በደልና ታሪክ ዎልስትሪት ጆርናል ላይ ካነበበ በኋላ የሚገባትን የሽልማት ገንዘብ ሊሰጣት ወስኖ ነበር፡፡ ጉዳዩ የት እንደደረሰ ግን ከዚያ በኋላ በሚዲያ የተገለፀ ነገር አልታየም፡፡

የቦስተን ማራቶን አዘጋጆች ለአትሌት ብዙነሽ የሽልማት ገንዘቡን ሳይሰጡ ለአስር ዓመታት በማንገላታታቸው ትልቅ ትችት እንዲያስተናግዱና ስማቸውም እንዲጎድፍ አድርጎ ነበር፡፡ ይህንንም ተከትሎ ለኢትዮጵያዊቷ አትሌት የሽልማት ገንዘቧን ያልሰጡት ውጤቷ የተሰረዘው ኬንያዊቷ አትሌት ቀደም ሲል የተረከበችውን የሽልማት ገንዘብ ባለመመለሷ መሆኑን አስረድተዋል። የቦስተን አትሌቲክስ ማህበር በወቅቱ እንደገለፀው፣ ኬንያዊቷ አትሌት አላግባብ የወሰደችውን የሽልማት ገንዘብ እንድትመልስ ጥረት ቢያደርግም አልተሳካላትም፡፡

የቦስተን አትሌቲክስ ማህበር የዘገየውን የአትሌቶች ሽልማት ለመስጠት መወሰኑን ተከትሎ ካለፉት ስምንት የቦስተን ማራቶን ውድድሮች ስምንት አትሌቶች፣ ከቦስተን 5 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር ደግሞ ዘጠኝ አትሌቶች የዘገየ ሽልማት ይቀበላሉ ተብሎ ይጠበቃል። ለዚህም የቦስተን ማራቶን እስከ ሦስት መቶ ሺ ዶላር ወጪ እንደሚጠብቀው መረጃዎች ጠቁመዋል።

## አዲስ አበባ አስተዳደር

ከሳሽ አቶ ሄኖክ እንዳልካቸው እና በተከሳሽ ወ/ነፃነት ወልደሰንበት መካከል ስላለው ፍ/ብሄር ክስ ጉዳይ ተከሳሽ/ ወ/ነፃነት ወልደሰንበት በ02/04/2017ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ3፡45 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ኮ/ቀ ምድብ 3ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

አመልካች አቶ አበባው ይታየው እና ተጠሪ አቶ ታመነ ዮሴፍ ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 01/04/2017ዓ.ም በ5፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 9ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

አመልካች ወ/ሮ የኔነሽ ጌታሁን እና ተጠሪ አቶ መስፍን አባተ ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 27/03/2017ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 8ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በፍ/ባለመብት፡- 1ኛ ስኬት ባንክ አ/ማ በፍ/ባለዕዳ፡- 1ኛ አቶ አብዱልሰላም ሰይድ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ባለእዳ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ24/03/2017ዓ.ም በ3፡31 ሰዓት እንደፍርዱ ፈፅመው እንዲቀርቡ ችሎት እንዲቀርቡ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ ችሎት አዟል፡፡

**በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች /ፍ/ባለመብት፡- 1ኛ ስኬት ባንክ ኢ.ማ በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ፡- 1ኛ አቶ ይስሃቅ ሀይሌ ገ/እግዚአብሄር መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ26/03/2017ዓ.ም በ4፡45 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ17/04/2017 ዓ.ም በ4፡40 ሰዓት ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ ወ/ሮ ምዕራፍ ግርማ እና በተከሳሽ፡ አቶ ሸምሰዲን አብደላ ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 01/04/2017ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 7ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

ከሳሾች 1ኛ አቶ አዋሽ ይርጋ 2ኛ ወ/ሮ ኪሮስ ግርማይ እና ተከሳሾች 1ኛ አቶ ሙሉቀን አበበ 2ኛ ወ/ሮ በለጡ ኩሪ ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች በ01/04/2017ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 10ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

አመልካች ወ/ሮ ዘይነባ መሀመድ እና ተጠሪ አቶ ይመር እንድሪስ ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 08/04/2017ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 8ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/አመልካች /ፍ/ባለመብት፡- 1ኛ ፀሐይ ኢንሹራንስ አ/ማ በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ፡- 1ኛ አቶ ታምራት ሙሉጌታ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ03/04/2017ዓ.ም በ8፡02 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ17/04/2017 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

አመልካች ወ/ሮ ራሔል ሰይድ እና ተጠሪ አቶ አለማየሁ ረታ ባለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 08/04/2017ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 8ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/አመልካች /ፍ/ባለመብት፡- 1ኛ ብርሃን ኢንሹራንስ ኢ.ማ በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ፡- 1ኛ ዮሀንስ ግርማ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ ባ/ኢን ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ24/03/2017 ዓ.ም በ3፡00 ሰዓት ይዘው እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

ከሳሽ/አመልካች፡- ስኬት ባንክ አ/ማ ተከሳሽ/ተጠሪ፡- 1ኛ ዳንኤል ሀ/ማርያም 2ኛ ወንድይፍራው አለሙመካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ኢንቨስትመንት 3ኛ ባ/ኢ ምድብ ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች/ ተጠሪዎች በ30/03/2017ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**